# አዲስ ዘመን

እናድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 068 ኅዳር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በቴሌኮም ዘርፉ ሦስተኛውን ኩባንያ ወደገበያው ለማስገባት ጨረታ ወጣ

## - የኢትዮ-ቴሌኮምን 40 በመቶ ድርሻ ለመሸጥ ጨረታ ወጥቷል

ዘሳስም ግዛው

አዲስ አበባ:- የኢትዮ-ቴሌኮምን ድርሻ በከፊል ወደ ግል ዘርፉ ለማስተላለፍ እንዲሁም በቴሌኮም ዘርፉ የኢትዮጵያን ገበያ በሦስተኛነት በመቀላቀል የቴሌኮም ፍቃድ የሚያገኝ ኩባንያን ለመመልመል ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጣ።

ኢትዮ-ቴሌኮም በከፊል ወደ ግል በሚዛወርበት (ፕራይቬታይዝ በሚደረግበት) እና ኢትዮ-ቴሌኮም እና ሳፋሪኮም ኢትዮጵያን በመከተል ተጨማሪ የቴሌኮም ፍቃድ በሚሰጥበት ሁኔታ የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አሕመድ ሽዴ እና ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር እዮብ ተካልኝ እንዲሁም የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ባልቻ ሬባ ትናንት መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫው አቶ አሕመድ እንደገለጹት፤ በዓለም አቀፍ የጨረታ ሂደት ኢትዮ-ቴሌኮምን የ40 በመቶ ድርሻ ለመሸጥ ተቋርጦ የነበረውን በማስቀጠል እንደገና በአዲስ መልክ ማስጀመሩን ተናግረዋል። በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ እና የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ በሀገር አቀፍ ደረጃም ምቹ ሁኔታ ስላልነበረ መቋረጡን አስታውሰዋል።

አሁን በተፈጠረው ስምምነት መሠረት እንዲቀጥል መወሰኑንም ነው ያመለከቱት። ትግበራው የቴሌኮም ዘርፉን ተወዳዳሪነት እና እድገት እንዲሁም የዲጂታል ኢኮኖሚውን እቅድ ለማሳካት የሚያግዝ ይሆናል ብለዋል አቶ አሕመድ።

በቴሌኮም ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ደበበ ዘውዱ

# በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች የሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል

## - ትናንት 67 ባለተሳቢ የጭነት ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ ተጉዘዋል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ:- በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች የሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል ሲል የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር

በግጭት በተጎዱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የዓለም የምግብ ፕሮግራም በጎንደር ኮሪደር ወደ ትግራይ ሰብዓዊ ድጋፍ ማጓጓዝ ጀመረ

## - የዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ 40 ቶን መድኃኒት ወደ ትግራይ ልኳል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ:- ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የዓለም የምግብ ፕሮግራም በጎንደር ኮሪደር ወደ ትግራይ ክልል ሰብዓዊ ድጋፍ ማጓጓዝ መጀመሩን አስታውቋል። በዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴም 40 ቶን መድኃኒት ወደ ትግራይ መላኩን ተመልክቷል።

የዓለም የምግብ ፕሮግራም ትናንት በቲዊተር ገጹ ባሰፈረው መረጃ፤ ከሰኔ 2013 ዓ.ም ወዲህ በትናንትናው ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም የምግብ ፕሮግራም በጎንደር ኮሪደር ወደ ትግራይ የሰብዓዊ ድጋፍ የጫኑ ተሽከርካሪዎች

የዓለም የምግብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የሰላም ስምምነቱን የሚቃወሙ አካላት የትግራይ ሕዝብ ሰቆቃ ሊሰማቸው ይገባል

## - የትግራይ ተወላጆች

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ:- በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት የሚቃወሙ አካላት በጦርነቱ ምክንያት የትግራይ ሕዝብ የደረሰበት ሰቆቃና ችግር ሊሰማቸው እንደሚገባ አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡ የትግራይ ተወላጆች

የሰላም ስምምነቱን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


















ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን በዘላቂነት ማቋቋም እንደሚያስፈልግ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ አሳሰበ

ገጽ 2



ዶክተር ዮሐንስ አያሌው

## ልማት ባንክ የሦስተኛ ደረጃ ሕክምና ለሚሰጡ ተቋማት ብድር ሊሰጥ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁና በውጭ ሀገራት የሚሰጡ የሦስተኛ ደረጃ የሕክምና አገልግሎቶችን በሀገር ውስጥ መስጠት ለሚችሉ የጤና ተቋማት ብድር መስጠት ሊጀምር መሆኑን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው እንደገለጹት፤ ባንኩ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁና በውጭ የሚደረጉ የሕክምና አገልግሎቶች በሀገር ውስጥ እንዲጀመሩ ለማስቻል የሦስተኛ ደረጃ ሕክምና የሚሰጡ ተቋማትን ለመደገፍ ተዘጋጅቷል።

በዘርፉ ድጋፍ ለማግኘት ጥያቄ ያቀረቡ የጤና ተቋማት መኖራቸውን ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ የብድር ፕሮጀክቱን በቀጣዮቹ አራት ወራት ለማፅደቅና ወደ ሥራ ለመግባት መታቀዱን ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ የጤናው ዘርፍ የፋይናንስ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኘው የልማት ባንክ የፋይናንስ አጋር ሆኖ ለመቅረብ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

ከጤናው ዘርፍ ባለፈ ባንኩ የተቀናጀ የግብርና ማቀነባበሪያ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ አቅዶ ሥራ መጀመሩን አንስተዋል።

ባንኩ ከዚህ ቀደም ይስተዋልበት የነበረውን የተበላሸ ብድር ምጣኔ ወደ ጤናማነት ለማምጣት በርካታ የሪፎርም ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

አሠራሩን ቀልጣፋና ፍትሐዊ ለማድረግ ባንኩ ካከናወናቸው የለውጥ ተግባራት መካከል የባንኩ የማበደርና ብድር የማስመለስ ምጣኔ ከዓመት ዓመት መሻሻል እያሳየ ይገኛል።

ባንኩ አገልግሎቱን ቀልጣፋ ከማድረግ ባሻገር አዳዲስ አሠራሮችን እየተገበረ ሲሆን የፈጠራ ሃሳብ ላላቸውን ሰዎች ብድር መስጠት በቅርቡ ከጀመራቸው መካከል ይጠቀሳል።

ባንኩ የገቢ ንግድን በሚተኩና የወጭ ንግድን በሚያሳድጉ ፕሮጀክቶች ላይ አተኩሮ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የተለያዩ 90 ፕሮጀክቶች በሁሉም ክልሎች በሙከራ ደረጃ ለመተግበር ሥራ መጀመሩን አንስተዋል።

ሦስተኛ ደረጃ (ተርሸሪ ሌቭል) ሆስፒታል ዘመናዊ መሣሪያዎችን አካቶ የተሟላ አገልግሎትን ለታካሚዎች የሚሰጥ ነው።

በቀጣይ ከባንኩ የብድር ድጋፍ የሚያገኙ ሦስተኛ ደረጃ ሕክምና ማዕከላት ከሁለተኛና አንደኛ ደረጃ ሆስፒታሎች በሪፈር የሚላኩ ታካሚዎችን ተቀብለው አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋሟት ናቸው።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ 10 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ብድር ለተለያዩ አካላት ሰጥቷል።

# ከአንድ ማዕከል የኤሌክትሪክ አገልግሎትን መከታተል የሚያስችል ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ሊደረግ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከአንድ ማዕከል በመሆን የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለመከታተል የሚያስችል የስካዳ አውቶሜሽን አገልግሎት ተግባራዊ እንደሚያደርግ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት አስታወቀ። ተቋሙ ከመሠረተ ልማት ግንባታና ጥገና ጎን ለጎን የኤሌክትሪክ አገልግሎቱ ፈጣንና ተደራሽ እንዲሆን እየሠራ መሆኑን አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመብራት ኃይል አገልግሎት ላይ የሚታዩ የጥራት ችግሮች ተለይተው ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ሥራዎቹ በአጠቃላይ በ2017 ዓ.ም ሲጠናቀቁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኤሌክትሪክ አገልግሎት ፈጣን፣ ተደራሽ እና እንከን የለሽ ይሆናል ብለዋል።

የመብራት ኃይል አገልግሎት ጥራት እንዳይኖር ከሚያደርጉት ችግሮች አንዱ የመብራት መቆራረጥ እና ለረጅም ጊዜ ጠፍቶ መቆየት መሆኑን ያነሱት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ችግሩን ለመፍታት በቴክኖሎጂ የማገዝ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

በዚህም መብራት ሲቋረጥ የተቋረጠባቸው ሰዎች ማመልከት ሳይጠበቅባቸው የት አካባቢ መብራት እንደጠፋ የሚያሳይ (ስካዳ አውቶሜሽን) ቴክኖሎጂ እየተገነባ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ገበየሁ፤



ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ

ቴክኖሎጂው መብራት የጠፋባቸውን አካባቢዎች ከማሳየት ባለፈ ቴክኒሽያኖች መሥሪያ ቤታቸው ቁጭ ብለው የመብራት አገልግሎት እንዲገኝ ማድረግ የሚያስችል እንደሆነ ገልጸዋል።

ቴክኖሎጂው የሚያካትተው ስካዳ አውቶሜሽን እየተሠራ ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ስካዳ አውቶሜሽን ቢሮ ቁጭ ብሎ ኃይል ሲቋረጥ የት እንደተቋረጠ መረጃ የሚሰጥ ሥርዓት በመሆኑ የመብራት መቆራረጥና ጠፍቶ መቆየት ችግሮችን በብዙ መልኩ እንደሚያቃልል ጠቁመዋል። ሥራው በ2016 የሚጠናቀቅ መሆኑንም አብራርተዋል።

በተጨማሪም በዘርፉ ዘመናዊ የሬዲዮ ግንኙነት ጥቅም ላይ እንደሚውል ዶክተር ገበየሁ ጠቁመው፤ ይህም ፈጣን መረጃን ለመለዋወጥ ከማስቻሉም በላይ የመብራት መቆራረጡ መረጃ ደርሷቸው ፈጣን ምላሽ ያልሰጡ አካላትንም ተጠያቂ ማድረግ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል። ይህም ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል ሲሉ አክለዋል።

በሌላ በኩል የኃይል መቆራረጡን ለማሻሻል የውስጥ አደረጃጀቱ እንዲዘምን እየተደረገ እንደሆነ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተናግረዋል። በዚህም በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ አራት ዲስትሪክቶች ስር የኦፕሬሽን፣ የሜንቴናንስ፣ የኮንስትራክሽንና የስዊቺንግ ቡድኖች ለየብቻቸው መዋቀራቸውን አብራርተዋል።

ቀደም ሲል የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ላይ የኦፕሬሽንና የሜንቴናንስ ቡድኖች እንዳልነበሩ የጠቀሱት ዶክተር ገበየሁ፤ አደረጃጀቱ በዚህ መልኩ መሻሻሉ ለሥራ ቅልጥፍና እና ለተጠያቂነት እንዲያመች እንደሚያደርግ ጠቁመዋል። በውጤቱም አገልግሎቱ ጥራት ላይ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

በተጨማሪም የመብራት መሠረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ዘመኑ የደረሰባቸውን ዘመናዊና ጥራት ያላቸውን እቃዎች ጭምር በመጠቀም ላይ መሆናቸውን የጠቀሱት ሥራ አስፈፃሚው፤ እስካሁን የመካከለኛ ቮልቴጅ የኃይል ማስተላለፊያ ላይ በተሠራው የማሻሻል ሥራ ወደ ሁለት ሺህ ኪሎ ሜትር ከሚደርሰው ውስጥ አንድ ሺህ መታደሱን ተናግረዋል። ይህም አገልግሎቱ ላይ ጥራት እንዲኖር የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

# ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን በዘላቂነት ማቋቋም እንደሚያስፈልግ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-በሀገሪቱ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን በዘላቂነት ማቋቋም እንደሚያስፈልግ የብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ ሰብሳቢ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን አሳሰቡ።

በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የሚመራው ብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ ትናንት ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦትና ተደራሽነት ጉዳይ ላይ በመምከር የቀጣይ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል። ኮሚቴው በሀገሪቱ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የሰብዓዊ እርዳታ የሚሹ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ገምግሟል። በዚህ መነሻነትም ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን በዘላቂነት ማቋቋም ያስፈልጋል ብሏል።

በድርቅ፣ በጎርፍ እና በግጭት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ተገቢውን ትኩረት የሚፈልግና የሁሉንም ዜጋ ርብርብ እንደሚያስፈልግ አመልክቶ፤ በትግራይ፣ አፋር፣ አማራና በሌሎች አካባቢዎች በግጭት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉና ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች መንግሥት አስቸኳይ የሰብዓዊ ርዳታ በማድረስ ላይ መሆኑንና ለችግር የተጋለጡ ተረጂዎችን በዘላቂነት ማቋቋም እንደሚያስፈልግ አቶ ደመቀ አሳስበዋል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ለችግር ከተጋለጡት ዜጎች ጎን ለጎን ባለፉት ዓመታት በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎች የሚገኙ ተረጂዎችም ትኩረት እንደሚሹ ተናግረዋል።

በግጭት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው ርቀው የቆዩ ተማሪዎችና በተለያየ ምክንያት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችም ከሰብዓዊ ርዳታ በተጨማሪ የሥነ-ልቦና ድጋፍ



ሊደረግላቸው እንደሚገባም አቶ ደመቀ ጠቁመዋል።

የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦትን በተመለከተ በሀገሪቱ ካላት የተረጂዎች ቁጥር አንፃር መንግሥት ላይ የሚፈጥረው ጫና ከፍተኛ መሆኑን ያነሱት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሁሉም ሴክተሮች ሃብት ማሰባሰብና ድጋፍ ለሚሹ ዜጎች ለመድረስ መቀናጀት አለባቸው ብለዋል።

የሰብዓዊ ርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና የልማት አጋሮችም ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችንን ለማገዝ ባላቸው አቅም ሁሉ መረባረብ እንዳለባቸው ጥሪ ቀርቧል።

የግብርናና የከተማ ሴፍትኔት መርሐ ግብሮችም የተረጂዎችን ሕይወት በዘላቂነት ለመቀየር በሚያስችል መልኩ ሊሠራባቸው እንደሚገባም ነው ያነሱት።

የሚመለከታቸው ሴክተሮች፣ የፌዴራልና የክልሎች የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ተቋማት ልምዳቸውንና ሃብታቸውን በማቀናጀት በእለት ተእለት እቅዳቸው ውስጥ በማካተት መረባረብ እንዳለባቸውና ዜጎች በዘላቂነት ከተረጂነት በሚላቀቁበት መንገድ ላይ አተኩረው መሥራት እንዳለባቸዉም በአስቸኳይ ስብሰባው አቅጣጫ ተሰጥቷል።

ብሔራዊ ኮሚቴውም በየሳምንቱ በመገናኘት የሰብዓዊ ርዳታ ፍላጎት፣ አቅርቦትና ተደራሽነት ሁኔታን እየገመገመ ይቀጥላል ተብሏል።

ዜና

# ኢትዮጵያ በምትገነባቸው ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚደርሱባትን የውጭ ጫናዎች ለመቋቋም በምርምር የተደገፈ ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል

**- ትኩረቱን በዓባይ ግድብና በሌሎች ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ላይ ያደረገ ውይይት እየተካሄደ ነው**

**ሞገስ ተስፋ**



ሆሳዕና:- ኢትዮጵያ በምትገነባቸው ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚደርሱባትን የውጭ ጫና ለመቋቋም በምርምር የተደገፈ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ ተገለጸ። ትኩረቱን በዓባይ ግድብና በሌሎች ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ላይ ያደረገ ውይይት በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ እየተካሄደ ነው።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶክተር) በመድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ባህሪው ውሃ አመንጭቶ ወደ ታችኛው የተፋሰስ ሀገራት የሚፈስ ቢሆንም ከዚህ እውነታ በተቃራኒ የሚደረገው ጫና መሠረት የሌለው ነው።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ አንዳንድ የውጭ ሀገራትና ሚዲያዎቻቸው በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጫና ለማሳደር ጥረዋል፤ ኢትዮጵያ ግን እውነትን ይዛ በመጓዝ የዓባይ ግድብን ሦስተኛ ዙር ሙሌት አጠናቃ ሁለት ተርባይኖች ኃይል እያመነጩ ነው።

ሃይድሮ ፓወር በተፈጥሮው የአረንጓዴ ኢነርጂ ልማት መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፣ ዓለም የምትተረማመሰው ትልቅ የካርቦን ልቀት ያላቸው ኢነርጂዎችን በመጠቀም እርስ በእርስ በመወነጃጀል ነው፤ ኢትዮጵያ ከዚህ ነጻ በሆነ መንገድ ልማቱን አከናውና ለጐረቤቶቿ ስትሰጥ የካርበን ልቀትን በመቀነስ ትልቅ ሥራ ማሳየት የምትችልበት ነው ብለዋል። የበለጸጉ ሃገራትም ይህን ተገንዝበው ቢረዱን ጥሩ ነው፣ ነገር ግን ትልቁ ጉዳይ የዲፕሎማሲ ሥራን መሥራት ነው ብለዋል።

በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ባለፉት አስር ዓመታት ጀምሮ በርካታ ተግዳሮቶች ማጋጠማቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፣ ይታዩ የነበሩ አላግባብ ስም ማጥፋቶችን፣ የጋራ ብሔራዊ ጥቅም ስም ማጥቆር አዝማሚያዎችን መታገያ መንገድ ልክ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ያዘጋጀውን ዓይነት ፕሮግራም በማዘጋጀት ሳይንሳዊ በሆነ ደረጃ ከዓለም ማኅበረሰብ ጋር መግባባት ያስፈልጋል ብለዋል። ይህ ለዲፕሎማሲው ሥራ ትልቅ ትርጉም አለው ነው ያሉት።

ኢንጂነር ሀብታሙ (ዶክተር)፣ አንድ ዩኒቨርሲቲ የሚሠራው ሳይንሳዊ ሥራ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ግብዓት የሚሆንና ከዓለም ማኅበረሰብ የምንግባባበት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከ40 በላይ ዩኒቨርሲቲዎች አሉ፣ በዛው ልክ መሥራት አለባቸው፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባህርዳር፣አዲስ አበባ፣ አዳማና አርባምንጭ ዩኒቨርስቲዎችን ያካተተ የሃይድሮ ዲፕሎማሲ ሥራን ለማከናወን እየሠራ ሲሆን የኢትዮጵያን ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራን ለማጠናከር እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

በዓባይ ግድብ ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን ያከናወኑት ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ የዓባይ ግድብን ጨምሮ ለምትገነባቸው ሌሎች ፕሮጀክቶች ላይ የሚያጋጥሙ ተጽዕኖዎችን ለመቅረፍ የሃይድሮ ዲፕሎማሲ ሥራ እየተሠራ ነው። ዩኒቨርሲቲዎች እያደረጉ ያሉት የውይይት ፎረም ለውሃ ዲፕሎማሲው ትልቅ ግብዓት በመሆኑ ሳይንሳዊ ጥናቶች በቅንጅት ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ገልጸዋል።

በካናዳ የዓባይ ግድብ ጥምረት ሊቀመንበር ዶክተር ጌቱ ቢፍቱ በካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለፉት ሁለት ዓመታት ግማሽ ሚሊዮን ዶላር በማዋጣት ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል። ከዚህም ባሻገር በውሃ ዘርፍ እውቀቱ ያላቸው ምሑራንን በማሰባሰብ ሳይንሳዊ ሙግት እንዲደረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሀብታሙ አበበ በውይይቱ መክፈቻ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ጥቂት የውጭ ኃይሎች ኢትዮጵያ እየገነባችው ባለው የዓባይ ግድብ ሐሰተኛ መረጃዎችንና ጥናት ላይ ያልተመሠረቱ ሐሰተኛ መረጃዎችን ሚዲያዎቻቸውን ጨምሮ በማሰራጨት በኢትዮጵያ ላይ ጫና ሲያሳድሩ ቆይተዋል ብለዋል።

ለናይል ወንዝ 86 በመቶ የሚሆነውን ውሃ የምትለቀው ኢትዮጵያ በሚገባው ልክ ሳታለማ ቆይታለች። 65 በመቶ የሚሆነውም ሕዝቧ በጨለማ ውስጥ የሚኖር ነው። ስለዚህ የሚገነባው ግድብ በጨለማ ውስጥ የሚኖረውን ሕዝብ ብርሃን እንዲያገኝ ለማድረግ ነው ብለዋል።

# በኢትዮጵያ በፀሐይ ኃይል የሚሠራ ተንቀሳቃሽ የኮዲንግ እና ሮቦቲክ ቤተ-ሙከራ ተመረቀ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- ሕዋዌ ኢትዮጵያ ‘አይኮግ ኤኒዋን ካን ኮድ’ ከተባለ አገር በቀል ድርጅት ጋር በመተባበር ‘ዲጅ ትራክ ኢትዮጵያ’ የተሰኘ በፀሐይ ኃይል የሚሠራ ተንቀሳቃሽ የኮዲንግና ሮቦቲክ ቤተ-ሙከራ በአዲስ አበባ ከተማ አስመረቀ።

በምርቃቱ ወቅት በኢትዮጵያ ተንቀሳቃሽ የኮምፒዩተር ፕሮግራሚንግ እና ሮቦቲክ ሳይንስ ቤተ-ሙከራ መፈጠሩ በቴክኖሎጂ የዳበረ ትውልድ ለማፍራት ሰፊ ዕድል እንደሚሰጥ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ተናግረዋል። የተመረቀው ቤተ-ሙከራም የሮቦቲክ ሳይንስ ማሰልጠኛ ማዕከልን እንደያዘም ተገልጿል።

በመርሐ-ግብሩ ላይ የተገኙት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንዳሉት ኢትዮጵያ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2025 የዲጂታል ቴክኖሎጂን ተደራሽ በማድረግ በዘርፉ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ሥራ ፈጣሪ ዜጎችን የማፍራት ግብ ጥላ እየሠራች ትገኛለች።

የተመረቀው ተንቀሳቃሽ የኮምፒዩተር ፕሮግራሚንግ እና ሮቦቲክ ሳይንስ ቴክኖሎጂ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ተማሪዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ የቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ ዕድሉን ይፈጥራል ብለዋል ፕሮፌሰሩ።

ትምህርት ሚኒስቴር ከቻይናው ቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አምራች ሕዋዌን ጨምሮ ከበርካታ በዘርፉ ከተሠማሩ ኩባንያዎች ጋር በቅርበት እየሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

በሚኒስቴሩ የአይሲቲና ዲጅታል ትምህርት ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ዘላለም አሰፋ በበኩላቸው፤ ቤተ-ሙከራው ኢትዮጵያ በኮምፒዩተር ፕሮግራሚንግና ሶፍትዌር ዘርፍ ያለባትን የሰው ኃይል ችግር ለመቅረፍና በዘርፉ ሥራ ፈጣሪዎችን ለማፍራት ያግዛል ብለዋል።

‘አይ ኮግ ኤኒዋን ካን ኮድ’ የተሰኘው አገር በቀል ድርጅት መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ቤተልሔም ደሴ፤ በቴክኖሎጂው የኮዲንግና የሮቦቲክስ ክህሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ አስፈላጊ እየሆነ መምጣቱን ገልጸው በኢትዮጵያም ይህን ማሳደግ የሀገሪቱን እድገት ለማፋጠን ይረዳል ብለዋል።

‘ዲጅ ትራክ ኢትዮጵያ’ በዘጠኝ የክልል ከተሞች ላይ በቀጣይ ሰባት ዓመታት ውስጥ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን በሂደቱም ተንቀሳቃሽ ዲጂታል ላቦራቶሪዎችን በማስፋት ሁሉንም ክልሎች ተደራሽ ለማድረግ አቅዷል ብለዋል ወይዘሮ ቤተልሄም።

በዘርፉ በመጀመሪያው ዙር ብቻ ከ3 ሺህ 500 በላይ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን ተደራሽ ለማድረግ መታቀዱን ወይዘሮ ቤተልሔም ወይዘሮ ገልጸዋል።

የሕዋዌ የኖርዝ አፍሪካ ምክትል ፕሬዚዳንት ሊዮ ሊዩ፤ በትላንትናው እለት የተመረቀው ‘ዲጅ ትራክ ኢትዮጵያ’ በኢንኮዲንግና ሮቦቴክስ ቴክኖሎጂም በመላ አገሪቷ የሚገኙ ተማሪዎችን ተደራሽ ለማድረግ ከ75 ሺ ዶላር በላይ ወጪ የተደረገበት መሆኑን ገልጸዋል።

ተንቀሳቃሽ ቤተ-ሙከራው በዘጠኝ ክልሎች ተዘዋውሮ ለሚሰጠው ስልጠናም ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መያዙን ገልጸው፤ በኢትዮጵያ የትምህርት ዘርፉን እድገት በቴክኖሎጂ ለመደገፍና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ያስችላል ሲሉ ፕሬዚዳንት ሊዮ ተናግረዋል።

# በክልሉ የተቋቋሙ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ አስችለዋል

**ገመቹ ከድር**

ሐረር ፡- በኦሮሚያ ክልል የተቋቋሙ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረተሰብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ማስቻላቸውን የክልሉ የባሕልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ገለጹ።

የምዕራብ ሸዋ ዞን ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ሸንኮሬ እንዳለ እንደገለጹት፤ ጽ/ቤታቸው በአዲስ እሳቤ አዳዲስ ሃሳቦችን በማፍለቅ የኅብረተሰቡን ባሕላዊ እሴቶችን በማሳደግ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ለማዋል እየሠራ ነው። ከዚህ አኳያ ዞኑ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች በማቋቋም ተስፋ ሰጪ ሥራዎች በመሥራት ላይ ይገኛል።

ባሕላዊ ፍርድ ቤቶቹ ኅብረተሰቡ ፍትሕ ለማግኘት መደበኛ ፍርድ ቤት የሚያባክነውን ጊዜና ሀብት በማስቀረት በቀዬው መፍትሔ እንዲያገኝ አስችለዋል ያሉት ኃላፊዋ፤ የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቱ የኅብረተሰቡን መሠረታዊ እሴቶች ታሳቢ ያደረገ በመሆኑ ፍትሕን ከሚያዛቡ የውሸት ምስክርነቶች የጸዳ በመሆኑ በኅብረተሰቡ ዘንድ ሰላም ለማስፈን ትልቅ ሚና እንዳላቸው አስገንዝበዋል።

ፍርድ ቤቶቹ ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን ጫናን ይቀንሳል ያሉት ወይዘሮ ሸንኮሬ ሰላም ከሰፈነ ለልማት አስቻይ ሁኔታዎች እንደሚፈጠሩ ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ፡- እስከ አሁን በተሠራው ሥራ ዞኑ ካለው 590 ቀበሌዎች በ557 ቀበሌዎች የመጀመሪያ ደረጃ ባሕላዊ ፍርድ ቤት ማቋቋም ተችለዋል። ኅብረተሰቡን በማስታረቅ የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ ኑሮ በማጠናከር በኢኮኖሚው ውስጥ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ስለሚያደርግ ጽሕፈት ቤቱ ከፍትሕ ተቋማት ጋር በመሆን ሥራውን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

የኅብረተሰቡን ባህላዊ እሴቶችን በማሳደግ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ሴክተሩ ድጋፍ ያሉት ኃላፊዋ ሥራው መሬት ለማስያዝ ሚዲያው የኅብረተሰቡን ባህላዊ እሴቶች ለማስተዋወቅና ለመንከባከብ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል።

የቢሻን ጉራቻ ከተማ ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ የኔነሽ ኢደዓ በበኩላቸው፣ጽሕፈት ቤቱ ከተማዋ ባሏት ሶስት ቀበሌዎች አንድ መጀመሪያ ደረጃ ባሕላዊ ፍርድ ቤትና አንድ ደበርሳ (ይግባኝ የሚባልበት) ፍርድ ቤት በማቋቋም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህ ኅብረተሰቡ ፍትሕ ፍለጋ ወደ ሻሸመኔ የሚመላለስበት ጊዜና ሀብት እንዳይባክን አድርጓል።

ትውልዱ ባህላዊ እሴቶቹንና ታሪኩን ተረድቶ እንዲያድግ በዜግነት አገልግሎት መጻሕፍት በመሰብሰብ የንባብ ባህል በመቀየር ኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው ብለዋል። የኅብረተሰቡ እሴት የሆነው እሬቻ ሥነሥርዓት እንዲመለስ በማድረግ ኅብረተሰቡ ባህላዊ እሴቶቹን በማስተዋወቅ በከተማው ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር ያለው ማኅበራዊ ትስስርና አቃፊነት የታየበት ሁኔታዎች መኖሩን ገልጸዋል። ከተማ ያላት የቱሪዝም ሀብት ከከተማዋ በላይ በመሆኑ ከተማዋን ምቹ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጥሪ አቅርበዋል።

የክልሉ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ ሁሴን ፈይሶ በክልሉ በተከበረው ዓለም አቀፍ ቱሪዝም ቀን መዝጊያ ፕሮግራም "ትልቁ ጠላት ድህነት ነው፣ ድህነትን ለማስወገድ ባሕላዊ እሴቶችን በማስተዋወቅ በመንከባከብ ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማዋል ይገባል" ያሉ ሲሆን፣ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች አንዱ የኅብረተሰቡ እሴቶች በመሆናቸው ሁሉም በማሳደግ ኅብረተሰቡ ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት እንዲያገኝ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

# በቴሌኮም ዘርፉ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

በተለይ በቴሌኮም ዘርፉ የኢትዮጵያን ገበያ ለመቀላቀል ፍላጎት ያላቸው አካላት በወጣው ዌብሳይት መሠረት ሊወዳደሩ እንደሚችሉ ተናግረዋል። ጨረታው ከትናንት ጀምሮ ለቀጣይ ሦስት ሳምንታት እስከ እኤአ ዲሴምበር 19 ቀን 2022 (ታኅሳስ 07 ቀን 2015 ዓ.ም) ግብዓት ለማሰባሰብ ክፍት መደረጉንም ጠቁመዋል።

የኢትዮ-ቴሌኮምን ድርሻ ለመግዛት ፍላጎት ያላቸው አካላት ከትናንት ጀምሮ በአዲስ መልክ ፍላጎታቸውን እንዲገልጹ ክፍት ተደርጓል ያሉት አቶ አሕመድ፤ ጠንካራ እና አቅም ያላቸው ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ሊወዳደሩ ይችላሉ ነው ያሉት።

ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር እዮብ በበኩላቸው፤ በቴሌኮም ዘርፉ የተጀመረው ሪፎርም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና ዘርፉን ጠንካራ አድርጎ የመገንባት ዓላማን መሰነቁን ተናግረዋል። ሥራውም በአንድ በኩል ኢትዮ-ቴሌኮምን የማጠናከር በሌላ በኩል ደግሞ ዘርፉን ለውድድር የመክፈት ዓላማን ይዞ መጀመሩንም ገልጸዋል።

ኢትዮ-ቴሌኮም ባለፉት የለውጥ ዓመታት ራሱን በማሻሻል ጠንካራ ኩባንያ መሆን መቻሉን በመጠቆም፤ ዘርፉ ለውድድር ክፍት ተደርጎ ሳፋሪኮም ኩባንያ ሥራ መጀመሩንም አስታውሰዋል። የዲጂታል ኢኮኖሚውን የማሳለጥና የቴሌኮም ዘርፉን የማጠናከር ሥራውን መደገፉንም አመልክተዋል።

ባለፈው ዓመት ኢትዮ-ቴሌኮምን 40 በመቶ ለውጭው የግል ዘርፍ አሳልፎ የመሸጥ ሥራውን እንዲቋረጥ የተደረገው ሀገራዊ ሁኔታው ጥሩ ስላልነበረና ዓለም አቀፍ ማክሮ ሁኔታው የሚጋብዝ ስላልነበረ የሪፎርም ሥራውን ማሳካት አይቻልም፣ ተገቢውን ጥቅም ያሳጣል በሚል በመንግሥት ተወስኖ መሆኑን አስታውሰዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ለጊዜው በኢትዮጵያ ሦስት የቴሌኮም ፍቃድ በቂ መሆኑን መንግሥት ያምናል። ኢትዮ-ቴሌኮም ፍቃድ አለው፤ በተጨማሪነት ሁለት ኩባንያዎች እንዲገቡ ታስቧል። ከሳፋሪኮም ኩባንያ ቀጥሎ ወደ ገበያው የሚገባው ሦስተኛውን ፍቃድ ያገኛል።

ኢትዮጵያ በተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ መገኘቷ እንዲሁም በኢትዮጵያ በዘርፉ ለመሠማራት ፍላጎት መኖሩን በመመልከት ጨረታው እንዲጀመር ተደርጓል ነው ዶክተር እዮብ ያሉት።

መንግሥት የኢትዮ-ቴሌኮምን 40 በመቶ ድርሻ ወደ ግል ለማዛወር አውጥቶት የነበረው ዓለም አቀፍ ጨረታ በተፈጠረው ስምምነት መሠረትና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታውን ግምት ውስጥ በማስገባት ከሳፋሪኮም ቀጥሎ አንድ ተጨማሪ ኩባንያ ለማስገባት ሂደቱ ቀጥሏል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ባልቻ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አዲስ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፍቃድ ሰጥቶ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚሠራው ሥራ ሦስት የቴሌኮም ኦፕሬተሮች እንዲኖሩ ዕድል ይሰጣል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴው የቴክኖሎጂ አስፈላጊነቱን፣ የሀገሪቱን የቆዳ ስፋትና የሕዝብ ቁጥር በመመልከት ለጊዜው በሦስት ኦፕሬተሮች የገበያ ውድድር የቴሌኮም አገልግሎት መስጠት እንደሚቻል እምነት እንዳለውም ነው የተናገሩት።

ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ወደ ሥራ ከተሰማራበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን 17 የሚደርሱ ከተሞች ላይ ተደራሽነት እንዳለው፣ አንድ ሚሊዮን አካባቢ ደንበኞችን ማፍራት መቻሉንም ነው የገለጹት። ጨረታው በኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን ዌብ ሳይት ላይ እስከ ታኅሳስ 07 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ግብዓት ከተሰባሰበ በኋላ ወደ ጨረታ ይገባልም ብለዋል።

# በግጭት በተጎዱ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ኮሚሽን አስታወቀ። በአራት ዙር 263 ባለተሳቢ የጭነት ተሽከርካሪዎች ሄደዋል።

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በግጭት የተጎዱ የትግራይ፣ አማራና አፋር አካባቢዎች የሕዝባዊ ድጋፍ አቅርቦት እንዲደርስ በማድረግ ረገድ በመንግሥትና በሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ አካላት ትኩረት በመስጠት እየተሠራ ይገኛል። በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች የሚደረገው ሰብዓዊ ድጋፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል።

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሁም የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በራስ አቅም የሚሰጠው ድጋፍ እንዳለ ሆኖ ይሄንን በቅንጅት አስተባብሮ ሥራውን መሥራት እንዲያስችል ባለፈው ሳምንት ከአጋር አካላት ጋር ምክክር በማድረግ መግባባት ላይ ተደርሷል። ድጋፉ በመንግሥትም በአጋር አካላትም የሚሰጥ ነው። በተሳትፎ ረገድ አቅምን አሟጦ ለመጠቀም ተገቢ በመሆኑ ኮሚሽኑ በትኩረት እየሠራ ይገኛል።

በትላንትናው ዕለት 67 ተሽከርካሪዎች ለሽሬ፣ ለሽራሮና ለአክሱም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ለማድረስ መጓዛቸውን ጠቁመዋል። የትላንቱን ጨምሮ በአራት ዙሮች 263 ባለተሳቢ የጭነት ተሽከርካሪዎች መሄዳቸውን፣ ከእነዚህ ውስጥ መድኃኒትና የሕክምና ቁሳቁስን የያዘ ተሽከርካሪም መካተቱን ጠቅሰዋል።

98ሺህ357 ኩንታል እህል፣14ሺ910 ኩንታል አልሚ ምግብም፣ በድምሩ ጉዳት ለደረሰባቸው የሰሜኑ ክፍል አካባቢዎች 113ሺህ 267 ኩንታል እህልና አልሚ ምግብ በመጓጓዝ ለተጠቃሚው የኅብረተሰብ ክፍል መሠራጨቱንና አሁንም በመሰራጨት ላይ እንዳለ አመላክተዋል። ድጋፉ በወቅቱ ስሌት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊየን ወገኖችን ተደራሽ የሚያደርግ ነው ሲሉ ነው የገለጹት።

ይህ በዚህ የሚያበቃ አይደለም ያሉት አቶ ደበበ፤ የጉዳቱ መጠን በጦርነት የደረሰ በመሆኑ፤ በተለይ ምግብ ላይ በፍጥነት መድረስ የሚገባ ነገር እንዳለና በቀጣይ በሂደት የሚሠሩ ሥራዎች እንዳሉ ጠቁመዋል።

በተለይ በእነዚህ አካባቢዎች ያለውን የአደጋና የተጎጂ ሁኔታ የበለጠ ለማጠናከር ወደ ፊት የሚሠሩ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በቅንጅት መንግሥትም አጋር አካላትም የሚሠሩበት ሁኔታ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

አቶ ደበበ የጤና ጉዳይ፣ ትምህርት፣ ውሃና ሌሎች ነገሮች ላይ ያተኮሩ ድጋፎች የበለጠ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ጠቁመው፤ ከሥነ ልቦና ጉዳዮች ጋር ተያይዞም ትኩረት በመስጠት ሥራዎች በቀጣይ በቅንጅት እንደሚሠሩና ኮሚሽኑም ድጋፉን ከአጋር አካላት ጋር በመሆን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል። ይህንን የሚመሩ ልዑካን ወደ አካባቢው መሄዳቸውንም ጠቅሰዋል።

# የዓለም የምግብ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ገብተዋል። በተጨማሪም የምግብ ዕርዳታዎች እና የተመጣጠነ ምግብ እንዲሁም የሕክምና ቁሳቁሶች በተቻለ ፍጥነት በሁሉም መንገዶች ማሰራጨት እንደሚቀጥልም አስታውቋል።

በተመሳሳይ ዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ወደ ሽሬ የመጀመሪያውን በረራ ማድረጉንም አመልክቶ፤ ግጭቱ ከተቀሰቀሰ ከሁለት ዓመት በኋላ የመጀመሪያው የሆነው የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ አውሮፕላን የሙከራ በረራ በትናንትናው ዕለት ሽሬ አየር ማረፊያ አርፏል ሲል አስታውቋል።

ወደ ትግራይ የሚደረጉ የአየር በረራዎች እንደገና መጀመራቸው አስቸኳይ ሰብዓዊ እርዳታን በፍጥነት ወደ ክልሉ ለማድረስ ያግዛል ያለው ኮሚቴው፣ ይህም አፋጣኝ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸውን በርካታ ሰዎች ችግር ለመቅረፍ ይረዳል ብሏል።

በሌላ በኩል በፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ተፈፅሞ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የነበረው ጦርነት ከቆመ በኋላ አስፈላጊ የመድኃኒት አቅርቦቶችን የጫኑ ሁለት ሙሉ የጭነት መኪናዎች ኅዳር 6 ቀን 2015 ዓ.ም መቀሌ መድረሳቸውን ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበር አስታውቋል። የደረሱት መድኃኒቶች ለሕክምና ተቋማት አስቸኳይ የሕክምና ግብዓት የሚውሉ መሆናቸውን ተነግሯል።

“ይህንን የመድኃኒት አቅርቦት ማቅረባችን ለእኛ ትልቅ እፎይታ ነው። በክልሉ ያለው የጤና አጠባበቅ ሥርዓት በከፍተኛ ጫና ውስጥ በመሆኑ በአካባቢው የደረሱ የመድኃኒት አቅርቦቶች የሕክምና ዕርዳታ ለሚፈልጉ ሰዎች ሕይወት ቀጥል ናቸው” ሲሉ በኢትዮጵያ የኮሚቴው የልዑካን ቡድን መሪ ኒኮላስ ቮን አርክስ ተናግረዋል።

“በሁለቱ ዓመታት ግጭት ውስጥ በከፍተኛ ስቃይ ላሳለፉ ወገኖች ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማድረስ ተሳትፎ ላደረጉ ወገኖች ያደረጉትን ጥረት እናደንቃለን” ሲሉም አመስግነዋል።


የጭነት መኪናዎቹ 40 ቶን አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና ቁሳቁሶችን፣ የአደጋ ጊዜ መድኃኒቶችን እና የቀዶ ጥገና መሣሪያዎችን ጭነው ወደ ትግራይ መሄዳቸውን አውስተው፤ የቀረቡት ዕርዳታዎች በክልሉ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አስቸኳይ ፍላጎቶችን ለመሸፈንና ለመርዳት ያለሙ እንደሆኑ ተገልጿል።

በትግራይ የሚገኙ አንዳንድ የጤና ተቋማት አገልግሎት መስጠት ባይችሉም፣ ክፍት የሆኑት ግን መሠረታዊ መድኃኒቶች፣ መሣሪያዎች እና ሌሎች አስፈላጊ አቅርቦቶች እጥረት አለባቸው ያለው ኮሚቴው፤ የሚመለከታቸው አካላት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ፣ ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ኮሚቴ እነዚህን አቅርቦቶች በመደበኛነት ለማስቀጠልና የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦቶችን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ እንሠራለን ብሏል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የአገሪቱ ክፍል ጦርነቱ ካገረሸበት ጊዜ ጀምሮ ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ኮሚቴ እና የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በትግራይ፣ አማራ እና አፋር የተጎዱ አካባቢዎች አስቸኳይ ዕርዳታ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይህ እርዳታ ምግብን፣ አስፈላጊ የቤት እቃዎችን እና የሕክምና አቅርቦቶችን የሚያካትት እንደሆነ ተገልጿል። በጦርነት ለተጎዱ ወገኖች መድኃኒቶችን፣ የሕክምና መሣሪያዎችን፣ የአምቡላንስ አገልግሎትና የመጀመሪያ ደረጃ የሕክምና ዕርዳታ እንዲሁም የውሃ እና የንፅሕና አጠባበቅ አቅርቦትን ማሻሻልን ያካተተ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደቆዩ ታውቋል።



ሕሉፍ ኣባይ



ሙዘይ ዘርኡ



አቶ ሰለሞን ገብረእግዚአብሔር



ኢንጅነር ሱራፌል እሸቱ



ኪዳነማሪያም ሃይሉ



ወይዘሮ ባንቺ ፀሐዬ

ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

# የሰላም ስምምነቱን...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ገለጹ።

አስተያየታቸውን የሰጡት የአዲስ አበባ ነዋሪው አቶ ሰለሞን ገብረእግዚአብሔር እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት አስደሳችና አጋጣሚውን ተጠቅመው እጃቸውን ለማስገባት የፈለጉ ኃይሎችን ያሳፈረ ነው።

በአፍሪካ ሕብረት መሪነት ተነጋግረን ስምምነት ላይ መድረሳችንም ችግራችንን በራሳችን ለመፍታት የሚያስችል አቅም እንዳለን ለዓለም አሳይቷል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ስምምነቱ ከግብ እንዲደርስ ሁላችንም መረባረብ አለብን ብለዋል።

በተደላደለ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙና መሬት ላይ ሕዝቡ እየደረሰበት ያለው ችግር የማያሳስባቸው አንዳንድ አካላት ስምምነቱን ሲቃወሙ እየተስተዋለ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ ከራሳቸው ግላዊ ፍላጎት ይልቅ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ ተሰምቷቸው ከዚህ ድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል ብለዋል።

የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ መላው ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያንም የሰላም ስምምነቱን ለማደናቀፍ የሚሠሩ አካላትን በቃችሁ ሊሏቸው እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ ባንቺ ፀሐዬ በበኩላቸው፤ በተደረሰው ስምምነት የቤተሰቦቻቸውን ድምጽ መስማት በመቻላቸውና ሕዝቡም የሰላም አየር የሚተነፍስበት እድል በማግኘቱ መደሰታቸውን ገልጸዋል።

የተፈረመው ስምምነት ስኬት ላይ እንዲደርስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ ጦርነት ለማንም መልካም ሆኖ አያውቅም። በመሆኑም ያለፈውን ችግር በመርሳትና ይቅር በመባባል ሕዝቡ ወንድማማችነቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል መሥራት አለብን ብለዋል።

ቤተሰቦቻቸውን በተስተካከለ ሁኔታ ውስጥ አስቀምጠው የደሃ ልጅ በጦርነት እንዲማገድ የጦርነት ነጋሪት ሲጎስሙ የነበሩ አካላት መኖራቸውን አስታውሰው፤ በጦርነቱ ምክንያት ሕዝቡ ላይ የደረሰው መከራ ሳያሳዝናቸው የሰላም ስምምነቱን እየተቃወሙ ነው ብለዋል።

በመሆኑም ሀገራችንና የሕዝባችን ሰላም ግድ የሚለን ሁሉ እነዚህን የግጭት ነጋዴዎች በጋራ ልንታገላቸው ከዚህ እኩይ ድርጅታቸው እንዲታቀቡ ልናደርጋቸው ይገባል ብለዋል።

ኢንጅነር ሱራፌል እሸቱ የተባሉ የአዲስ አበባ ነዋሪ በበኩላቸው እንደሚሉት ደግሞ፤ የሰላም ስምምነቱ ለትግራይ ሕዝብና እንደ ሀገር ለኢትዮጵያ ትልቅ እፎይታ የሚሰጥ ነው።

ቀጣይ የቤት ሥራችን ስምምነቱ ከዳር እንዲደርስ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ የምንሠራበትና ሕዝቡ ከደረሰበት ችግር እንዲያገግም ማድረግ ነው ያሉት ኢንጂነር ሱራፌል፤ ሰላም ሁላችንም እኩል አትራፊ የምንሆንበት ስለሆነ ለስኬቱም የየድርሻችንን አስተዋጽኦ ማበርከት አለብን ብለዋል።

የሰላም ስምምነቱ ዳግም እንደ ሀገር ያሸነፍንበት መድረክ መሆኑን ጠቁመው፤ የሕዝቡን ሰቆቃ ከግምት ባላስገባ መልኩ ሰበብ እየደረደርን ስምምነቱን መቃወም ተገቢነት የሌለው ተግባር ነው። በመሆኑም በውጭ ሀገራትና በሌሎችም የተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች በችግር ውስጥ የሚገኘውን የትግራይ ሕዝብና ኢትዮጵያን አስቀድመው ለሰላም ስምምነቱ መሳካት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት መዘጋጀት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

በተያያዘ ዜና ሃሳባቸው ለትግራይ ቴሌቪዥን የሰጡት የሓውዜን ወረዳ አርሶ አደሮች አቶ ሕሉፍ ኣባይ፣ ኪዳነማሪያም ሃይሉ፣ ሙዘይ ዘርኡ የሰላም ስምምነቱ ለትግራይ ሕዝብ በተለይ ለገበሬው ደስታ እንደፈጠረለት የተናገሩ ሲሆን ስምምነቱ በአፋጣኝ እንዲተገበርና ወደ ቀድሞ ግብርና ሥራ ተመልሰው ልጆቻቸውን የሚያስተምሩበት ቀን እንደናፈቁ ገልጸዋል።

ይህ የሰላም ስምምነት ከተሰማ ጀምሮ ስለ ሌላ ጉዳይ ማውራት እንደረሱና ቀን ከሌት ጉጉታቸውና ሃሳባቸው ሰላም እንደሆነ ደጋግመው የተናገሩት አርሶ አደሮቹ፤ ላለፉት ሁለት ዓመታት የተፈፀመው ግፍና ስቃይ እጅጉን ቢያሳዝነንም በዚህ ሰዓት ስለ ሰላም መስማማት የበለጠ መልካም ዜና መሆኑን አስረድተዋል።

የሰላም ስምምነቱ ወደ ታች ወርዶ አሁን የሚሰሙ አንዳንድ የጦርነት ድምፆች ሙሉ በሙሉ ተዘግተው የሰላም አየር እየተነፈስን ወደ ማሳችን መሄድና ቤተሰቦቻችንን ማስተዳደር ናፍቆናል ሲሉ የተናገሩ ሲሆን እስከ አሁን ያሳለፍነው አላስፈላጊ ስቃይ ዳግም እንዳይከሰት ለሰላሙ ዘላቂነት መሥራት ይገባል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ስኬቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል!

የአንድ አገር ኢኮኖሚ ጥንካሬ መገለጫ ከሆኑ ጉዳች አንዱ ፈተናዎችን መሻገር የሚያስችል አቅም የመገንባቱና ያለመገንባቱ ፤ ከፈተናዎች በላይ የመሆኑና ያለመሆኑ እውነታ ነው። በተለይም በጦርነት ውስጥ የሚያልፍ ኢኮኖሚ የጦርነትን ሁለንተናዊ ተጽእኖ ተቋቁሞ ማለፍ የሚያስችል አቅም የመገንባቱ እውነታ ለጥንካሬው ዋነኝ መገለጫ እንደሆነ ይታመናል።

ጦርነት ለየትኛውም ዓላማ፤ በምንም ምክንያት ይቀስቀስ አጥፊነቱ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም፤ የሚያስከትለው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመትም መተኪያ የሌለው ነው። በቀጣይ አገራዊ ተስፋ/ኢኮኖሚ እድገት/ ላይም የሚፈጥረው ግርዶሽ ከፍ ያለ ፤ ከጦርነት ማግስት ጀምሮ ትልቅ አገራዊ አጀንዳም ሆኖ የሚወሰድ ነው ።

አገራችን ካሳለፈቻቸው የጦርነት ታሪኮች አንጻር ጦርነት እና ጦርነት ለሚፈጥረው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት እንግዳ አይደለችም ፤ለዚህ ችግር ትናንት /በቀደሙት ጊዜያትም/ ሆነ ዛሬ ብዙ ዋጋ ከፍላለች። ለዘመናትም ከጦርነት አገግማ ዜጎቿን ከችግሮቻቸው መታደግ የሚያስችል ኢኮኖሚ መገንባት ሳትችል ቀርታለች ።

የለውጥ ሀይሉ ወደ ስልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ ይህን ዘመን ተሻጋሪ ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት ከፍ ያለ አገራዊ መነቃቃት መፈጠሩ ይታወሳል፤ ይህንንም ተከትሎ ብዙ ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴዎችና ተጨባጭ ውጤቶች ተመዝግበዋል። በዚህም የሕዝባችን ነገዎች በአዲስ የተስፋ ብርሀን ወጋገን ፈክተው ታይተዋል።

ይህ የተስፋ ወጋገን ብዙም ሳይቆይ በአገሪቱ በተቀሰቀሱ ግጭትና ጦርነት ምክንያትጨልሟል። በተለይም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተቀሰቀሰው ጦርነት አገርና ሕዝብ ብዙ ዋጋ ለመክፈል ተገደዋል። ጦርነቱ ያደረሰው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመትን በአግባቡ ባላገገመው አገራዊ ኢኮኖሚ ላይ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆን ከፍ ያለ የጥፋት ምንጭ ሆኗል።

መንግስት የአገርን ህልውና የተፈታተነውን ጦርነት /አገርን እንደ አገር የማስቀጠል ጦርነት/ በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጦርነቱን የሚሸከም ኢኮኖሚ ለመገንባት የሄደበት መንገድ እጅግ ፈታኝ እንደነበርና አሁንም አገርን እንደ አገር እየተፈታተነ እንደሚገኝ የአደባባይ እውነት ነው። በዚህ ሂደት የተገኘው እና እየተገኘ ያለውም ውጤት አገርን የመታደጉ ስኬት አቅም ሆኖ ታይቷል።

የግንባር ላይ ጦርነቱን ጨምሮ በኢኮኖሚው ግንባር በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር ውስጥ የተከፈተውን የተቀናጀ ጦርነት በአሸናፊነት ለመወጣት መንግስት በለውጡ ማግስት የጀመረው እና በብዙ ቁርጠኝነት የተጓዘበት የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ወሳኝ ስፍራ እንዳለው ፤ ጦርነቱን መቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር እንዳስቻለ ይታመናል።

መንግስት ባልተረጋጋ ፖለቲካና በጦርነት ውስጥ ሆኖ ከፍተኛ መዋለ ነዋይ ወጥቶባቸው ተጀምረው የመጠናቀቅ ስጋት ውስጥ የነበሩ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን /የታላቁ የህዳሴ ግድብ የመሳሰሉትን / በተለየ ትኩረት በስኬት ማስኬድ መቻሉ ፤ከዚም አልፎ ሕዝብ ስለ ቀጣይ ልማት ተስፋ እንዲያደርግ ያስቻሉ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ማጠናቀቁ ሕዝቡ በለውጡ ማግስት የነበረውን የልማት ተስፈኝነት ይዞ እንዲጓዝ ረድቷል።

ከዛም ባለፈ ፖለቲካ አለመረጋጋቱንና ጦርነቱን ምክንያት በማድረግ የመላውን ሕዝባችንን ሕይወት ቀውስ ውስጥ ለመጨመር በአላማ የተንቀሳቀሱና እየተንቀሳቀሱ ያሉ ኃይሎች የጥፋት ተልእኮ ለመቀልበስ በቢሊዮን ብር የሚቆጠር ሀብት ለማፍሰስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያው የተሻለ እድል ፈጥሮለታል።

የፖሊሲ ማሻሻያው የአገሪቱ ኢኮኖሚ አውዳሚ የነበረውን ጦርነት እንዲሸከም ከማድረግም ባለፈ በፖለቲካ አለመረጋጋቱና በጦርነቱ ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ማህበራዊ ቀውሶችን በመቀነስ ጠለቶቻችን የተመኙት አገራዊ ማህበራዊ ምስቅልቅል እንዳይፈጠር ረድቷል።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከታችኛው የሳህራ አፍሪካ አገራት ሶስተኛ ግዙፍ ኢኮኖሚ እንዲሆን ያደረገው ሲሆን በምስራቅ አፍሪካ ደግሞ ቀዳሚ ኢኮኖሚ ሊሆን በቅቷል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የውጪ ኢንቨስትመንት በመሳብ ተጠቃሽ ከሆኑ አገራት ውስጥ አገራችን አንዷ እንድትሆንም አቅም ፈጥሮላታል።

አገር በቀል የፖሊሲ ማሻሻያው በቀጣይ ተስፋ የምናደርገው ሰላም የሚፈጥርለትን አቅም ተጠቅሞ አገራችንን ለዘመናት ከቆየችበት ድህነት ተላቅቃ፤ ለዜጎቿዋ የተሻለች የመኖሪያ ምድር የምትሆንበት ጊዜ ቅርብ እንዲሆን የሚያደርግም ነው። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ለማበርከት ራስን ማዘጋጀት ይጠበቃል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከትናንት በስትያ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ የሰጡት ማብራሪያና ምላሽ፤**

# ‹‹ሰላምን የሚጠሉ የጦርነት ነጋዴዎች አሉ፤ ጦርነት የሚጠሉ የሰላም አምባሳደሮች አሉ››

- የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

**ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶች 2ተኛ ዓመት የጋራ የሥራ ዘመን መክፈቻ ላይ ያደረጉት ንግግር ተከትሎ፤ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ የሰጡት ማብራሪያና ምላሽ ክፍል ሁለት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-**

ሌላው መታቀብ ነው። ምንም ቢመረት ሌብነት ካለ፤ ስንፍና ካለ ዋጋ የለውም። መታቀብ ያስፈልጋል ከሌብነትና ከስንፍና። የመጨረሻው መምረጥ ነው። ከግጭት ሰላምን፤ ከስንፍና ትጋትን፤ ከሌብነት ሃቀኝነትን። እነዚህን መርጠን ከሄድን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚም ሆነ ኢፍሌሽን ይስተካከላል። በቀደም ሰምታችሁ ከሆነ፤ አይ ኤም ኤፍ እና ወርልድ ባንክ በነበራቸው ስብሰባ በሰብ ሰሃራን አፍሪካ ያሉ አገራት አብዛኞቹ ኢንፍሌንሽን በ2 በመቶ ይጨምራል። የኢትዮጵያ ግን ምርቱ ከፍተኛ ስለሆነ በ2 በመቶ እንደሚቀንስ ተተንብይዋል። ኢንፍሌሽን የማይክሮ ኢኮኖሚያችን ስብራት ነው። በማምረት፤ ከሌብነት በመጠበቅ፤ በማጋራት፤ ብክነት በመቀነስ፤ ሁለት ሶስት አመት ብንሰራ ግን ሲግኒፊካንት ሆነ ውጤት ልናመጣ እንችላለን።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተነሳው ኢምፖርት መደረግ ሲገባቸው የተከለከሉ የሸቀጥ አይነቶች ጉዳት አያመጡም ወይ፤ በቂ ጥናት ተደርጓል ወይ የሚል ጥያቄ ተነስቷል። እንግዲህ ኢትዮጵያ በህጋዊ መንገድ፤ ናሽናል ባንክ የሚያውቀው ብቻ ከ18 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለኢንፖርት ታወጣለች። ይሄ ባንክ የሚያውቀው ነው፤ በየቦርደሩ የሚገባውን፤ በየሻንጣ የሚገባውን አይመለከትም። ከዚህ 18 ቢሊዮን ዶላር ውስጥ ከሚገቡ የሸቀጥ አይነቶች ከ6 ሺ በላይ ናቸው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡት። እኛ በቅርቡ እንዳይገቡ ጊዜያዊ እገዳ የጣልንባቸው 38 አይነቶች ናቸው።

ወደ አገር ውስጥ የሚገባው ከፍተኛ ነው። ወደ አገር ውስጥ የሚገባው 38 ቱ ላይ ለጊዜው እገዳ ተጥሎባቸዋል። ለምን ቢባል እነዚህ 38 አይነቶቹ አይተሞች ባለፈው አመት የወጣባቸው ህጋዊ ወጪ ብቻ ሲታይ ከ1 ቢሊዮን ዶላር በላይ ነው። ለማዳበሪያ ያወጣነውና ለእነዚህ 38 አይተሞች ያወጣነው ፕላስ ኦር ማይነስ እኩል ነው።

ሁለተኛው ለአገር ውስጥ ምርት ዕድል ለመስጠት ነው። ፍራፍሬ ኢምፖርት ይደረጋል። ብርቱካን ኢምፖርት ይደረጋል፤ ጭማቂ ኢምፖርት ይደረጋል፤ የታሸገ ውሃ ኢምፖርት ይደረጋል። እነዚህን አገር ውስጥ ማምረት ይቻላል፤ ለምንድን ነው ከውጭ የምናስመጣው፤ ሳሙናም ጭምር ኢምፖርት ይደረጋል።

ለአገር ውስጥ አምራቾች ዕድል ብንሰጥ በተለይ ጭማቂ አሁን ባለው ሁኔታ ከፍራፍሬ በቂ ምርት እያገኘን ስለሆነ ኤክስፖርትም እየተደረገ ስለሆነ ኢምፖርት የምናደርገውን ያዝ እናድርግ በሚል ነው። ሶስተኛው በከፊልም ቢሆን ለጥቁር ገበያ የተጋለጡ አይተሞች ናቸው። መቶ ፐርሰንት አይደለም ግን ለጥቁር ገበያ የተጋለጡ ናቸው።

አራተኛውና የመጨረሻው ምክንያት መሰረታዊ ሸቀጦች አይደሉም። ለምሳሌ ውስኪ አለበት፤ ጸጉር አለበት፤ አሻንጉሊት አለበት፤ መኪና አለበት። እነዚህ አያስፈልጉም ከእንግዲህ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ማለት ቆያቸው እንብዛም አይጎዱም። የሕይወት፣ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ አይደለም። አንዳንዱ ሌግዤሪ ስለሆነ። ወደፊት ዘና ስንል እንፈቅዳለን ለጊዜው ግን ብናቆያቸውም አይጎዱም በሚል ነው። እና በዚህ ምክንያት እንደ አገር ከምናጣው የምናገኘው ስለሚበልጥ ነው። ምንም የሚጎዱ ሰዎች የሉም ማለቴ አይደለም ይህንን ሰርተው የሚኖሩ ሰዎች ይኖራሉ፤ የሚፈልጉ ሰዎች ይኖራሉ። ግን እንደአገር ስናይ ከምናጣው የምናተርፈው ስለሚልቅ ነው። ወደፊትስ ሁኔታው እየታየ የሚከፈት ይሆናል። ለጊዜው ግን በሰፊ ጥናት እና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በውጪ ምንዛሬ ምክንያት ውስኪ እያስገባን ማዳበሪያ ማስገባት እንዳንቸገር ታስቦ ነው የተወሰነው። ይህንን የተከበረው ምክር ቤት ከግምት ቢያስገባው መልካም ይሆናል።

ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ ትክክለኛ ጥያቄ ነው። በሁለት መንገድ ማየት ያስፈልጋል። በአንድ በኩል ከኢንቨስትመንት ጋር በሚያያዝ ኢሹ መሬት አቅርቦት ላይ፤ ቀልጣፋ አሰራር ላይ አውቶሞሽንን ማስፋት ላይ እና ብድርን በሚመለከት ነው። በዚህ ረገድ መንግስት ብዙ ማረም የሚገባው ነገር አለ። መሬትን በሚመለከት በጣም ሰፊ ጊዜ ስለሚወስድብን ልለፈው እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት የመንግስትም አይደለም የሕዝብም አይደለም የደላሎችና የሌቦች ነው። መንግስትም አያዝበትም፣ ሕዝብም አያዝበትም። ይሄ ስር ነቀል ማስተካከያ ይፈልጋል።

ሕገመንግስቱ የመንግስትና የሕዝብ ነው የሚለው የደላሎች አይልም ግን ደላሎች ወስደውታል። ይህንን ማስተካከል የሚቻለው ኢንክሉሲፍ ናሽናል ዲያሎግ ያልነውን በትክክል መነጋገር ስንችል ነው። ሕገመንግስታዊ ጉዳይ ስለሆነ። ቢያንስ ቢያንስ በከተሞች መሬት የግለሰብ መሆን አለበት ቢያንስ። ባለቤቱ ይሸጠው፤ መንግስት ወይ አይሸጠው ወይ አይጠቀምበት መከራ ነው የሆነው። በአጭሩ እንድትገነዘቡ አዲስ አበባ ላይ በኋላ የመጨረሻውን ጥያቄ እመጣበታለሁ የጀመርናቸው የልማት ሥራዎች እንደመንግስት መስራት ያልቻልነው በህገወጦች ነው። በጣም በርካታ ሥራ መስራት አልቻልንም።

የመንግስት መሬት አለ የጋራ አለ የመንግስትና የሕዝብ አለ የግለሰቦች አለ። ይህንን ለይተን አርሶ አደሩን እንዳይጎዳ አድርገን ካልቀረጽን በስተቀረ አርሶአደር የማያዝበት አንድ ከንቲባ ተነስ እያለ የሚያባርረውን ቦታ የአንተም ቦታ ነው እያልን ጊዜ ልናባክን አይገባም። ከዚህ ቀደም ኖረናል አሁን ግን ጊዜው አይመስለኝም። ጥናት ይፈልጋል። በምክርቤት የምንወያይበትና የምንወስንበት ጉዳይ አይደለም። ግን ምክርቤት ሀሳብ መስጠት ስለሚቻል ነው ሀሳብ ያነሳሁት ችግር አለ።

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# ፖለቲካና ወቅታዊ

ከ ገፅ 5 የዞረ

አንችልም። ነገር ግን አሁን ባለብን ጫና ለጊዜው ብናበሌላ መንገድ በኢንቨስተሮችም ችግር አለ። ኢንቨስተሮች አካባቢ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ብዙ ፋክቶች አሉኝ ሁሉን አላነሳውም እዚህ። ለምሳሌ ድሬደዋ ላይ ፍሪ ትሬድ ዞን ተከፍቷል። ፍሪ ትሬድ ዞን ብቻ ሳይሆን ከጎኑ በጣም ዘመናዊ ጉምሩክ ለደረቅ ጭነት የሚውል የጉምሩክ ቦታም ተከፍቷል። ለምንድነው ለማቅለል ነው ሥራውን ኮምፕሌን ስለሚደረግ። የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ሲስተሙን ኦቶሜት አድርጎ የአንድ ዊንዶ ሰርቪስ መስጠት ጀምሯል። መሬትን በሚመለከት ኢንቨስተሮች እንዳይቸገሩ እዚህ አዲስ አበባ ቦሌ ለሚ ላይ የፈለገ ሰው የፈለገውን ሸድ እንዲሰራ፣ መንገድ ሰርተን፤ መብራት ስሪ ፌዝ በየቦታው አስገብተን ብትጎበኙት ይገርማችኋል። ከተማ ነው የሚመስለው ኢንቨስተር አይፈልገውም።

ኢንቨስተር የሚፈልገው የአንድ ሰው ቦታ ወስዶ ያንን ቦታ አሲዞ ብር ተበድሮ መሰረት አውጥቶ ካልቻለ መሸጥ፤ ካልቻለ ባንክ አስቸገረኝ እኮ መንግስት አስቸገረኝ፣ ከንቲባ አስቸገረኝ ማለት ነው። ይህ የብዙዎቹ ነው፤ የሚሰሩ አሉ። ግን የብዙዎች ምክንያት እርሱ ነው። የውጪዎቹም ጭምር እንደዚያ ነው። ብር ሳይመጣ ብሩም ከዚህ፣ መሬቱም ከዚህ ይሆንና የምንቸገርባቸው ቦታዎች አሉ። እኛም የእኛን እናርማለን፣ የግሉን ግን ጀኒውን ኢንቨስተር ሆኖ ከመጣ በተለይ ማዕድን ላይ፣ ግብርና ላይ፣ ቱሪዝም ላይ፣ አይሲቲ ላይ በእነዚህ ዋና ዋና የልማት ሴክተሮችና ማኑፋክቸሪንግ ላይ ከመጣ በቅርብ ድጋፍ አብረን ለመስራት ፍላጎት አለን። ቦታም እያዘጋጀን ነው ለምሳሌ አግሮ ኢንዱስትሪ እያዘጋጀን ነው። በጣም ሰፋፊ ቦታ። ታውቃላችሁ ኢንቨስተር አይገባበትም።

የመሬት ጥያቄ ግን አለ። መብራት አለ፣ ውሀ አለ፣ ሰርቪስ አለ። ፖሊስ አለ፣ ሰው እሱን አይፈልገውም። ለምን የሚለው ጥያቄ መመርመር ይኖርበታል። ሁለቱም ጋር ችግር እንዳለ ታሳቢ ማድረግ ነው። ያም ሆኖ ግን በምስራቅ አፍሪካ አሁንም ትልቁ የፎሪን ዳይሬክት ኢንቨስትመንት ያለው ኢትዮጵያ ነው። ከአራት ፐርሰንት በላይ ዕድገት አለ አሁንም። ስንሰማ ትንሽ እየለየን መስማት ያስፈልጋል። አንዳንዱን ነገር። በጣም እየደጋገሙ ይነግሩንና ያንን እንድንከተል የሚፈልጉ ሀይሎች በጣም ሰፊ ስለሆኑ። የኢንቨስትመንት ዕድገቱ ከዚህ በላይ ካላደገ በቀር አስተማማኝ ውጤት አናመጣም። መደረግም ይኖርበታል።

መስኖን በሚመለከት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሚባል የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሀ አላት። ያን ውሀ መጠቀም አለባት። ውሀ ህይወት ነው። ውሀን መጠቀም የቻለ አገር ይለማል፣ አይራብም። ቆፍረንም አላግባብ የሚባክነውን፤ ቆጥበንም መጠቀም ይኖርብናል ትክክል ነው። ከዚህ አንፃር ባለፈው ዓመት ታስታውሳላችሁ ይህንን ጉዳይ የሚሰራ በተለይ ሎ ላንድ ላይ የሚሰራ ሚኒስትሪ ካቋቋምን በኋላ በጣም በርካታ ውጤቶች እየመጡ ነው። ቅድም በተነሳው ጥያቄ እንኳን ትንሽ ኤግዛምፐል ለማንሳት ሶማሌ ላይ የሸንሌ የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ እየተከናወነ ይገኛል። አፋር ላይ የሱኖታ ፕሮጀክት እንዲሁ ጥልቅ ጉድጓድ ላይ እየሰራ ነው። ኦሮሚያ ላይ ቦረና ላይ እየተሰራ ነው። አማራ ላይ ቆቦና ግራር እንዲሁ እየተሰራ ነው። በደቡብ ሶስት ቦታዎች፣ በሲዳማ አንድ ቦታ መለስተኛ ቁፋሮዎች እየተደረጉ ነው። ይህ በከተማ የምናደርገውን አይመለከትም። ለምሳሌ ጎንደር ከፍተኛ የመጠጥ ውሀ ችግር አለ። ጎንደር አቴንሽን የሚፈልግ ሲቲ ነው። መመራት የሚፈልግ ከተማ ነው። ውሀ የለውም። ያን ችግር ለመፍታት ግድብ አስር ዓመት የፈጀ ግድብ እየተሰራ ነው። ያን ግድብ ልናፋጥን ሞክረን ሲታይ ግድቡ አንዳንድ ቦታ በጥልቀት ፈርሶ ካልተሰራ በስተቀር ከመሰረቱ ችግር አለበት። ያ እስኪፈታ ህዝቡ እንዳይጠማ ጉድጓድ የምንቆፍርባቸው ሁኔታዎች አሉ። እነዚህን አይመለከትም። ቅድም የማነሳው፤ ለጊዜው ጉድጓድ ቆፍረን የህዝቡን ጥያቄ እየመለስን በዘላቂነት ግን ግድቡን አፋጥነን በመጨረስ ዘላቂ መፍትሄ እናመጣለን ብለን እየሰራን እንገኛለን። እናም ጉድጓድ ቁፋሮ ላይ ከዛም ባሻገር ትናንሽ ግድቦች ላይ ሰፊ ስራ ተሰርቷል። ምንአልባት በአገር ደረጃ ውሀና ውሀ ማኔጅመንትን አስመልክቶ የሰራነው ስራ ባለፉት አስር ዓመታት አልተሰራም። በእርግጠኝነት። አንድ ዓመት አምና የሰራነው ነው። ብዙ ቦታ ውሀ ጋ ልምምድ እያደረግን ነው። ውጤቱን እየዋልን እያደር እናያለን። ብዙ ቦታ፣ እዚህ አዲስ አበባ። አዲስ አበባ ላይ የምታዩዋቸው አርቲፊሻል ውሃዎች የዚያ ልምምድ ውጤት ነው በየአገሩ እንዲሰፋ የተደረገው። እሱን ስናሰፋ ከውሀ ጋር ያለን ነገር እያደገ የሚሄድ ይሆናል።

ከዚህ በተጨማሪ በሺ የሚቆጠሩ ፓምፖች አስገብተን የሪጌሽን ስራ ጀምረናል። እሱም የዚሁ ውሀ መጠቀም አካል ተደርጎ ይወሰዳል። ሀሳቡ ግን ትክክል ነው ብዙ ሀብት አለን፣ መጠቀም ይኖርብናል የሚለውን ማየት ጠቃሚ ይሆናል።

ከጤና አንጻር ውሀና ጤና የተያያዙ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሙከራዎች ተደርገዋል። ጤናን በሚመለከት፣ ልክ እንደትምህርቱ የተሰሩ ስራዎች አሉ ግን በጣም ብዙ ይቀረናል። በጥሬ ዳታ ለማየት በ2011 17 ቢሊዮን ብር ነው ያወጣው። ጤናን በሚመለከት ለመድሀኒትና ለህክምና መገልገያ ዕቃዎች ባለፈው ዓመት ግን 47 ቢሊዮን ነው



ያወጣነው። በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በየአካባቢያችሁ እንደምታዩት ጥቃቅን ጤና ጣቢያዎች፣ ሆስፒታሎች፣ መስፋፊያዎች ይሰራሉ። በርከት ያሉ ኤም አይ አር መሳሪያዎች፣ ሲቲ ስካኖች፣ እንዲሁም ለአይሲዩ መገልገያ የሚሆኑ መሳሪያዎች ለማስገባት ሙከራ ተደርጓል። ነገርግን አሁንም በጣም ብዙ ስራ የሚያስፈልገን ሴክተር አንዱ ጤና ነው።

ልክ እንደትምህርቱ እኛ ቤዚክ የሆነ የጤና ተቋማት እናስፋፋለን፣ የግል ተቋማት ግን በዩኒቨርሲቲና በተሻለ ሆስፒታል ካላገዙን በስተቀር ባጠረ ጊዜ የኢትዮጵያን ጤና ችግር መፈታት ይከብዳል። ለዚህ ተብሎ የተሞከረ ሙከራ አለ፣ ውጤቱ ገና አልታየም። በስፋት ፕራይቬት ሴክተር ማስገባት ይኖርብናል። ዩኒቨርሲቲና ከፍተኛ መስመሮች ላይ። መንግስት ደግሞ ዝቅተኛ ሴክተሮች ላይ አበክሮ ቢሰራ ተደምሮ ውጤቱ ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል። እናም ከውሀ፤ ከጤና ጋር የሚያያዘውም በዚህ አግባብ ብናይ መልካም ይሆናል። ስራን በሚመለከት ስራ አጥነት ለዓለም ፈተና ነው ለኢትዮጵያም በጣም እጅግ ወሳኝ ፈተና ነው። ስራ ያጡ ሰዎች ናቸው በየቦታው እየሸፈቱ ከሽፍቶች ጋር እየተቀላቀሉ፣ በአገር ደረጃ ችግር ከሚያስከትሉብን ነገሮች አንዱ ሥራ አጥነት ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ስራ አፍ አውጥቶ «የሰራተኛ ያለህ » ይላል ይጮሀል። እርሻው «የሰራተኛ ያለህ» ይላል፣ ከተማ ውስጥ ጽዳቱ፣ ችግኙ፣ ፍሩቱ፣ «የሰራተኛ ያለህ» ብሎ ይጮሀል። ሰራተኛው ደግሞ «የስራ ያለህ» ብሎ ይጮሀል።

የሰራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆኖ የተፈጠረው ስራውም አለ፤ ሰራተኛውም አለ ድልድይ ነው የጠፋው። ድልድይ ሆኖ እነዚህን ሁለት አካላት ቢያገናኝ በጣም በርካታ ችግር ሊፈታ ይችላል፤ በሚል ሂሳብ። ይህ የሰራተኛና ክህሎት ሚኒስቴር ምንአልባት ቋሚ ኮሚቴ አይቶት ሊሆን ይችላል፣ ከተመሰረተ አንድ ዓመቱ ነው። እጅግ አመርቂ ስራ ከሚሰሩት ተቋማት አንዱ ነው። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አስር ዓመት፣ አምስት ዓመት እንደቆየ ተቋም ራሱን አደራጅቶ ለረጅም ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ምኞታችን የነበረ ው የንግግራችን ሴንተር የነበረው ጉዳይ ኢንፐሎይመንት ዳታ መደራጀት ጀምሯል። ቀደም ሲል የሰራተኛ ዳታ ውሸት ነው፣ ሲቀጠርም የሚቀርበው ዳታ ይጋነናል፣ ስራ የለም ሲባልም የሚቀርበው ዳታ ይጋነናል። እንዳደጉ አገራት በየቀኑ ስንት ሰው ስራ ያዘ ስንት ሰው ስራ አልያዘም የሚለውን ሁሉንም ሰው ማየት የሚያስችል አቅም መፍጠር አለብን የሚል ምኞት፣ ፍላጎት፣ ግምገማዎች ነበሩ። የተሳካው ዘንድሮ ነው። ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ይነን ሲስተም ዴቭሎፕ አድርጎ ስራ ጀምሯል። እየለመድን ስንሄድ ልክ እንደአደጉት አገራት በየቀኑ ስንት ሰው ስራ እንዳገኘ፣ እንደቀየረ፣ እንዳጣ እናውቃለን ማለት ነው።

ለዘንድሮ ከሶስት ሚሊዮን ሰው በላይ ስራ ለማስያዝ ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ነው። የተከበረው ምክርቤት በጥቅል ነገር እንዲገነዘብ የምፈልገው፤ ህዳሴ አልቆመም፣ ኮይሻ አልቆመም፣ በግብርና በስፋት ስራ ጀምረናል፤ ከተማ ውስጥ ህንጻ እንደምታዩት ነው። መቼም ለማየት አትቸገሩም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ ቀደም የስራ መስክ የነበረ የታጠፋ ነገር የለም። ከዚህ ቀደም የስራ መስክ ያልነበረ በጣም በርካታ ስራ ግን ተፈጥሯል። ይሄን በግሉም በመንግስትም እያስፋፋን መሄድ ይኖርብናል። ይህን ስንስፋፋ ግን ግራጅዌት ያደረጉ ተማሪዎች ስራ አጡ በሚል ብቻ ከሆነ የኢትዮጵያን የስራ አጥነት ችግር አንፈታውም። ኢትዮጵያ ውስጥ አንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የጀመሩ፣ ያጋመሱ፣ ያጠናቀቁ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ብቻ እስካሁን ባለው ቅጥር ውስጥ 68 ፐርሰንት ይይዛሉ። ሁለተኛ ደረጃ 20 ፐርሰንት ይይዛሉ፣ ቴክኒክና ሙያና ግራጁዌት በአጠቃላይ ስራ ፈላጊውና ስራ አጡ 12 ፐርሰንት ይይዛሉ። ጥያቄያችን መሆን ያለበት በዝቅተኛ ትምህርት ደረጃም፣ በመካከለኛ ትምህርት ደረጃም፣ በከፍተኛ ደረጃም የተማረ ሰው በአቅሙ ልክ ስራ የሚያገኝበት አውድ መፈጠር አለበት ነው እንጂ አስራሁለት ፐርሰንቱን ብቻ ስራ ብናስይዝ ና የሀይስኩሉንና የኢለመንተሪው ከቀረ ተመልሶ ሌላ ዕዳ ይሆናል።

የተማረና ያልተማረ የሚለያየው ለስራ ሲቀጠር ነው እንጂ ስራ ካጣና ወደጥፋት ከሄደ ሁለቱም እኩል ነው። ክላሽ ከያዘ ሁለቱም እኩል ነው። ሁለቱንም ማስቀረት በእጅጉ ያስፈልጋል።

ስራ የሚሹ ሰዎች ማሰብ ያለባቸው ነገር ስራ የሚፈጠር ነገር እንጂ እንደጠፋ እቃ የሚፈለግ ነገር አይደለም። ስራ የሚፈጠር ነው። ምን ማለት ነው ስራ? በየቦታው ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር አለ። የቤት ችግር አለ። የውሃ ችግር አለ። የምግብ ችግር አለ። የልብስ.. የሌለ ችግር የለም። ለነዛ ችግሮች መፍትሄ መፍጠር ነው ስራ ማለት። ችግር ባለበት አገር ውስጥ መፍትሄ ማምጣት የሚችል ሃይል በሙሉ ስራ ፈጠረ ማለት ነው። ነገር ግን መፍትሄ በግለሰብ ብቻ አይቻልም። ፋይናንስ ድጋፍ ያስፈልጋል። ስልጠና ያስፈልጋል። መንግስት መደገፍ አለበት። የመረጃ ልውውጥ መስራት አለበት። ለዚህ ደግሞ መንግስት ማገዝ አለበት። የግሉ ዘርፍም ማገዝ አለበት። ነገር ግን አካባቢያችንን ግራ ቀኝ ብንመለከት ስራ አለ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቤተመንግስት በ49 ቢሊዮን ብር እየገነቡ ነው። አዎ እየገነቡ ነው። ነገር ግን በ400 እና በ500 ቢሊዮን ብር ነው እየገነቡ ያሉት። ለምን 49 ቢሊዮን ብር እንደሆነ አላውቅም። ልንገነባ ያሰብነው የጫካ ቤት ይባላል። ልንገነባ ያሰብነው ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካ ኩራት የሚሆን ሳተላይት ከተማ ነው። ልንገነባ ያሰብነው የኢትዮጵያን ቤት ነው። ነገር ግን ያ ፕሮጀክት ቢያንስ 2 ቢሊዮን ዶላር እንዲያመጣና በአንድ ተኩሉ አካባቢውን ገንብተን ትርፍ ልናተርፍበት እንጂ ፓርላማ መጥተን እባካችሁ ቤተመንግስት የምንገነባበት 49 ቢሊዮን ብር ስጡን ለማለት አይደለም። አልጠየቅናችሁም፤ አንጠይቃችሁምም።

የሚገነባው ሳተላይት ከተማ ነው። የሚገነባው እጅግ ዘመናዊ የሆነ ነገር ነው። ታዩታላችሁ። ትኮሩበታላችሁ። ባትኮሩበትም ልጆቻችሁ ይኮሩበታል። አሁን ለምን ሽኩቻው መጣ። 49 ቢሊዮን ብር ከየት መጣ ስትሉ ጫካ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ነው ያለው። እኛ ስር ኢምባሲዎች አሉ። አኮረፉ ሊያዩን ነው ብለው። የኢትዮጵያ ምሁር መሳይ ሰው ራት ጋበዙና ሰወዬው በዚህ የኑሮ ውድነት በ49 ቢሊዮን ብር ቤተመንግስት ይገነባል። እንዴት ዝምብላችሁ ታያላችሁ አሏቸውና እነሱም ወጥተው ፃፉ። እዛ ስር ያሉ ኢምባሲዎች የማይታዩበትና ችግር የማይፈጠርበት መንገድ እንፈጥራለን። ራት የበሉ ምሁሮቻችን የፃፉትን ጋዜጣ እናነባለን። ጫካን ግን እንገነባለን። ጀምረን የተውነው የለም። ጀምረን የማንጭርሰው ነገርም አይኖርም። ስንጨርስ የኢትዮጵያን ልማትና ብልፅግና እንዲያፋጥን አድርገን እንጂ የኢትዮጵያን ችግር እንዲያባብስ አድርገን አንሰራውም።

ቦታው ላይ የሚገኝ ሀብት ጫካን በምንገነባበት ሞዴል አዲስ አበባ አምስትና አስር ቦታ ስራ ቢጀምር አንድ ብር መንግስት አይለምንም። እኔ ደላላ የሚጫወትበትን መሬት ተጠቅሜ ነው የምሰራው እንጂ ከማንም የምጠይቀው ገንዘብ የለም። ስራው ሲያልቅ ግን የኢትዮጵያ ቤት እንጂ የመንግስት ቤት አይደለም። የኢትዮጵያን ቤት ነው የምንገነባው። ፓርላማው ከፈለገ ትንሽ ግዜ ይስጠንና በአካል እናየዋለን። እዩትና ትመሰክራላችሁ። ነገርግን ራት ብሊታችሁ የተወሰነ ለፃፋችሁ ወንድሞቻችንና ለምታፅፉ ሰዎችም እኛ ከጀመርን አናቆምም። እና ግዜ አታባክኑ። ለምነን ሃብት አምጥትን እንሰራለን፤ ለኢትዮጵያ ኩራት የሚሆን ነገር እንገነባለን። የምንገነባው ነገር ደግሞ አንድ አይደለም ይስፋፋል። ሞዴል እንገነባለን። ያንን እያዩ ከተሞች እያዩ አካባቢዎች ያስፋፋሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ለምሳሌ ጅማ 750 ሄክታር፣ አርባ ምንጭ 400 ሄክታር ቦታ ሰጡኝ። የጅማ ቀደም ብሎ የተሰጠ ነው። ዲዛይን እያሰራን ነው። ዋናው አቅም ምንድን ነው 750 ሄክታር ማለት በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ነው። ከንቲባው አልገባውም። እንዴት ተብሎ ከተማ እንደሚሰራ ሳምፕል እናሳየዋለን። በምንድን ነው ያላችሁ እንደሆነ አምስትና አስር ሄክታር ካጠቃላይ ዲዛይኑ ላይ በመስራት ነው።

የተከበሩ አፈጉባኤ ቤት ገንቢ ቢሆኑና ሪልእስቴት ቢገነቡ በነፃ ነው 10 ሄክታር የምሰጣቸው። ግን በኔ ዲዛይን ይገነባሉ። በኔ ዲዛይን 400 እና 500 ቤት ይገነቡ እላቸዋለሁ። አንድም ብር አልፈልግም ከእርሳቸው። እርሳቸው ያንን 500 ቤት ሲገነቡ ጅማ ላይ ስንት ሰው ስራ ይይዛል በሉ። ጅማ ቀይ አፈር አለ። ሸክላ፣ ጡብና ጣራ ይሆናል። ግን የሚሰራው ሰው የለም። እርሳቸው ነፃ መሬትና እባኮትን ማሽን ያምጡ ቀዩን አፈር ጡብ የምናረግበት እላቸዋለሁ።

ጅማ እንኳን ለኢትዮጵያ ለውጪ ገበያ የሚተርፍ የእንጨት ሀብት አለ። ጠረጴዛ፣ በርና መስኮት ወደአገር ውስጥ ይገባል። ስለዚህ የጣውላ ማሽን ያምጡ እላቸዋለሁ። የጣውላና የቀይ አፈር ማሽኖችን ካመጡ በኋላ ቤታቸውን ሲገነቡ ከንቲባው ከፕሮፐርቲ ታክስ ያገኛል። በዚህም በርካታ ጡብና እንጨት የሚያመርቱ ሰዎችን እፈጥራለሁ። ከአስር አመት በኋላ አሁን የምናያት ጅማ ሌላ ጅማ ትሆናለች።

ከንቲባችን ግን ያችን ለመዋዋል ከፈለጉና ስንት ሳንቲም እለቅማለሁ ካሉ አይሰራም። አንድ ቦታ እንሞክራለን ውጤቱን እያየን እናስፋፋለን። የጫካን ፕሮጀክት በሚመለከት ሰሞኑን በጣም ስለሚራገብ እባካችሁ ለኢትዮጵያ እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ ስራ ነው። በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ቤት ይገነባል። ሆቴሎች ይገነባሉ። እንደምትሉት አይደለም። በትእግስት ብናይ መልካም ነው። ባትታገሱም ግን ስለማይቆም ግዜ ባታባክኑ ጥሩ ነው።

ቱሪዝምን በሚመለከት የተነሱ ጥያቄዎች ትክክለኛ ናቸው። ቱሪዝም የብልፅግና እአማድ ከሆኑ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። ያ የሆነበት ምክንያት ወደፊትም ኢኮኖሚያችን እያደገ የሚሄደው በዋናነት በአገልግሎት ዘርፉ ነው። የአገልግሎት ዘርፉ በጣም እያደገና እየሰፋ ነው የሚሄደው። በመሆኑም የቱሪዝም እምቅ አቅም በጣም በስፋት ያላት አገር አበክራ ብትሰራ ውጤት ታመጣለች። አንደኛ ባህል፣ ሁለተኛ ታሪክ፣ ሶስተኛ ታይተው የማይጠገቡ ቦታዎች አሉ።

ምን እየሰራችሁ ነው? ለሚለው ለምሳሌ ላልይበላ እጅግ አስደማሚ የሆነ ስራ ነው። መጠነኛ ችግር ገጥሞታል። ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ሆነን ለመጠገን ብዙ ስራ እየተሰራ ይገኛል። የነበረው ቅርስ ሳይፈርስ መቆየት ስላለበት። አክሱም የጣልያን መንግስት አግዞን ጥናት ከጀመርን በኋላ የሰላም ችግር ተፈጠረ። አሁን ሰላም ከመጣ የሚቀጥል ይሆናል። ብሄራዊ ቤተመንግስት ከዚህ ቀደም የጎበኛችሁ ይመስለኛል። በከፊል ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ፕሬዚዳንት ማክሮን አግዘውን በከፊል ደግሞ ዩኒቲ ፓርክ ከተከፈተ ጀምሮ በርከት ያለ ሃብት እያስገባ ነው ብያችኋለው፤ ዩኒቲ ፓርክ 300 ሚሊዮን ብር መድቦ በታችኛው ቤተመንግስት ላይ ኢንቨስት እያደረገ ነው። ራሱ ገቢውን ችሎ ፅዳቱን ጠብቆ 300 ሚሊዮን ብር ደግሞ ታችኛው ቤተመንግስት ኢንቨስት አድርጎ በጣም ዘመናዊ የመኪና ኤግዚቢሽን እየሰራ ነው።

ዩኒቲ የመኪና ኤግዚቢሽን ይሰራል። የፈረንሳይ መንግስት ባገዘን ድጋፍ ደግሞ ራሱ ቤተመንግስቱን በጣም በፍጥነት እየታደሰ ነው። ጥሩ ደረጃ ላይ ነው አሁን ያለው። ስድስትና ስምንት ወር ይፈጃል። ቢያንስ ግን በሚቀጥለው ዓመት መስከረም ለህዝብ ክፍት ይሆናል። ታችኛው ቤተመንግስት በከፊል እንዳያችሁት ወርቁም፣ መፅሃፉም፣ ታሪኩም፣ መኪናውም ለቱሪስት መስህብ ሆኖ በምናስበው ደረጃ ከወጣ እጅግ አስደማሚ ቦታ ነው። ኢትዮጵያ ይህን የሚያክል ነገር አላት ወይ? ብለው ሰዎች እንዲጠይቁ የሚያደርግ ቦታ ነው። እነዚህ ይጠገናሉ። ነገር ግን ቱሪዝም የነበረውን በማዘመንና በመጠገን ብቻ የሚሆን ነገር አይደለም። አዳዲስ ግንባታ ይፈልጋል። ለምሳሌ ጎርጎራ። ጎርጎራን ለማየት የተወሰናችሁ አይታችሁት ሊሆን ይችላል።

አሁንም በቅርቡ የማየት እድል አግኝተን ነበረ። ጎርጎራ እንደ ፕሮጀክት ያስደነግጣል። በተለይ ያላያችሁ ሰዎች ስትሄዱ አይናችሁ ተጨፍኖ ብትሄዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ብላችሁ ልታምኑ አትችሉም። እጅግ ግዙፍ እጅግ በጣም ውብ ስራ ነው። ግን ጎርጎራ ብቻውን አይደለም።

ከጎርጎራ ሰላሳ ደቂቃ ባህር ላይ ብንሄድ ዳጋ ላይ በብዙ አለማት ልናያቸው የማንችላቸውን ታሪኮች እናያለን። የአፄ ፋሲልና የአፄ ሲሲኒዮስ አስከሬን መቃብር እስከ አሁን ድረስ ልክ እንደ ሰው ከእነ ስማቸው ከነዘመናቸው ተቀምጧል። ይሕን የትኛውም ኪንግደም ሊያሳየን

ወደ ገፅ 7 የዞረ

**ከ ገፅ 6 የዞረ**

አይችልም። የትም ብትዞሩ እንዲህ አይነት እውቀት በቀላሉ ሊገኝ አይችልም።

ደቅ እስጢፋኖስ ሲኬድ በጣም በጣም በርካታ ታሪኮች አሉ። እዛው ሰላሳ ና አርባ ደቂቃ። ሰው ጎርጎራ ሲሄድ ታሪክ ይማራል። እጅግ በሚያምር ፍሬሽ ውሃ ያያል የውሃ አክቲቪቲ ያያል። ባማረ ቦታ ያርፋል። ከዚያም ራቅ ልበል ካለ ባህር ዳር ይሔዳል። ጎንደር ይሔዳል። ሰሜን ተራሮች ይሔዳል። ይሕ ሲያያዝ ነው ቱሪስት ተስቦ ወደ ቦታው የሚሄደው እንጂ ዳጋ ላይ እንዲህ አይነት ታሪክ አለ ብትለው ማረፊያ ከሌለው አይሄድም። ትራንስፖርት ከሌለ አይሔድም። ግንባታ ያስፈልጋል። ለእርሱም እየገነባን ነው እንደምታውቁት አላላ ኬላ ጋር የገነባነው አልሞስት አልቋል። በሚቀጥሉት አይዶኖ በሚመች ጊዜ የሚመረቅ ይሆናል። በይኑና አልቋል። ብዙዎቹ ፕሮጀክቶች እያለቁ ይገኛሉ ጊዜው ሲደርስ እየተመረቁ እየተመረቁ የምናያቸው ይሆናል። ከግንባታ እና ጥገና ውጪ ግን ሰርቪስ ያስፈልጋል።

እኛ ኢትጵያውያን ሰርቪስ ላይ ችግር አለብን። በቅርቡ እንኳን አንድ አገር ሔጄ ብዙ ነገር ተምሬ መጥቻለሁ። አልጠብቅም ነበር የሚጠብቀውም ሰው በጣም ትህትና አለው። የሚያስተናግደው ሰው በጣም ትህትና አለው። ያ ሁሉ ሰው ሰልጥኖ እንደሆነ አላውቅም። እናም እንደዚሕ አይነት ሰርቪስ እዚህ አገር አለ ወይ አፍሪካ ውስጥ ይቻላል ወይ ብዬ ጠይቄአቸው ነበር። ወታደር ልብስ የለበሰው ሰው የሚያስተናግድበት አግባብ የሚገርም ነው። እኛ ብዙ ማሻሻል ያሉብን ነገር አለ በስልጠና። ሰው ወደ እኛ ሲመጣ ተቀብለን ማስተናገድ ላይ የሚቀሩ ነገሮች አሉ። እነርሱን በስልጠና ማሳደግ አለብን።

አዲስ አበባ በሚመለከት መጨረሻ የተነሳው ጥያቄ ላይ አዲስ አበባ መተላለፊያ ሳትሆን ማረፊያ መሆን አለባት ብለን እንደ ምክትል ከንቲባ እያገለገልን እንገኛለን። እያንዳንዱ የተመዘበረ ቦታ እየሄድን እያየን ይህ ቦታ ለዚህ አገልግሎት አይሆንም ወይ እያልን እየጠየቅን ማለት ነው።

አዲስ አበባ ኮምፕሌን ካደረገ ሌሎቹ ምን እንደሚሉ አላውቅም። እዚህ አካባቢ ብቻ ያለውን እና ከዚህ ቀደም ያነሳሁላችሁን ብቻ ላንሳ። መስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያ ተሰራ። ከመስቀል አደባባይ ቀጥሎ ግዮን በጣም በጣም የሚያምር ቦታ ከመቆሸሹ በስተቀር። ባለ ስድስት ኮኮብ ሆቴል በመንግስትና በግል ትብብር እውነት ለመናገር በጣም በጣም ከፍተኛ በሆነ እስታንዳርድ በሆነ መንገድ ዲዛይንና ስምምነቱ አልቆ በቅርቡ ግንባታ ይጀምራል። ግዮን ታሪካዊነቱን ሳያጣ የአፍሪካ መሪዎች ሲሰበሰቡ ለአፍሪክ ህብረት የተሰራ ስለሆነ አሁንም በዚሁ ልክ ቪላዎች እንዲሁም የገበያ ሱቆች ያለው ሆኖ ከመኪና መቆሚያው ጋር ተያይዞ አንድ የአዲስ አበባ ድምቀት እንዲሆን እየተሰራ ይገኛል። አልተጀመረም ስራ ድርድሩ ስምምነቱ አልቋል። ከግዮን ቀጥሎ በአጥር የሚገናኘው ቤተመንግስት ቅድም አንስቼዋለሁ አሁን ያለበትን ደረጃ መመልከት ትችላላችሁ። ግን ተጨማሪ ስድስትና ሰባት ስምንት ወር ይፈልጋል። ግን በጣም ድንቅ የሆነ ስራ እዛም እየተሰራ ነው።

ከታችኛው ቤተ መንግስት ሳይንስ ሙዚየም የሚያገናኝ መካከል ላይ የነበሩ ቤቶች አብዛኛው የመንግስት ተነስተው ለመንገድ ስራ ዝግጁ ሆነዋል። ቤተ መንግስቱን ከሳይንስ ሙዚየም ለማገናኘት። ሳይንስ ሙዚየም ፍሬንድሺፕ ምእራፍ ሁለት ላይብረሪ ይሕ ቤተ መንግስት እና መኪና መቆሚያው ተገናኝቷል።

ከዚህ ቀደም የዛሬ አንድና ሁለት አመት እንዲህ አያይዘን እንሰራለን ብለን ስንናገር ንግግር ነው የሚመስለው። አሁን እዩት አሁን ያልኳችሁ ከሞላ ጎደል ተያይዟል። ይሕ ምእራፍ ሁለት በቀደም የተከፈተው በአንድ ሰንበት ከመቶ ሺ በላይ ልጆች መጥተውበታል። በአንድ ሰንበት ሰላማዊ ሰልፍ ይመስል ነበር። ይሕ የሚያሳየው በከተማችን በአገራችን ልጆች ለመዋያ ምን ያክል ፍላጎት እንዳላቸው ቦታ ቢዘጋጅ መተናፈሻ ቦታ ሰው ፍላጎት እንዳለው ያመላክታል።

ይሄንን ከወዳጆቻችን ለምነን ነው አዲስ አበባ ላይ የሰራነው። ለምነን ነው አዲስ አበባ ላይ መስራት በኮንትራታችን ውስጥ የለም። ስንዋዋል አልተዋዋልንም እንዲህ አይነት ነገር የተለመደው አሰራር የመንግስት ገቢ ሰብስቦ በጀት ሰብስቦ መስራት ነው። ከዛ በላይ ማደግ ይችላል ተብሎ ነው አዲስ አበባ እየተሰራ ያለው።

ሌላው የተቀሩ የተነሱት ጥያቄዎች በፓርላማ ምላሽ የሚያገኙ መሆናቸውን እጠራጠራለሁ። አዲስ አበባ እንዴት ሆና ነው ትክክለኛ የአፍሪካ ዋና ከተማ የምትሆነው ? እንዳልነው ነው ያለው አዲስ አበባ እንደ ስሟ አበባ ትሁን ብለን በየሄዳችሁበት አበባ ማየት የጀመራችሁት አሁን በቅርብ ሁለት ዓመት ሶስት ዓመት ነው። ይሄ የሚካድ አይደለም። በቂ ነው ወይ? አይደለም። ገና ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል፤ ብዙ ሥራ። ግን ጅማሮው አዲስ አበባ ላይ ደሃ መመገብ ይሁን፣ ተማሪ መመገብ ይሁን፣ አካባቢን ማፅዳት ይሁን ይበል የሚያስብሉ እጅግ አስደማሚ ጅማሮዎች አሉ። አዲስ አበባ ላይ አሁንም ስራ የሚፈልገው የቤት ጉዳይ ነው። ሀውሲንግ ላይ አሁን ጠንካራ የሆነ ተሳትፎ ይፈልጋል።

እኔ ፓርቲ ወክሎኝ ነው ላሉት አሁን እኔ እዚህ ውስጥ የፓርላማ ስርዓትና አሰራር ላብራራ አልችልም። የብልጽግና አባል የሆናችሁ ሰዎች በብልጽግና አባልነታችሁ የምታገለግሉት። እኔን አዲስ አበባ ላይ መርጦኝ የሰፈሬ ሰዎች አግዘውኛል ያሉት ስህተት ነው። እርሶን የመረጠም ያገዘም የለም። የመረጠው ብልጽግናን ነው። እርሶን ማን ያውቆታል። ብልጽግና ነው እንደ ፓርቲ የተወዳደረው። ኢዜማ፣ አብን ነው እንደ ፓርቲ የተወዳደረው እንጂ፤ ግለሰቦች በግል ውድድር አይደለም ፓርላማ የገባነው። ፓርቲ ወክለን ፓርላመንተሪ ስርዓት እኮ ማለት እሱ ነው። በግሉ ተወዳድሮ ያለፈ ሰው ካለ ነው እንደዛ የሚባለው እንጂ፤ ሌሎቻችሁ በፓርቲ ሪሶርስ ... ኬኒያ ውስጥ እኮ አንድ ፕሬዚዳንት ተወዳድሮ ለማሸነፍ ከ60 እስከ 100 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልገዋል። ወጪ አውጥቶ ብር ሰብስቦ ነው የሚወዳደረው። እኔ ግን እንደዛ አይደለም የምወዳደረው።

ፓርቲው ነው አስተባብሮ፣ ሁላችሁም ሰርታችሁ ነው እንጂ አጋሮ ያሸነፍኩት፤ በግሌ ብቻ አይደለም። እና ህዝብ የመረጠኝ የሚባለው ነገር ጥሩ ሆኖ ግን የፓርቲ ውክልና እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። እግረ መንገድ ለማንሳት እንጂ ጥያቄዎቹ ችግር ኖሮባቸው ሳይሆን እግረ መንገድ እዲህ በግል ሶሎ ሆኖ ለመታየት መሞከር ጥሩ አይደለም። እዚህ የግል ውክልና የለም የፓርቲ ውክልና ነው ያለው። የተመረጣችሁት የብልጽግና ማኒፌስቶ እና የብልጽግናን የልማት እቅድ አሳይታችሁ ነው። ማከናወን ያለብን እሱን ቃል የገባነውን መፈጸም ነው። ለአዲስ አበባ ቃል የገባነውን መፈጸም፤ ለኢትዮጵያ ቃል የገባን መፈጸም የጋራ ኃላፊነታችን ይሆናል። በግል ግን እኔ አጋሮን ብቻ አቶ ታገሰ ጫፎም የአርባ ምንጭን ብቻ ከሆነ አይሆንም።

እንደዛ ከሆነ አይሆንም። በዛ ሂሳብ ቢታይ ጥሩ ይሆናል። ያም ሆኖ ግን የቀረ ነገር ካለ መወያየት ያለባችሁ ነገር ካለ ለመወያየት ዝግ አይመስለኝም። የብልጽግና አባላት ከሆናችሁ የብልጽግና፤ የአብን አባላት ከሆናችሁ የአብን፤ የኢዜማ ከሆናችሁ የኢዜማ ሌላም ፓርቲ ከሆናችሁ በየ ፓርቲዎቻችሁ የውይይት መድረክ ስላለ በዛ ጉዳዮቻችሁን ማንሳት ትችላችሁ። አለበለዚያ የድሬደዋ ከተማ አንተ አወያይ፤ የአዲስ አበባን ተመራጭ፤ የኮከስ ተመራጭ አንተ አወያይ ካላችሁ እንደሱ አይሆንም። ምክንያቱም ስራ አለኝ እኔም። የተሰጠኝ ስራ ስላለ እናንተን ብቻ እያወያየሁ ልዘልቅ አልችልም። ማመዛዘን ያስፈልጋል ጊዜ ሲኖር ጥሩ ነው። አሁን ያለንበት ሁኔታን ደግሞ ትንሽ ከግምት ማስገባት ደግሞ ጠቃሚ ይመስለኛል። ከንቲባ ጋር ለምን መግባት ፈልጋችሁ እንደተከለከላችሁ ስለማላውቅ መልስ አልሰጥም፤ ግን እዛ መነጋገርና መፍታት ይቻላል። እና አዲስ አበባን በሚመለከት ብዙ ማስተካከል ያሉብን ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም ጅማሮው ግን ይበል የሚያስብል ነው ብዬ የምገምተው። ከአዲስ አበባ ሰው ጋር ብንወያይ ከዚህ ውጪ አልጠብቅም። ምክንያቱም ብዙ እየተሞከረ ስለሆነ።

በጥቅሉ ቱሪዝምን በሚመለከት አንደኛው ፕሮዳክት ላይ ሳቢ ቦታዎች ማዘጋጀት፤ ፕራይስ ላይ የሚያወዳድር አቅም መፍጠር፤ ቦታ ላይ ደግሞ ማረፊያ ምቹ ቦታዎችን ማዘጋጀት፤ ፕሮሞሽን ደግሞ መሸጥ ያስፈልጋል። እነዚህን ካደረግን የቱሪዝም ገበያው በስፋት የሚያድግ ይሆናል። በተለይ በዚህ አመት ያየነው የሎካል ቱሪዝም ስምንት በመቶ አድጓል። ማደግ የሚችል ተስፋ እንዳለው ያመላከተ ነው። እና በዚህ አግባብ ብናይ ጥሩ ሆናል።

ድርድርን በሚመለከት በርከት ያሉ ሀሳቦች ተነስተዋል። ድርድርን በሚመለከት የተከበረው ምክር ቤት ቢገነዘብ መልካም የሚሆነው የማያልቅ ጦርነት ውሃ በወፊንት ነው። ዝም ብሎ እየተዋጉ መኖር አይቻልም። ውሃ በወንፊት ዘግኖ ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላ ጫፍ መውሰድ እንደማይቻለው በቀጣይነት በውጊያ ሰርክል ውስጥ የምንሽከረከር ከሆነም የምናስባቸውን ጉዳዮች ልናሳካ አንችልም። አንድን ነገር ለማስቀጠል ከፈለግን ሌላ ነገር መተው ይኖርብናል። ሰላምና ብልጽግናን ለማስቀጠል ሲባል ጦርነትን ማቆም በእጅጉ ያስፈልጋል። ሁላችሁም ታውቃላችሁ ለእናንተ መንገር አይጠበቅብኝም እምንዋጋው ከአንድ ግንባር ጋር አይደለም። ለአንድ ሳምንት ለአንድ ወር ቢሆን ችግር የለውም። እየቀጠለ ከሄደ ግን እንደአገር እንደቃለን። ለሰላማችን ለብልጽግናችን ስንል ነው ጦርነትን ማቆም ቀዳሚ ምርጫ አድርገን የምንወስደው። በግል እንዳላችሁት ነው። በግል የሚሰማን ስሜት ብዙዎቻችሁ እንደምትሉት ነው። እናንተ እንድትገነዘቡልኝ የምፈልገው ነገር። እዛ ጋር ሆኖ ይህንን ብርጭቆ ማየትና እዚህ ጋር ሆኖ ይህንን ብርጭቆ ማየት ለየቅል ነው። እኔ እዛ ጋር ሆኜ ኢትዮጵያን ሳያት ድሮ እና አሁን ባለሁበት ሆኜ ኢትዮጵያን ሳያት በጣም በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ከግል ፍላጎት ከግል ስሜት ውጪ ይቺ ብርጭቆ እንዳትሰበር የሚደረገው ጥንቃቄ መልኩ የተለየ ነው። ይህን በተቻለ መጠን እንድትገነዘቡ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው ሀሳብ የሰላም መጥፎ የጦርነት ጥሩ ደግሞ የለውም፤ ሰላም ሁሌም ጥሩ ነው ጦርነት ሁሌም እያሸነፍክም ቢሆን መጥፎ ነው። ምክንያቱም ሰው ትገድላለህ ዶላር ትተኩሳለህ። ዶላር እየተኮስክና ሰው



እየገደልክ የሚገኝ ጥቅምና ጥሩ ነገር የለም። ሁሌም ጦርነት መጥፎ ነገር ነው። ሁሌም ሰላም ጥሩ ነገር ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያን ህልውና የኢትዮጵያን ልእልና የኢትዮጵያን አንድነት የሚገዳደር ነገር ሲፈጠር ያ ነገር በሰላም መፍትሄ የማያገኝ ከሆነ መፋለም ግዴታ ነው። ትላንትም ነበር ነገም ይቀጥላል። ምን ሲሆን አንድነታችንን ልእልናችንንና ናሽናል ኢንተረስታችንን ሲነካ። ከዚያ በመለስ ባለው ጉዳይ እነዚህን ነገሮች ማዳን ከተቻለ መነጋገር ክፉ አይደለም። ድርድርም ካለ ንግግርም ካለ ውይይትም ካለ ለኢትዮጵያ አንድነት፤ ለኢትዮጵያ እድገት፣ ለኢትዮጵያ ሰላም ብቻ ነው። ለኢትዮጵያ ሰላም አንድነትና እድገት ድርድር እንኳን አፍሪካ ውስጥ ሌላም ቦታ ካለ እንሄዳለን። ደግሞ ባለፈው ሳምንት ሄደናል። ለአገር ጥቅም ሲባል መሄድ የማንፈልግባቸው ቦታዎችም ቢሆን እንሄዳለን። ናፖሊዮን የሚባለው ተዋጊ ሰላም ከፈለክ ትግልህን አፈ ሙዙ ከመጬሁ በፊት መድፍ ከመተኮሱ በፊት አድርገው ይላል። አንዴ ከጮህ ኪሳራ ስላለው ሰላም ቀላል ነገር አይደለም። ሳይጮህ ሳይተኮስ በፊት ሰላም አብዝተህ መሻት መፈለግ ይኖርብሃል ይላል። ታስታውሳላችሁ የጥይት ድምጽ አያስፈልገንም፤ የትግራይ ህዝብ የጥይት ድምጽ መስማት ይብቃው የተባለው ጦርነት ሳይጀመር ነው። ሽማግሌዎች ሰብስበን እባካችሁ ይሄ ነገር ይቅርብን ያልነው፣ ሽምግልና የላክነው ጦርነት ሳይጀመር ነው። ከተጀመረ በኋላስ የአምናውን ብቻ ላስታውሳችሁ። አምና ጦርነቱ ሰሜን ሸዋ ደርሶ ዘምተን ጦርነቱ ከተቀለበሰ በኋላ በብዙዎቻችን ውስጥ የአሸናፊነት ስሜት ከተፈጠረ በኋላ እስረኞች እንፍታ ስንል ስንት ወዳጆቻቸን ደጋፊዎቻችን የተቀየሙት ያኮረፉት። ይዘነጋል ያ ግዜ ።

ለምን ፈታን? ያን በማድረግ ሰላም ማፅናት ከተቻለ ስለሚሻል ነው። በግል ወዳጅ ስለሆን አይደለም። ካሸነፍን በኋላ ካለ ቅድመ ሁኔታ እንወያያለን ያልነው እኛነን። ቅድመ ሁኔታ ስላልነበረን እኮ አይደለም። እንኳን ለድርድር ውጊያም (ከአቅም ሁኔታ) እየተዋጋን ስለሆነ ችግር የለውም በሚል ሂሳብ ነው። ሰላምን አብዝተን የምንፈልገው በየቀኑ ከሰላም ማትረፍ ስለምንችል ነው። ከሰላም የምታተርፈው ኢትዮጵያ ናት። ከሰላም የሚጎዳ ኢትዮጵያዊ የለም ባይባልም፤ ግን እንደ አገር ሲታይ ሰላም ትርፉማ ነው። አንዳንዶች ይቃረናሉ ለተባለው የተከበረው ምክር ቤት መገንዘብ ያለበት ሰላም የሚያስከፋቸው ኃይሎች የጦርነት ነጋዴዎች ናቸው። በዓለም ላይ መሳሪያ የሚያመርቱ አገራት ጦርነት ይፈጥራሉ ይባላል። በአገር ደረጃ ደግሞ ሲታይ በጦርነት ውስጥ ንግድና ትርፍ የሚያገኙ ሰዎች ሰላም የሚባል፤ ድርድር የሚባል ነገር አይመቻቸውም። አሉ!

ሁለተኛው ጦርነት የማይመቻቸው ሰዎች ደግሞ አሉ። ጦርነት ሲባል የሰላም አምባሳደር ስለሆኑ፣ የሰላም ሰው ስለሆኑ ጦርነት በየትኛውም ጫፍ ቢሆን ጎጂ ስለሆነ፣ አይጠቅምም ብለው የሚያስቡ አሉ። ሰላምን የሚጠሉ የጦርነት ነጋዴዎች አሉ፤ ጦርነት የሚጠሉ የሰላም አምባሳደሮች አሉ። ግራ የሚያጋባው ሰላምም ጦርነትም የማይፈልጉት ላይ ነው። ሰላም ሲሆን ጦርነት ይላሉ። ጦርነት ሲሆን ሰላም ይላሉ። እነዚህ ግራ ያጋባሉ። ግራ የሚያጋባና መልስ ልሰጥበት የምቸገረው ጉዳይ ነው። ነገር ግን ውስጣዊ ሰላም የሌላቸው ሰዎች፤ ውስጣዊ እረፍት የሌላቸው ሰዎች በውጭ የሰላም አየር መተንፈስ ማየት አይችሉም። ውጫቸው የተናደ ነው። ከሁሉም ነገር ውስጥ ችግር መዘው ችግር ማየት ይፈልጋሉ። ለእኛ ግን ከዚህ ቀደም እንዳልነው፤ አሁንም እንደምንለው ሰላም በእጅጉ ያስፈልገናል። ሰላም ማለት የጦርነት አለመኖር ብቻ አይደለም፤ የሕግ መከበር ማለት ነው። የሕግና ሥርዓት መከበር ማለት ነው። ተኩስ ሳይኖር ሕግና ሥርዓት የማይከበር ከሆነ ከሞላ ጎደል የሰው ሰላም ይናጋል። ሕግና ሥርዓት በአገራችን እንዲከበር የሚደረገው ማንኛውም ንግግርና ድርድር የሚጎዳ አድርጌ አልወስደውም።

በሰላም ተምሳሌትነት ከሚወሰዱ 10 ገደማ እንስሳቶች አንዱ ጉጉት ነው። ጉጉት የሰላም ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። አስተዋይ ስለሆነ። ትዕግስተኛ ስለሆነ። ሰላማዊ ስለሆነ። ጉጉት እስከ 60 ዓመት ይኖራል። እድሜው የመርዘሙ ሚስጥር ከግጭት እና ካላስፈላጊ አደጋ እራሱን የመጠበቅ ልምምዱ ነው። እኛ እንደ አገር ለመጽናትና ለመቀጠል በተቻለ መጠን ትዕግስተኞች፣ አስተዋዮች እና ሰላም ፈላጊዎች መሆናችን ጠቃሚ ይሆናል። ይህ ማለት ግን ችግር የሉብንም ማለት ነው እንዴ? አይደለም። አንድ ሺ አንድ ችግር ነው ያለው። ከአዲስ አበባ እንኳን ተመርጠው ከአዲስ አበባ ጋር ለመነጋገር ችግር አለ። ከጌዲዮ እንኳን ተመርጠው ከጌዲዮ ለመነጋገር ችግር አለ። የችግር ብዛት ያለበት አገር ነው ይሄ። ነገር ግን መነጋገር መደማመጥ፣ መልሶ መመርመር፣ መጨረስ ከጦርነቱ ውጭ ይቻላል። መነጋገር ስንል መቀመጥና ለውይይት ዝግጁ መሆን የሚያመላክት ቢሆንም ግን መደማመጥ ከሌለበት መነጋገር ብቻውን ውጤት አያመጣም። ከውስጥ መደማመጥ አንደኛው የሌላኛውን ፔይን (pain/ ሕመም) ማድመጥ ሲጀምር፤ ወደ ኋላ ተመልሶ ተዋግተን ምን አገኘን? ምን ትርፍ መጣ? ከግጭት ምን እናገኛለን ብሎ ከመረመረ ዊን ዊን (win win) በሆነ አፕሮች (approach) ለመጨረስ ዝግጁ ከሆነ ግን ችግሮቻችን ይፈታሉ። በዚያ መንፈስ ነው መታየት ያለበት። ከድርድር በኋላ ብዙ ጊዜ በመተማመን እጦት እና ቃል የገባነውን ባለመፈጸም ምክንያት ድርድሮች ይበላሻሉ። በዓለም ላይ 154 ድርድሮች የከሸፉት ከተስማሙ በኋላ ቃላቸውን መጠበቅ ባልቻሉ ወገኖች ነው። ጥናት ነው ይሄ። እኛ አንድ እርምጃ ሄደናል። ተወያይተናል፣ ተስማምተናል፣ ፈርመናል።

ቀጥሎ የሚጠበቅብን የገባነውን ቃል በታማኝነት በመፈጸም ሰላሙን ዘላቂ ማድረግ ነው። ይህ ፈታና አልቦ አይደለም፤ ችግር አልቦ አይደለም። የዓለም ልምምድም የሚያሳየው እንደዚያ አይደለም። ያ ችግር እንዳያጋጥም ግን አበክረን መሥራት ይኖርብናል።

አንድ ወጣት ጠቢብ ሰው ጋር ሄዶ ከአዕምሮዬና ከአካሌ ይበልጥ የሚያድገው የትኛው ነው? ብሎ ቢጠይቀው ይበልጥ የመገብከው ነው አለው ይባላል። አዕምሮን ከመገብክ አዕምሮ ያድጋል፤ አካልን ከመገብክ ደግሞ እንዲሁ አካል ያድጋል ብሏል። ይበልጥ የመገብነው ነገር ስለሚሆን ሰላምን አብዝተን ብንመግብ ሰላማችንን መጨበጥ እንችላለን። ሁል ጊዜ ግጭትና ጦርነት ደግሞ ካልን ተመልሶ እርሱ ሊመጣ ይችላልና እንደአገር እንደ ህዝብ ምንም እንኳን ጦርነት ፈላጊ ሰዎች የሉም ባይባልም ብዙዎቻችን ብናደርግ መልካም የሚሆነው ለሰላም መትጋት፤ ለሰላም መሥራት፤ በምንችለው አቅም ልክ ሰላም እንዲረጋገጥ መጣር፤ ቢሆን መልካም ይሆናል።

ድርድሩን በሚመለከት ከአሸባሪ ጋር ተደራድራችኋል ለተባለው ከዚህ ቀደም በተለያየ መድረክ ሲነሳ እሰማለሁ። የተከበረው ምክር ቤት ያወጣችሁት አዋጅ ከአሸባሪ ጋር አትደራደር አይልም። አሸባሪን አታሰልጥን፣ አታስጣጥቅ ፤ አትደግፍ ነው የሚለው። እኛ ህጉን ተከትለን አላስታጠቅንም፤ አልደገፍንም፤ አላሰለጠንም። ሕጉ ግን

# ፖለቲካና ወቅታዊ

አትደራደር ስለማይል።

ሁለተኛው የዓለም ልምድን ማየት ጠቃሚ ይሆናል። አሜሪካ ታሊባንን ለ20 ዓመት አሸባሪ ብላ ሰይማለች። ከታሊባን ጋር ግን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በስልክ እንኳን እንዳወሩ በይፋ ይናገራሉ፤ ይደራደራሉ። በንግግር ውስጥ የሚገኝ ትርፍ ካለ በሚል ማለት ነው። እና አሸባሪ ከተባለ ሃይል ጋር መነጋገር ሰላም እስካመጣ፤ ሽብር የማያስቀጥል እስከሆነ ድረስ መነጋገር ክፋ አይደለም። ነገር ግን እርሶም እንዳሉት በሰላም ሞክረን የታሰሩ ሰዎች የተባለው በጣም ጥሩ ሥራ ነው አሁንም ቀጥሉበት። እናንተ የምታደርጉት ጥረት ካለ ሰላም እንዲመጣ፤ ሰዎች እንዳይታሰሩ፤ መግባባት እንዲፈጠር፤ የሚደረግ ጥረት ካለ ቀጥሉበት። አንድ ጊዜ እንዲህ ነው ስለተባለ የሚቆም ነገር አይደለም፤ እርሱ ጥሩ ሥራ ይመስለኛል። ከዚህ ቀደም አቶ ክርስቲያን ስላነሱት ይህ ነገር ቢቀጥል ጥሩ ነው አሁንም። ግን ከቲፒኤል ኤፍ ጋር ተደራድራችሁ ጋዜጠኛ ይታሠራል፤ ላሉት ጋዜጠኛ እኛን ስለሰደበ፣ እኛን ስለወቀሰ፣ አይታሰርም። ያው እርሶም እንደሚያውቁት። የተለያየ ወንጀል ይኖራል የሚጠየቁበት፤ እነርሱም ቢሆኑ ጸባያቸውን አርመው፣ ጸባያቸውን አርቀው፣ ተስተካክለው ከወንጀል ነጻ ሆነው በቅርርብና በሰለጠነ መንገድ ብንሠራ መጥፎ አይደለም። እነርሱን በማሰር የሚገኝ ጥቅም የለም። እና ያንን የምታደርጉትን መልካም ሙከራ እንደፓርቲም እንደግልም ብታጠናክሩት ጥሩ ነው። መፍትሔም ያመጣል ብየ ነው የማስበው። እንደተባለው ሳይሆን በንግግር ውስጥ ኪሳራ የለም። አንዳንዴ ላይመች ይችላል ገፍታችሁ ያን ነገር ፊር እንዲይዝ ብትደግፉ ሃላፊነታችሁም ነው፤ ለአገር ጠቃሚም ይመስለኛል። በመጥፎ አላየውም ቢቀጥል ባይነኝ እርሱ።

ከወልቃይት ጋር በተያያዘ ላነሱት ጥያቄ ብዙ አነባለሁ፤ ብዙም እሰማለሁ። ወልቃይትን በሚመለከት የሚነገሩ ሽረባዎች፣ ሴራዎች /ኮንስፓይረሲ/ ብዙ እሰማለሁ። የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ሽረባዎች ውስጥ እጁ የለበትም። የወልቃይት ህዝብ እንዲገነዘብ የምንፈልገው የሚወራው፣ የሚናፈሰው፣ አሉባልታ ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት እጁ የለበትም። እኛ ደቡብ አፍሪካ የሄድነው ወልቃይት ወደ አማራ ይሁን ወደ ትግራይ ይሁን የሚለውን ለመወሰን አይደለም። የፒሪቶሪያው ሳሚትም ይህን ለመወሰን ስልጣን የለውም። ምን አገባውና ነው የኢትዮጵያን መሬት እዚያ ይሂድ እዚህ ይሂድ የሚለው። እኛ እዚያ የሄድነው እንዴት ሰላም አምጥተን በንግግር ችግሮቻችንን እንፍታ ለማለት ነው። ለምን ወልቃይት እዚያ ውስጥ ተስቦ እንደሚገባ አላውቅም። ወልቃይት ላይ ብቻ እኮ አይደለም ሰሜን ሸዋ ላይ ኦሮሚያና አማራ ጥያቄ አላቸው። እርሱም ደቡብ አፍሪካ ይሂድ? ሲዳማና ወላይታ ብላታ ላይ ጥያቄ አላቸው እርሱ ደቡብ አፍሪካ ይሂድ? እኛ ስራ የለንም? ልምምድ የለንም? ቦታው አይደለም። የተስማማነው በኢትዮጵያ ሕግና ሥርዓት ይፈጸም ነው። ከህገ መንግሥት በፊት ነው የተወሰደው፤ በጉልበት ነው የተወሰደው፤ ላሉት የእኔ ፍላጎት ያ ስህተት እንዳይደገም ነው። ዛሬ እኔ በጉልበት፤ ነገ ታገሰ በጉልበት ከሆነ ዘላቂ ሰላም አያመጣም። ወልቃይት ብንፈልግም ባንፈልግም የተወላገደ አማርኛ የተወላገደ ትግረኛ የሚናገር የሁለቱ ህዝቦች ድልድይ የሆነ ሕዝብ ነው።

ሁለቱንም ቋንቋ የሚናገር የተጋባ የተዋለደ ህዝብ ነው። ወልቃይቴነቱን ነው እንጂ አትንኩብኝ ያለው ከእንግዲህ በኋላ ትግራይ ከሚባል ጋር አልገናኝም አልነጋገርም አላለም፤ አይችልም ቢልም። ይሄን በህግና ሥርዓት ብንፈጽም ለወልቃይት ይጠቅማል ለአማራ ይጠቅማል፣ ለትግራይ ይጠቅማል። የሚጎዳው ነገር የለም፤ በህግና ሥርዓት ብንፈጽም የሚለውን ነገር ከብዙ ተንኮል ጋር ማያያዝም አስፈላጊ አይደለም። እርስዎ እንዳሉት ነው፤ እዚያ አካባቢ ረዘም ላለ ጊዜ ጥያቄ ነበር ለዚያ ብለን ነው ኮሚሽን ያቋቋምነው ከዚህ በፊት ገልጫለሁ፤ አሁን ያኔም የነበረን አቋም በህግ አግባብ በውይይት በምክክር ይፈታ የሚል ነው። ይሄ ማንንም ይጎዳል ብየ አልገምትም ውጤቱን በጋራ እናያለን ዋናው ፍላጎት ግን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ንግግር ያስፈልጋል።

እርስዎም እንደሚያውቁት ግን የተሰጣቸውን ሥራ በትክክል የማይሰሩ ሰዎች የፌዴራል መንግሥት እያሉ ብዙ ሸረባ እንደሚሰሩ እናውቃለን። ሂደቱን ላለማበላሸት ነው ዝም ያልነው። ሂደቱ መስመር ከያዘ በኋላ ለህዝብ ግልጽ እናደርጋለን። ሥራውን መሥራት አለበት፤ እያንዳንዱ ዞን እያንዳንዱ ወረዳ ፌዴራል ላይ ተንጠልጥሎ ሳይሆን ሥራውን ነው መሥራት ያለበት መሬት ላይ። ያን ካደረገ ሌላው ጉዳይ ዕዳው ገብስ ነው። ብዙ የሚያስቸግር አይደለም።

ሁለተኛ፤ ሁላችሁም የትግራይ ሕዝብ ሕዝባችን ነው፣ የትግራይ ሕዝብና ሕወሓት አንድ አይደለም ስንል ኖረናል። በየሚዲያውና በየአደባባዩ ፤ ሕዝባችን ነው በታሪክ በእምነት ብለናል። አሁን የትግራይ ህዝብ ከፍላጎቱ ውጭ፣ ከእሳቤው ውጭ ችግር ላይ ሲወድቅ ፣ሲራብ፣ ሲደክም እኛ ካልደረስንለት ማን ይደርስለታል። እኛ ካላገዝነው ማን ያግዘዋል! ተጎዳ እኮ። ተቸገረ እኮ፤ የሚታይ ነገር ነው። ግዴላችሁም ስናሸንፍ ግራውንድ መሆን ጥሩ ነው።



ህዝባችን ከሚቸገር በደግነት ብናግዝና ሕይወት ብናተርፍ ምንም ጥፋት የለውም።

ከዚህ ቀደም እኛ ሕወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ አይደለም ስንል ተሳስታችኋል አንድ ነው አሉ፤ አሁን ደግሞ ውይይት ሲኬድ ሕወሓት አልተወያየም እንትና አልተወያየም አሉ። ትክክለኛው የአሁኑ ሀሳብ ነው፤ ሕወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ አይደለም። ብልጽግና እና ኢትዮጵያ አንድ አይደለም፤ ብልጽግናን የሚደግፉ ኢትዮጵያውያን አሉ የሚቃወሙ አሉ። አብንን የሚደግፉ አማሮች አሉ አብንን የሚቃወሙ አማሮች አሉ። ኢዜማንም እንደዚሁ፤ አንድ ሕዝብ በጅምላው የኔ ብቻ ነው ማለት አይቻልም።

የትግራይ ህዝብ ግን ሰላም ፈላጊነቱን ወታደሮቻችን ባሉበት ቦታ ሁሉ ተረጋግጧል፤ እንደሰማችሁት ዛሬ ወታደር ነፍሰጡር ያዋልዳል፤ የአርሶ አደር ማሳ ያርሳል። ኮቾሮና ውሃ ይሰጣል፤ ይሄንን ወታደር ነው ያጠቃነው ብሎ የትግራይ ሕዝብም ይናገራል። ይሄ ነው መቀጠል ያለበት። ይሄ መልካም ነገር አይበለሻሽም ወይ?

ስለነገ ማንም ሰው ጋራንቲ ሊሰጥ አይችልም። እኛ ግን ዛሬም ነገም በተቻለ መጠን ለሰላም ታምነን መትጋት አለብን ብለን ነው መወሰን ያለብን እንጂ ምን እንደሚመጣ ከወዲሁ መናገር ያስቸግራል። እና ድርድሩ በጣም ጥሩ ነገር ነው፤ ስምምነቱ በጣም ጥሩ ነገር ነው። ፍሬያማ ውጤታማ እንድሆን መደገፍ ያስፈልጋል። ሌላውንስ? ተወያይተን፣ ተደጋግፈን፣ ተደማምጠን ፊር እናስይዘዋለን የሚል ዘላቂ ሰላም በሚያመጣ አግባብ ብናይ መልካም ይመስለኛል።

ትግራይ ገብተን ያየነው ነገር ህዝቡ በጣም ሰላም እንደሚፈልግ ውሃ እንደሚፈልግ መብራት እንደሚፈልግ ምግብ እንደሚፈልግ፣ ከአማራ ወንድሞቹ፣ ከአፋር ወንድሞቹ ከኦሮሞ ወንድሞቹ ምንም ችግር እንደሌለበት ነው ያየነው። ይሄን ብናስቀጥል መልካም የሚሆን ይመስለኛል፤ በበኩሌ ሰላም እንዲመጣ ነው የምፈልገው፤ በመምጣቱም ደስተኛ ነኝ፤ ሰላሙ እንዳይበላሽም በታማኝነት የምችለውን ሁሉ ጥረት ለማድረግ ነው የምፈልገው። እናንተም እንድትደግፉ የምፈልገው በዚያው መንፈስ ነው።

በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎች፤ ከዚያ በፊት ለጉብኝት ታሪካዊ ቦታ አለ ላሉኝ በእርስዎ ምርጫ ጣቢያ ምንም ችግር የለም፤ ሲመች በጎጃም ስንሄድ እናየዋለን፤ ብዙ ተመላልሻለሁ እንደሚያውቁት፤ አሁን ደስተኛ ነኝ ታሪካዊ ቦታ ውስጥ ከከሚሴ በስተቀር ያልረገጥኩት ዞን የለም። በኦሮሚያ ውስጥ ያልረገጥኩት የለም፤ በደቡብ ውስጥ ሸካ የተባለውን ጨምሮ አንድም ዞን ያልረገጥኩት የለም። እና አሁን ጥያቄው ከዞን ወደ ወረዳ ወርዷል፤ ጊዜው እየተገኘ ሲሄድ መጥፎ አይደለም፣ ብዙ የማናውቃቸው ነገሮች ስላሉ ብሄድ አተርፍ እንጂ እንደማላጎድል እርግጠኛ ነኝ፤ አንድ ቀን ያው ጊዜው ሲደርስ አብረን እንሄዳለን ማለት ነው። ጦር ላይ የተጎዱ አካባቢዎችን በሚመለከት ለጊዜው ሶስት ነገሮች ላይ አተኩረን ነው የሰራነው፤ አንደኛው መደገፍ ሰብዓዊ እርዳታ፣ እህል፣ ማሳ ላይ ያለ ማጭድ፣ የታመመ ማከም፣ ማብላት ማጠጣት፣ መርዳት፣ ይሄን አቅም በፈቀደ መጠን እያደረግን እንገኛለን ይጠናከራል። ሁለተኛው መገንባት ነው፣ ከመደገፍ በኋላ መገንባት ነው። አንደኛው መሰረተ ልማት ነው የሚገነባው፣ ለምሳሌ ሰቆጣ አካባቢ ታስታውሳላችሁ ባለፉት ስምንት ዘጠኝ ወራት መብራት አልነበረም፣ አሁን ሁለት ሶስት ሳምንት እፎይታ ስናገኝ ተገንብቷል። መብራት ሰቆጣም አለ አላማጣም አለ፣ ኮረምም አለ። ስልክም እንደዚሁ፣ ይሄ እየሰፋ በሄደ ቁጥር አቅም በፈቀደ መጠን እየተገነባ የሚሄድ ይሆናል። ትምህርትም፣ ጤናም መንገድም ሁሉም መሰረተ ልማት አቅም በፈቀደ መጠን እየገነባን የምንሄድ ይሆናል። በጣም ፈጣን ምላሽ ነው የሰጠነው፣ ሰላም ተብሎ ሳምንት እንኳን ሳይቆጠር በማግስቱ ቲም ተዋቅሮ ነው የእርዳታውም የመሰረተ ልማት ግንባታውም ስራ የተጀመረው። ሶስተኛው መመለስ ነው። የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ቀያቸው መመለስ፣ ትግራይ ሽሬ አካባቢ ብቻ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች መከላከያ ወደ አዲአቦ ወደ ቦታቸው መልሳቸዋል። ከሽራሮ፣ ከአዲ አገራይ፣ ከአዲአለዋ፣ ከአዲ ነብሪ ተፈናቅለው ወደ ሽሬ የሄዱ ሰዎች ወደ ቤታቸው የመመለስ ስራ እየተሰራ ነው፤ ወደ ፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ወልቃይትን በሚመለከት እንዳላልፍ ሁለት ነገሮች አሉ፣ ከአማራ ወገን ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ብዙ ወልቃይቴዎች ሲፈናቀሉ ሲሰደዱ ኖረዋል፣ ኢን ዜር አብሰንስ ሪፈረንደም ይካሄድ ቢባል የተመናመነ ሕዝብ ነውና እንጎዳለን። በትግራይ በኩል አሁን በተፈጠረው ግጭት ብዙ ሰው ወጥቷል፣ ስለወጣ አሁን ባለው ቢወሰን አማራ ክልል አድቫንቴጅ ይወስዳል የሚሉ ስሞታዎች ይሰማሉ፣ ወልቃይቴ ወልቃይቴ ነው ይታወቃል። ከአድዋም ሄደ ከደብረማርቆስም የሄደ ሰው ሊሆን ይችላል፣ ግን ወልቃይቴ እንደሆነ ይታወቃል፣ አትላንታም ይኑር፣ አውስትራሊያም ይኑር፣ ጅማም ይኑር ስለዛ ቦታ ሃሳብ እንዲሰጥ እድል ካልተሰጠው በቀር ዘላቂ ሰላም አያመጣም። ጉዳዩ ወደዛ ስለሄደ ወደዚህ ስለመጣ ሳይሆን ያ ሕዝብ የራሱን ፌት እንዲወስን ዲሞክራሲያዊ እድል እንዲያገኝ ማድረግ ከቻልን ብቻ ነው መፍትሄ የሚመጣው። እና እነዚያን ችግሮች በሚቀርፍ መንገድ እንደሚሰራ ተስፋ አደርጋለሁ። ጊዜ የወሰድነው ጊዜ የጠበቅነው ለዚያ ነውና ብዙ ስጋት ባይኖር በተረጋጋ መንፈስ ቢሰራ ዘላቂ ነገር ያመጣል ቢባል ጥሩ ነው። አለበለዚያ ግን ከሕገመንግስት በፊት ቲፒ እል እፍ በግድ ስለወሰደ አሁን እኛ ደግሞ በግድ ወስደን እዚያ ዘመን በሙሉ ወታደር ልናቆም አንችልም። በስምምነት ካልሆነ በወታደር ነው የሚሆነው፣ በወታደር ከሆነ ዘላቂ አይሆንም ጊዜ ይፈታዋል። አሁን ያለን ሰዎች ስናረጅ ስንደክም ልክ አሁን እንደተፈጠረው ይፈጠራል፣ ያ አካባቢ ሊለማ ስለሚችል ሰላማዊ በሆነ መንገድ ወደ ልማት እንዲገባ ቢደረግ ለሁሉም ጠቃሚ ይመስለኛል። እዚሁ አካባቢ ያሉ ተንኮሎች ኮንስፓይሬሲስ ቢቀሩ ጥሩ ነው። ብዙ የሚባለው ብዙ አይፈይዱም፣ መሬት ላይ ያለው ግን ስራውን ቢሰራ መልካም ይሆናል።

ሸኔን በሚመለከት በመጀመሪያ በሽብር የሚገኝ ነፃነት፣ የሚገኝ ዲሞክራሲ፣ የሚገኝ ክብር የለም፣ ሽብር ሽብር ነው። በሽብር መንገድ ዘላቂ ጥቅም ማምጣት አይቻልም፣ ሸኔ ግን እንኳን ለእኛ ለሚጋልቡትም ችግር ሆናል። የማይጨበጥ የማይዳሰስ፣ ፍላጎቱ የማይታወቅ፣ ኮማንድ እንድ ኮንትሮል ስርዓት የሌለው፣ የሚልኩት ሰዎችም ግራ ገብቷቸዋል እንኳን እኛ፣ የሸዋ ሸኔና የወለጋ ሸኔ እያለ እኮ ነው ሲዋጋ የሚውለው፣ አንድ ኮማንድ አንድ ስርዓት በማይኖርበት ሰዓት ተነጋግሮ ችግርን ለመፍታት በእጅጉ አስቸጋሪ ነገር ይፈጥራል። ለኦሮሞ ቆምኩ ይላል፤ ኦሮሞን ያፈርሳል፤ ኦሮሚያን ያፈርሳል፣ በኦሮሚያ ውስጥ ልማት እንዳይካሄድ የልማት ቦታዎች፣ የልማት ስራዎችን ያደናቅፋል። በዚህ መንገድ የሚመጣ ነጻነትና ሰላም ያለ አይመስለኝም። ነገር ግን በእኛ በኩል አቋማችን ያው ነው። የተለየ ሁለት አይነት መርህ የለንም። ለሸኔም ለከበደም ለተሰማም አንድ ነው። ታጥቀህ በሀይል የሚገኝ ጥቅም የለም። በፖለቲካ በንግግር ብቻ ነው ፍላጎትን ማሳካት የሚቻለው። ህገ መንግስት ላይም መነጋገር እንችላለን፤ ክልል ላይም መነጋገር እንችላለን። ስርአታችን ላይ መነጋገር እንችላለን። በንግግር ብቻ መሆን አለበት በሀይል መሆን የለበትም የሚል ነው የእኛ አቋም። ትናንትም ዛሬም ወደፊትም። ለሰላም በራችን ሁሌም ክፍት ነው። ለንግግር በራችን ሁሌም ክፍት ነው። ነገር ግን ሸኔ አካባቢ ያለው ችግር ሻርክ የባህሩን ከባቢ፤ እሱ ያለበትን የባህር ጫፍ ሲያናውጥ ባህሩን በሙሉ ያናወጠ ይመስለዋል። በዚያ አካባቢ ደም ያሉ አሳዎች ባህር ሳይሆን አለም ተናወጠች ይላሉ። እንደዚህ አይነት ቅዠት ጥቅም የለውም። ንጹሀን በመግደል መኪና በማቃጠል የሚገኝ ጥቅምም ትርፍም የለም። በመዝረፍ የሚገኝ ጥቅምም ትርፍም የለውም። ሰከን ባለ መንገድ ማየት ጠቃሚ ይሆናል። እና መንግስት ሰላም ማስከበር ግዴታው ነው ሰው በሀይል ከመጣበት። ከክላሽ ባሻገር ለመወያየት ዝግጁ ከሆነ ግን በራችን ሁሌም ክፍት ነው። በንግግር በውይይት ሰው ህግ እስካከበረ ድረስ ችግር የሉብንም። ህግ ሳያከብር ግን ሰው እየገደሉ ንጹሀንን እየገደሉ አርሶ አደር እየገደሉ እንደ መብት ማየት ግን የሚፈቀድ አይደለም። ይሄን መንግስት ሰፊ ስራ እየሰራ ይገኛል። በተባለው ልክ ውጤቱ አመርቂ ባይሆንም ስራው ቀላል አልነበረም ፤ አሁንም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ አዲስ አበባን በሚመለከት አዲስ አበባ መግባት ችግር ነው፤ ተንቀሳቅሶ ሀብት መፍጠር ህገ መንግስታዊ መብት ነው የተባለው ትክክል ነው። ግን ባለፈው እንዳነሳሁላችሁ አዲስ አበባን ለማሸበር ለማናጋት መሀሉን ዳር እናድርግ የሚል ሰፋፊ እቅዶች ይዘጋጁ ነበር። ያን ለማስቀረት ብዙ ስራ ተሰርቷል። በዚህ ስራ ውስጥ የተጉላሉ ሰዎች ይኖራሉ። የተጉላላሁት ለአዲስ አበባ ህዝብ ሰላም ነው፤ ለሀገሬ ሰላም ነው ብሎ ማሰብ አለበት። ሰው ለሀገሩ ሰላምና ደህንነት ህይወቱን ከፍሎ፤ እግሩን ከፍሎ፤ አይኑን ከፍሎ እየተዋጋ በፍተሻ የሚፈጠርን መስተጓጎል ወይም በአንድ ቀን በሁለት ቀን ውስጥ የሚፈጠርን ድካም ከሕይወት መስዋእትነት አንጻር መታየት የለበትም። ዝም ካልን እንዳያችሁት ነው። የምንይዘው ቦንብ ነው፤ ጥይት ነው፤ ከገባ ሰው ነው የሚገለው። ይሄ በኦሮሚያና በአማራ በተደጋጋሚ ኮምፕሌይን ይደረጋል። እኛ መረጃ ስላለን ነው። ወጣቶች ተመልምለው አበል ተከፍሏቸው አዲስ አበባ ገብተው እንዲረብሹ በተደጋጋሚ ሙከራዎች ይደረጋሉ። ያን ለማስቀረት ነው ስራ የተሞከረው። በሸኔውም፤ በቲ ፒ ኤል ኤፉም በአዲስ አበባውም የተከበረው ምክር ቤት ቢያስብበት፤ ቢገነዘበው ብዬ የምጠይቀው ነገር የኢትዮጵያ የፖለቲካ ገበያ ችግር አለበት። የፖለቲካ ገበያው ተበለሻሽቷል። ስትመድብ ብቃት የሚባል መመዘኛ ማየት አስቸጋሪ ነው፤ ከየት ሰፈር ነው፤ መንገድ የት ሰፈር ነው ነው፤ ማንኛውም አገራዊ ፕሮጀክት ከሰፈር እንጂ ከሀገር አንጻር አይታይም። ፖለቲካል ማርኬቱ እየተበላሸ ባህል እየሆነ ሲሄድ ብልጽግና ተሸንፎ አዲስ ፓርቲ ከመጣም አደገኛ ባህል ነው ይሄ። ፖለቲካል ማርኬቶቻችንን ብንፈትሽ በጣም ጥሩ ይመስለኛል። አዲስ አበባ ተብሎ ፖለቲሳይዝ ይደረጋል፤ ሸኔ ተብሎ ፖለቲሳይዝ ይደረጋል፤ ወልቃይት ተብሎ ፖለቲሳይዝ ይደረጋል፤ በጋራ ስንት ድል አምጥተን፤ በጋራ ብንቆም ስንት ተአምር ልንሰራ የምንችል ሰዎች በአልባሌ ምክንያት እንፋረሳለን። ይሄ ደግሞ በስራ ሳይሆን በጩኋት ለውጥ ይመጣል ብለው የሚያስቡ ሰዎች የሚፈጥሩት ችግር ነው። በአንድ ወቅት አንድ ሳይንቲስት ነበር። ይሄ ሳይንቲስት ምርምር አደርጋለሁ ወፍ አምጡልኝ ይላል። እና ወፏን ከነነብሷ ይዞ ላብራቶሪ ይገባል። እና በጣም ይጮህባታል ብረሪ ብሎ ። ከጮኸባት በኋላ ይለቃታል። እዛው ቤት ውስጥ በረረች። መልሶ ይይዛትና ክንፎቿን ይገነጥላል። ክንፎቿን ከገነጠለ በኋላ ብረሪ ብሎ በጣም ይጮህባትና ይለቃታል። ወፏ መብረር ሲያቅታት ክንፏ ሲገነጠል መስማት አትችልም የሚል ድምዳሜ ደረሰ። በእርሱ ጩኸት እንደበረረች አስቦ ማለት ነው። ዝም ብለው ሚጮኹ አሉ፤ የሽግግር መንግሥት፣ የምናምን መንግሥት ምናምን እንደጮህክ ትቀራለህ እንጅ የአገር ክንፍ እየቆረጥክ፣ አገር በሁለት እግሯ ቆማ እንድትሄድ ሚያደርግ ነገር እያበላሸህ ቢሰጥህም ሥራ አትሠራበትም። ሰው መብረሪያ ክንፉን እየቆረጠ ሃገር አላደገችም አልተነሳችም ቢል ዋጋ የለውም። ቢያንስ ቢያንስ በናሽናል ኢንትረስት ላይ ቆሞ ክንፏን የማይቆርጥ፣ እግሯን የማይቆርጥ ሰው ሆኖ መራመዷ ይፍጠንና ይስከን

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለምጣኔ ሃብቱ ዕድገት ጉልህ ድርሻ ያለው ኢንቨስትመንትና ሰላም

ፍሬሕይወት አወቀ

ኢትዮጵያ ባላት የተፈጥሮ ሃብት፣ ምቹ የአየር ጸባይና በቂ የሰው ኃይል ምክንያት ለኢንቨስትመንት ተመራጭ መሆኗ ይታወቃል። የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሃብቱን መሳብ የሚችሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮቿ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ናቸው። መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ይበልጥ ለመሳብ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑም ለዚሁ ነው። ኢትዮጵያ በተለይም ካለፉት አራት የለውጥ ዓመታት ወዲህ ከአሁን በፊት ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ያልሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን ጭምር ክፍት በማድረግ የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረች እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።



በኢትዮጵያ ከሚገኙ የኢንቨስትመንት አማራጮች መካከል አንዱ የሆነው የጨርቃጨርቅ ዘርፍ

የውጭ ባለሀብቱም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚፈጠሩ የተለያዩ አስቸጋሪ ወቅቶች ጭምር መዋለ ንዋያቸውን በማፍሰስ ኢንቨስት ሲያደርጉ ይስተዋላል። ለዚህም መንግሥት ለባለሃብቶቹ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታን በመፍጠር ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። የኢትዮጵያ መንግሥት በኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚነሱ ጥያቄዎችን ከባለሀብቶች በማሰባሰብ እንዲሁም ጊዜ ሰጥቶ በማዳመጥ ምላሽ ለመስጠት ያለው ቁርጠኝነት ከፍ ያለ ስለመሆኑ ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ለኢንቨስትመንት አስፈላጊ ከሆኑ ምቹ ሁኔታዎች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው ሰላም እንደመሆኑ በአሁን ወቅት በአገሪቱ እየመጣ ያለው ሰላም ለኢንቨስትመንት ጥሩ አጋጣሚን የሚፈጥር እንደሆነ ብዙዎች ያነሳሉ። ኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት ዓመታት ከገባችበት ጦርነት ተላቃ ወደ ሰላማዊ ድርድርና ውይይት እየመጣች ነው። ይህ ጦርነት የማቆም ስምምነትና ድርድር በተለይም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚፈጥረው አጋጣሚ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

መንግሥት ከጦርነት የሚገኝ ኪሳራ ብቻ እንደሆነና ትርፍ የሌለው መሆኑን በማመን ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራ እንደሆነ ይታወቃል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በተካሄደው 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ስብሰባ ከምክር ቤት አባላት ለተነሱት ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ እና ማብራሪያ ከሰላም የምታተርፈው ኢትዮጵያ እንደሆነች ተናግረዋል። ከሰላም የሚጎዳ ኢትዮጵያዊ የለም ባይባልም፤ እንደ አገር ሲታይ ሰላም ትርፋማ እንደሆነ ተናግረው ሰላም የሚያስከፋቸው ኃይሎች የጦርነት ነጋዴዎች ናቸው ብለዋል። “ውሃ በወንፊት ዘግኖ ከአንድ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ መውሰድ እንደማይቻለው ሁሉ ሰላምና ብልጽግናን ለማስቀጠል ሲባል ጦርነት ማቆም በእጅጉ ያስፈልጋል” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለሰላማችንና ለብልጽግናችን ስንል ጦርነት ማቆምን ቀዳሚ ምርጫችን አድርገናልም ብለዋል።

በአሁን ወቅትም ቀዳሚ ምርጫ የሆነውን ሰላም ለማረጋገጥ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የነበረውን ጦርነት ገታ ማድረግ ተችሏል። ጦርነቱን ለማቆም በተደረሰው የሰላም ስምምነትም በርካታ ትርፎች የሚገኙ እንደሆነ ይታመናል። በተለይም የኢትዮጵያን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በማሳደግ በኩል ሰላም የሚኖረው አዎንታዊ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከሰሞኑ ባደረገው የምክክር መድረክ አመላክቷል። ኮሚሽኑ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሳተፉበት ሀገር አቀፍ የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ አካላት ጋራ በጎንደር ከተማ ባደረገው የምክክር መድረክ ላይ አሁን እየታየ ያለው የሰላም ሂደት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱን ለመሳብ ያለው ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው አስረድተዋል።

በምክክር መድረኩ የተገኙት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ተመስገን ጥላሁን እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈጠረው የሰላም ስምምነት በኢንቨስትመንት ዘርፍ የውጭ ባለሀብቶችን በብዛት ለመሳብ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር ነው። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ከምንም በላይ ሰላም የሚያሻው ጉዳይ እንደመሆኑ በአገሪቱ ሰላምን ማረጋገጥ የግድ ነው። በተለይም የውጭ ባለሀብቶች በአንድ አገር ኢንቨስት ለማድረግ ሲነሱ የመጀመሪያ ጥያቄያቸው የሚሆነው የሰላም ጉዳይ ነው። ሰላምና መረጋጋት ካለ ኢንቨስተሩን ማቆየት የሚያስችሉ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች ስለመኖራቸው አንስተዋል።

የሰላም ስምምነቱ ተስፋ ሰጪ ከመሆኑም በላይ በኮቪድና በጦርነቱ የተቀዛቀዘውን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት በቀጣይ ለማካካስ የሚያስችል አመቺ እድል እንደሚፈጥር ያነሱት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ የኢትዮጵያ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት ባለፈው አመት 3 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር እንደነበር ጠቁመዋል። ይህንንም ዘንድሮ ወደ 6 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል።

እቅዱ ተግቶ መሥራትን የሚጠይቅና የሰላም ስምምነቱንም እንደ አንድ ምቹ አጋጣሚ በመውሰድ በትኩረት ለመፈጸም የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን ያነሱት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ በኢትዮጵያ ለውጭ ባለሀብቶች ምቹ የሆኑ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዳሉ ነው የጠቀሱት። በአገሪቱ ከሚገኙ የኢንቨስትመንት አማራጮች መካከልም ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ማዕድን፣ ቱሪዝምና የአይሲቲ ዘርፍ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ተናግረዋል።

በምክክር መድረኩ የተገኙት የአማራ ክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ እድሪስ አብዲ በበኩላቸው፤ ክልሉ በችግሮች ውስጥ ቢሆንም የክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት አልተቋረጠም በማለት ያለውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አንስተዋል። በክልሉ በዘንድሮ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 131 ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ አንድ ሺህ 180 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠቱን ተናግረዋል።

በአሁን ወቅትም በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት በቀጣይም ለክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰት የጎላ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አንስተው፤ በተለይም ክልሉ በጦርነት የቆየ እንደመሆኑ የተጀመረው የሰላም ውይይት ለዘር መነቃቃት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል ነው ያሉት።

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ጉደታ አበበ በበኩላቸው የሰላም ስምምነቱ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ያለ ስጋት እንዲሰማሩ እድል የሚፈጥር እንደሆነ በማስረዳት ለኢንቨስትመንት ቀዳሚ ጉዳይ ሰላም ነው ብለዋል። በክልሉ በበጀት አመቱ 400 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያላቸውን ባለሀብቶች ለማስተናገድ እቅድ መያዙን ጠቁመው፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 42 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ከአንድ ሺ 700 በላይ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ማስተናገድ እንደተቻለ ነው ያስረዱት። ክልሎቹ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማሳለጥ በሚያስችሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድረግ አቅጣጫ ማስቀመጥ ችለዋል።

ኢትዮጵያ ባሏት የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚሳቡ በርካታ የውጭ ባለሃብቶች ስለመኖራቸው ያነሱት የጊዜ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ሥራ አስኪያጅና ባለቤት ወይዘሮ ጊዜሽወርቅ ተሰማ ናቸው። እንደሳቸው ገለጻ፤ ማንኛውም ሰው አገር በጦርነት ውስጥ ስትሆን የሚሰማው ጭንቀት እንዳለ ሁሉ የቢዝነስ ሰዎችም ሰላም ከሌለ የበዛ ጭንቀት የሚገጥማቸው መሆኑን አንስተዋል። በተለይም የውጭ ባለሃብቶች ከፍተኛ መጠን ያለውን መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ ኢንቨስት የሚደርጉ እንደመሆናቸው የሰላም ጉዳይ በእጅጉ የሚያስጨንቃቸው ነው በማለት የአገር ሰላም ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ዋናው ቁልፍ እንደሆነ አስረድተዋል።

በቅርቡም በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የነበረውን ጦርነት ለማቆም ደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ የተደረገውን የሰላም ውይይት መነሻ በማድረግ በአገር ውስጥ ያሉ በርካታ የውጭ ኢንቨስተሮች ደስታቸውን እንደገለጹ አስታውሰዋል። በሥራ ባህሪያቸውና ባላቸው አገራዊ ተሳትፎ አማካኝነት ከተለያዩ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች ጋር በየጊዜው የሚገናኙት ወይዘሮ ጊዜሽወርቅ፤ አሁን እየታየ ያለው የሰላም ስምምነት ጅማሮ የውጭ ባለሃብቱን የበለጠ የሚያስደስት እንደሆነ ገልጸው፤ የተጀመረው የሰላም ስምምነት በትክክል መሬት ወርዶ ተግባራዊ መሆን ሲችል ደግሞ በተለይም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ይበልጥ የሚሰፋ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

በአገር ውስጥ ለሚገኙ የውጭ ኢንቨስተሮችም የተጀመረው የሰላም ሂደት መስመር እየያዘ እንደሆነ እያስረዳን ነው የሚሉት ወይዘሮ ጊዜሽወርቅ፤ ይህን የምናደርገው የገቡት እንዳይወጡ ነው። ከዚህ ባለፈ የተጀመረው የሰላም ስምምነት ዘላቂነቱ ከተረጋገጠ በአገር ውስጥ ካሉት የውጭ ኢንቨስተሮች በተጨማሪ ሰፊ የኢንቨስትመንት ፍሰት ሊኖር እንደሚችል ጠቅሰዋል። አያይዘውም ኢትዮጵያ ገና ብዙ ያልተነኩ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮች እንዳሉ ተናግረዋል።

ለምጣኔ ሃብት ወሳኝ የሆነው ኢንቨስትመንት በተለያየ ጊዜ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በሚፈጠር የሰላም መደፍረስና አለመረጋጋት ሲቀዛቀዝና ሲጎዳ ይስተዋላል። እንደሚታወቀው ሰላምና መረጋጋት ለኢንቨስትመንት በተለይም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና ለምጣኔ ሃብቱ ዕድገት ጉልህ ድርሻ ያለው ነው። ይሁንና የውጭ ባለሃብቶችን ወደ አገር ውስጥ ለመሳብ እንዲሁም በአገር ውስጥ ያሉትን ባለሃብቶች ለማቆየት የውስጥ ሰላምና የፖለቲካ መረጋጋትን ማስጠበቅ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል።

በተለያዩ ምክንያቶች መንገራገጭ የሚታይበት የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት በኢንቨስትመንቱ በይበልጥ የሚደገፍ ቢሆንም የሰላም ዕጦቱ ጋሬጣ ሆኖበት ቆይቷል። ይሁንና አሁን በአገሪቱ እየመጣ ባለው የሰላም ውይይት መነሻነት ዘርፉ ከገባበት ችግር ሊላቀቅ የግድ የሚለውና ለዚህም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ይታመናል።

በዋናነት የሚመለከተው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም በርካታ ሥራዎችን እየሠራ የሚገኝ ሲሆን በተለይም የውጭ ባለሃብቶችን በመሳብ በኩል ትርጉም ያለው ሥራ እየሠራ ይገኛል። ለአብነትም ከሰሞኑ ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት ካሳዩ የተለያዩ አገራት ከመጡ ባለሃብቶች ጋር የጋራ ስምምነት ማድረጉን ከኮሚሽኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ወደ አገር ውስጥ ከገቡት የውጭ አገር ባለሃብቶች መካከልም የባንግላዲሽ ባለሃብቶች የሚገኙበት ሲሆን፤ ባለሀብቶቹ በሶላር ሃይል፣ በሞባይል ባንኪንግ እንዲሁም በአይሲቲ ዘርፍ በኢትዮጵያ ኢንቬስት በማድረግ የሁለቱ አገራት ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት እንዲዳብር እየተሰራ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን ፕሮጀክቱንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ለማስገባት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ከኮሚሽኑ የተገኘው መረጃ አመላክቷል።

ላይ ይነጋገራል እንጅ እግር ቆርጦ ካልሮጥክ፣ ክንፍ ቆርጦ ካልበረርክ የሚባል ነገር ብዙ የሚያዋጣ አይደለም። እንደዚህ ዓይነት ፖለቲካዎች በስፋት አሉ ይህን ነገር እንዳያበላሽብን ጥንቃቄ ብናደርግ ጥሩ ይሆናል። ማደግ እንችላለን መሥራት እንችላለን ሕዝባችን ለሥራ በጣም ብርቱ ነው። ያ እድገትና ሥራ ግን ዘላቂ ነገር እንዳያመጣ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ማየት ጥሩ ይሆናል።

አመራር በሚመለከት የሚተባበሩ እንዴት ይታያል የተባለው ያው አይተባበሩም የሚተባበር አመራር የለም ብሎ ቃል መስጠት ያስቸግራል። ግን የተከበረው ምክር ቤት መገንዘብ ያለበት የኢትዮጵያ ፖለቲካል ማህበረሰብ እዚህ ምናስበው ሰፈር ውስጥ ብቻ አይደለም ኤጀንት ሆኖ የሚሠራው። አንድ የብልጸግና አመራር ለሸኔ ወይ ለቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ወይ ለምናምን ብቻ አይደለም። አንዴ የተሸጠ ከሆነ ራቅ ላሉት ወገኖችም ይሸጥላቸዋል። ሰፋ አድርጎ ማየት አስፈላጊ ነው፤ ለነማን ነው ይኸ ነገር የሚያጋጥመው የሚለውን እየገመገሙ መፍትሔ ማበጀት ያስፈልጋል፣ ይሠራልም።

ሌብነትን በሚመለከት እውነት ነው ፤ሌብነት በጣም አታካች ነገር ሆኗል። በተለይ የገጠመንን ሃገራዊ ፈተና የገጠመንን ሃገራዊ ችግር እንደ እድል የወሰዱ ሰዎች ቀይ መስመር ያልነውን ሌብነት ቀይ ምንጣፍ አድርገውታል። ቀይ ምንጣፍ አድርገው በነጻነት የሚንሸራሸሩበት ሰዎች እየተፈጠሩ ሄደዋል። አዲስ አበባ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ፋይል በእግሩ አይሄድም የሚለው ቋንቋ ኮመን ቋንቋ ነው። ፋይል በእጅ ብቻ ነው የሚሄደው በእግሩ አይሄድም። ሌብነት ልምምዱ ብቻ ሳይሆን እንደ መብት መወሰዱ አደገኛ ነገር ነው። ሌብነት የኢኮኖሚ ነቀዝ ነው፣ የእድገት ነቀርሳ ነው። ሌብነት ባለበት ማደግም መኖርም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ሌቦች መስረቃቸው ብቻ አይደለም። ከሰረቁ በኋላ ገንዘቡ ባንክ አይሄድም። ቢኮዝ ባንክ ከሄዱ መስረቃቸው ይታወቃል፤ ይቀመጣል። ከሰረቁ በኋላ በትክክለኛው ሆቴል ሄደው በትክክለኛው ዋጋ በትክክለኛ ክፍያ መብላት መጠጣት መልበስ ይቸገራሉ፤ ሁሉ ነገር ድብብቆሽ ስለሆነ። ድብብቆሽ ደግሞ ወደ ኢሌጋል ቢዝነስ ስለሚወስደው አንዴ የተሰረቀ ገንዘብ ወደህጋዊ ለመምጣት ይቸገራሉ። ለዚህ ነው አዲስ አበባ ውስጥ በቁጥራቸው ከፍ ያሉ ፎቆች ባለቤት አልባ የሆኑት፣ ፎቁ አለ ባለቤቱ አይታወቅም፣ ቤቱ አለ አይታወቅም ባለቤቱ። እና ንጽጽሩን እንተወው፣ ንጽጽሩ እንተወውና ከብልጽግና ምናምን ሚለውን ትተን እንደማህበረሰብ ግን ሌብነት እየተለማመድንነው በየሁሉም ተቋማት ውስጥ። ይሄን ነገር መፍትሄ ካላበጀን እድገታችን ይጎዳል ሚለውን ማሰብ ጠቃሚ ነው። ሳይሠሩ የሚበሉ ነበር ድሮ አሁን ሳይሠሩ የሚበሉ አይደለም የሚሠራ የሚበሉ፣ የሚሠራውን ሰው መርጠው ይበላሉ ሰው እንዳይሠራ። እነርሱ ተቀምጠው መጠቀማቸው ብቻ ሳይሆን እየሠራ የሚንቀሳቀስን ሰው በተለያየ መንገድ ጠላልፈው ይጥላሉ። ሥራ ይበላሉ ሠራተኛ ይበላሉ ሣይሠሩ ተቀምጠው መብላት ብቻ አይደለም አሁን ያለው። እሄ በስፋት በሁሉም መስክ እየታየ ያለ ጉዳይ ነው። ሌባ ከዚህ ቀደም እንዳልኩት ቤት ይሠራ ይሆናል እንጅ ሃገር አይኖረውም። በሌብነት ቤት እንጅ ሃገር አይገነባም።

ሀገር አልባ ቤት ደግሞ ዘላቂ አይሆንም። በጋራ እንደ ሀገር ማደግ የምንችልበት እድል እያለ በተናጠል ቤቴን ብቻ ልገንባ የሚል ሰው ችግር ያስከትላል። የሆነው ሆኖ በስራ አስፈጻሚ ተወያይተንበታል። በካቢኔ ተወያይተንበታል። ምን አልባት በሁለት በሶስት ቀን ውስጥ ለህዝብ ይፋ እናደርጋለን። ሀገራዊ ኮሚቴ አቋቁመን ጥናት እያጠናን እንገኛለን። የተከበረው ምክር ቤት፣ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለዚህ ዓላማ ብቻ የተዘጋጁ ስልኮች አሉ፣ ቢሮዎች አሉ፣ መረጃ ሰነድ በማቀበል ቢያንስ ባናጠፋ እንኳ ሌብነትን አንገት እንድናስደፋ በጋራ እንስራ። መጠየቅ ብቻ ሳይሆን በጋራ ቆመን ተረባርበን ትንሽ አንገት ለማስደፋት ጥረት እናድርግ። ያን ካደረግን ቀላል የማይባል ጥቅም እናገኝበታለን። አሁን ያለው ክሱ ብዙ ነው። እጅ የማይጠቆምበት ሰው የለም፤ በመረጃ፣ በማስረጃ እያስደገፍን ለህግ ካላቀረብን የፍትህ ስርዓቱ ቅድም እንዳላችሁት ነው። ሰውየው ገባ፣ ወጣ ነው። እና ዘላቂ ነገር እንድናመጣ አድርገን በጋራ በትብብር አብረን ብንሰራ ጥሩ ይሆናል።

የፍትህ ስርዓትን በሚመለከት ልክ እንደ ኢንፍሌሽን ትልቁ ስብራት የፍትህ ስርዓቱ ነው። በእርግጥ የፍትህ ስርዓቱም የሁላችንን ተሳትፎ ይጠይቃል። በተለይ የፓርላማውን ተሳትፎ ይጠይቃል። ፓርላማው ቀጥታ የሚመራባቸውን ተቋማት ጠንከር ያለ የሪፎርም ስራ መስራት ይጠበቅበታል። አስፈጻሚውም እንደዚሁ። በሌላውም ሴክተር ስራ ካልሰራን በስተቀረ የፍትህ ስብራቱ ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ ዘመናዊ የፍትህ ስርዓት ከመፈጠሩ በፊት ባህላዊ የፍትህ ልምምዶችና ልማዶች ነበሩን። አሁንም አሉን። በዛፍ ስር ሽምግልና መቀመጥ እና መወያየት ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ ነው። ልዩነቱ ፍትህ ጥፋተኛ ለይቶ ይቀጣል። ባህልዊ ፍትህ ደግሞ ጥፋተኛ ለይቶ ካሳ ካስከፈለ በኋላ ያስታርቃል። ያ በባህል የምናውቀው የበለጠ ውጤታማ ነው። ጉቦ የለውም ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛ ይለያል፣ ካሳ ያስከፍላል ከዚያ



ደግሞ ያስታርቃል። በደም የሚፈላለጉ ሰዎች ሳይቀሩ ያስታርቃል። የፍትህ ስርዓት ይቀጣል እንጂ አያስታርቅም። ያም ሆኖ በጣም ሰፊ የሆነ ችግር አለበት። ባለፈው ሌብነት በስፋት አለ ብየ አንስቼ አንዳንዶች ካለምንም ጭንቀትና ስጋት ነገርየውን ለመቃረን ሲፈልጉ ሰምቼለሁ። ዛሬ በደንብ ጠንከር አድርጌ መድገም እፈልጋለሁ። በፍትህ ስርዓት ውስጥ ዐቃቤ ህግ ሆኖ፣ ዳኛ ሆኖ፣ ፖሊስ ሆኖ፣ በገንዘብ አልሰራም፤ ቃለ መሃል ገብቼለሁ፤ ቃሌን ጠብቄለሁ፣ እምነት አለኝ የሚሉ ሰዎች አሉ። እነኝህ ሰዎች ግን በጓደኞቻቸው በቤተሰቦቻቸው ሞኞች ናቸው የሚሰደቡ። በእውነት የሚሰራ ሞኝ ነው፤ አልገባውም፤ ያልሰለጠነ ነው። ይሰደባል፣ ጓደኛ ይሰድበዋል፤ እነሱ አላመማቸውም በባለፈው ንግግር። ሌብነት አለ ሲባል ዝም ብሎ ሳይሆን በቴሌግራም ግሩፕ ከፍተው ጉቦ የሚቀበሉ ዳኞች አሉ። አርበኛ ለመሆን የሚቀላቅሏቸው ጨዋታዎች ደግሞ አሉ። እንትናን ፈታሁ እንትናን አሰሩ እያሉ ይናገራሉ። እንደዚህ አይነት ቀልድ ጥሩ አይደለም። የፍትህ ስርዓት ጊዜው አሁን ነው። እስከዛሬ በነበረው ጊዜ ውስጥ በነበረው ኢንተርቬንሽን አልቻልነውም። እንደምታውቁት በጀት እንኳ ሳይቀር ከአስፈጻሚ አውጥተን ወደ ፓርላማ ያስገባነው አሁን ነው። የፍትህ ስርዓቱ ብዙ ተደግፏል። መሻሻል ካለባቸው አሁን ነው ጊዜው። አሁን ከተበላሸ፤ መሰረት ከተናደ መቼም አይቃናም። ለዚህ እውነተኛ የሚሆኑቱ፣ ሀገር የሚወዱ፣ ቃላቸውን የሚያከብሩ ሰዎች ተባባሪ ሆነው ጠንካራ ሪፎርም መስራት ይኖርብናል። ምክር ቤቱ ጀምሯል። አጠናክሮ ለኢትዮጵያ ህዝብም ለሁላችንም እፎይታ ያመጣል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። በእኛ በኩል ያለውን እናጠናክራለን።

ሲቪል ሰርቪሱም ጋር ችግር አለ። በአንድ በኩል የመንግስት ሰራተኛ በቂ ደሞዝ አይከፈለውም እንደምታውቁት። በሌላ በኩል ለሚሰጠው አገልግሎት እንደ ግል ሰርቪስ ክፍያ መጠየቅ ልማድ እየሆነ መጥቷል። ቅድም ባልኩት ማዕቀፍ ውስጥ ተባብረን ከሰራን ብዙ መልክ እናስይዛለን ብየ አስባለሁ። ሲቪል ሰርቪሱ አንደኛው ማብቃት ነው። በማሰልጠን ማዘመን ነው ሁለተኛው፣ ሶስተኛው ደግሞ ማጥራት ነው። እያጠራን በመሄድ መፍትሄ ለማምጣት ጥረት ይደረጋል። በጥቅሉ ግን ብዙ የሚለፉ፣ ብዙ የሚሰሩ፣ ብዙ የሚደክሙ ሰዎች ያሉ ቢሆንም አሁንም ሌቦች፣ አጥፊዎች ስራ ጠሎች ስላሉ ብዙ ነገር እንደፈለግነው እየሄደ አይደለም እና በዚህ አቅም ማስኬድ እንደምንችል በየቀኑ መፈተሽና ማረቅ ያስፈልጋል። ቅድም አዲስ አበባ እንዳነሳሁት አዲስ አበባ ላይ የሪቨር ሳይድ ፕሮጀክቶች ያ ነው ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ላለው ነው ገንዘብ ያገኘነው። ከእንጦጦ ጫፍ እስከ ፒኮክ ድረስ ይሄ ሪቨር ሳይድ ፕሮጀክት ማለት በፌዝ 2 አሁን ሙሽሮች አካባቢ የተሰራው ስራ ያለበት ከእንጦጦ ጀምሮ እስከ ፒኮክ አላማ የነበረው እነዚህ ፓርኮች ናቸው። ተከፍሎባቸው ሰው ይገባል። ሰው ፍሬንድ ሺፕ ለመጠቀም ከሜክሲኮ ከመገናኛ ነድቶ ይመጣል። ይሄኛው ግን እያንዳንዱን ጎረቤት እያለፈ ነው የሚሄደው። ሰው ሁሉ በሰፈሩ ወክ የሚያደርግበት ፓርክ ንፁህ ውሃ የሚያይበት ሽታ የሚጠፋበትን እድል ይሰጣል። ሁለት አመት አጓተውት ፋይናንስ የሚያደርጉልን ሰዎች ገንዘቡ እየጨመረ ስለሄደ ከእንጦጦ ፒኮክ የነበረው አሁን ከናይጀሪያ ኢምባሲ ፍሬንድሺፕ ጋር አምስት ኪሎ ሜትር ብቻ ሆኗል። ይሄ እንዳይሰራ የሚያደናቅፈው ሃይል ልክ እንደ ጫካው ነው። ብዙ የሚተርተው ተረት አለው። 49 ቢሊየን 59 ቢሊየን ይላል ይተርታል። ስራ ያበላሻል። ሌብነት ብቻ ሳይሆን ስራ መግደል የተለማመዱ ሰዎች አሉ። ይሄ ደግሞ ልማታችን እንዳይፋጠን በጣም በጣም ጉዳት እያመጣ ስለሆነ መንቃትና መተባበር በጋራ መስራት ቢኖርብን መልካም ይሆናል።

ዲፕሎማሲውን በሚመለከት የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ መለያ ነፃነት፣ እኩልነት እና ፍትሃዊነት ነው። ይሄ ከመንግስት መንግስት ከዘመን ዘመን አይቀየርም። ለነፃነት ቀናይ ለእኩልነት ለፍትሃዊነት መርሃችን ነው። ሁለተኛው የአፍሪካ ችግሮች በአፍሪካ መፍትሄ ሊበጅላቸው ይችላል የሚል እምነት አፍሪካውያን በሙሉ አላቸው፤ እኛም የፀና እምነት አለን በዚህ ጉዳይ። ሶስተኛ በርካታ ችግሮች አሉ ግን በጋራ አሸናፊ የምንሆንበት (ዊን ዊን አፐሮች) ዊን ዊን ሶልሽን መፍጠር ያስፈልጋል። አንዱ አሸናፊ ሌላው ተሸናፊ ከሆነ አያዋጣም። የሚል መርህ አለን። በዚህ ምክንያት አንዳንዴ ከፍ አንዳንዴ ዝቅ ሲል የቆየ ነገር አለ። የሆነው ሆኖ የኛን ጎረቤቶች በሚመለከት ከኤርትራ፣ ከጅቡቲ፣ ከኬኒያ፣ ከሶማሌ፣ ከሳውዝ ሱዳን ከሱዳንም ጭምር ባለፉት ሶስት ወራት መልካም የሚባል ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ተደርገዋል። ውጤቱም ጥሩ ነው። ከሱዳን ጋር አንዳንድ የማያግባቡ ጉዳዮች ነበሩ አሁን ግን በጣም በተሻለ ደረጃ ነገሮች መስመር እየያዙ እየሄዱ ነው። ማጠናከር የሚያስፈልግ ኤሪያ አለ አጠናክረን ከሱዳን ወንድሞቻችን ጋር በጋራ ሰርተን ማደግ መለወጥ የምንችልበትን ነገር እናመቻቻለን። ባለፈው አንድ ወር ሁለት ወር አካባቢ በነበረው ግጭትም ይሁን በአለም አቀፍ ዲፕሎማቲክ ሁኔታዎች ሱዳን የኢትዮጵያ አጋር ሆና ነው የሰራችው። በመጨረሻው ውጊያ ሱዳን ምንም አይነት ድጋፍ አላደረገችም በጣም እናመሰግናታለን። ከዚያ በኋላ ለነበሩ ዲፕሎማቲክ ጫናዎችም ሙሉ ለሙሉ ኢትዮጵያን ደግፋ ቆማለች። ጎረቤቶቻችን አፍሪካውያን ወንድሞቻችን በድርድሩ በጣም እረድተውናል። የደቡብ አፍሪካ መንግስት አግዞናል ፤የኬኒያ መንግስት አግዞናል። ፕሬዚዳንት አባሳንጆ አግዞናል። ፕሬዚዳንት ኡሁሩ አግዞናል፤ የአሜሪካ መንግስት አግዞናል። የአውሮፓ መንግስታት አግዘውናል። ብዙዎች ወዳጆቻችን ይሄ ጉዳይ በሰላም እንዲፈታ ጥረት አድርገዋል። መካከለኛው ምስራቅ፣ ሩቅ ምስራቅ ያሉ አገራት ረድተውናል። ለሁሉም ለኢትዮጵያ ሰላምና ብልፅግና አስበው ላገዙን ሃይሎች ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን። በግልም እንደ አገርም ለረዱን አንዳንዶች ደውለው። አንዳንዶች ሰው ልከው። አንዳንዶች በአካል ተገኝተው ብዙ ምክር ብዙ ጉትጎታ አድርገዋል ሰላም እንዲመጣ። ለእነዚህ ሁሉ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን። ዲፕሎማሲያችን ግን ቅድም ባነሳሁት ሪፎርም፤ አሁንም ሰፋፊ ሪፎርም እየተሰራ ነው ያለው። ምናልባት ውጪ ጉዳይ አሁን የጀመራቸውን ስራዎች አጠናክሮ ከቀጠለ አስተማማኝ የሆነ ተቋም ይገነባል የሚል እምነት ነው ያለኝ። ዝርዝሩን ውጪ ጉዳይ ሪፖርት ሲያደርግ ልታደምጡት ትችላላችሁ አሁን ግን በርካታ ሰራዎች እየተሰሩ ውጤትም እየመጣ ነው።

ዲፕሎማሲ አሁን ባለበት ሁኔታ ዲጂታል ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዲፕሎማት መሆን አለበት። ሁሉም ሰው። ሰርቪስ የሚሰጥ ሰው የታክሲ ሹፌር፣ ቡና የሚያቀብል ሰው ለሀገሩ ዲፕሎማት ነው። ስለ አገሩ መልካም ነገር በመናገር፣ መልካም በመለጠፍ በሶሻል ሚዲያ ላይ ዲፕሎማት መሆን ይችላል። በምእራቡ አለም ኢትዮጵያውያን መኖር ከጀመርን 50 ዓመት አልፎናል። 60 እና 70 አመት ገደማ ነው። በምእራብ አለም ውስጥ ቋሚ ነዋሪ መሆን መኖር ከጀመርን። በምእራብ አለም ያሉ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራ አገራቸውን የሚወዱበት ልክ ለአገራቸው በሚጮሁበት ልክ አገራቸውን ይወዳሉ። አሁን ተጨማሪ ያለኝ ምክር ግን አገራቸውን መውደድና ወደዚህ መጮህ ብቻ በቂ አይደለም። ባሉበት አገር ፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ አለባቸው። ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶችና ሴኔተሮች በውጪው ዓለም መታየት አለባቸው። ልክ የሱማሌን እንደምናየው የተለያዩ አፍሪካ አገራት እንደምናየው ኢትዮጵያውያን እይታቸውን እዚህ ብቻ ሳይሆን እዛ ባሉበት አገር ፖለቲካ ውስጥ መግባት አለባቸው። ዜጎች ናቸው የተማሩ ናቸው ቢያንስ ልጆቻቸው በዛ አገር ፖለቲካ እንዲሳተፉ ቢያደርጉ አሁን ከሚያደርጉት ድጋፍ በላይ ማገዝ ይችላሉ። ሁለት ሴኔቴሪ ኢትዮጵያዊ ቢኖር አስቡ እዛ አገር ምን ማድረግ እንደምንችል ።ወደዛ አይነት እንዲቀየሩ እንዲያደርጉ መምከር እፈልጋለሁ።

ዩኒቨርሲቲዎች ወደ 50 ገደማ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች አሉ። የግሉ ጋ በጣም በርከት ይላል። ወደ 50 ሺ ገደማ ምሁራን አሉ። እነዚህ 50 ሺ ምሁራን በሳምንት አንዳንድ ገጽ ስለ አገራቸው ቢጽፉ በዲጅታል አውድ ውስጥ ምን ያክል ሥራ ሊሠራ እንደሚችል አስቡት። 50 ሺ ምሁር ቀላል አይደለም 50 ሺ ምሁር የተፈጠረው በኢትዮጵያ ሃብት ነው። ኢትዮጵያ አስተምራ ነው። ኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሲሰነዘር በአንድ ድምጽ መቆም ከቻልን ትልቅ ውጤት ልናመጣ እንችላለን እና ሁላችንም በዛው አግባብ መሥራት ብንችል ጠቃሚ ይሆናል። የአዲስ አበባ ታክሲ ማህበራት ከዚህ አንጻር እጅግ የሚያኮራ ሥራ እየሰሩ ነው። የታክሲ ማህበራቱ ከመንግሥት በጣም በርካታ የተደረገላቸው አይደሉም ብዙ ጥያቄዎች አሏቸው። ነገር ግን በዚህ ችግር ጊዜ መንግሥትን፣ ህዝብን፣ አገርንም መደገፍ አለብን ብለው ከፍተኛ ሥራ እየሠሩ ነው። እነሱን እናመሰግናለን። ሌሎቹም እነሱን እንዲመስሉ እናበረታታለን። የታክሲ ማህበራት ለሚያደርጉት ጥረትና ሥራ የኢትዮጵየ መንግሥት ትልቅ ክብርና አድናቆት እንዳለው በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ። ሌሎቻችንም ካደረግን ዲፕሎማሲው ይቃናል የሚል ዕምንት አለኝ።

የብሔራዊ ምክክርና በሚመለከት ምን ላይ ነው ያለው የሚለውን እኔ በቀጥታ ለመመለስ እቸገራለሁ። ነገር ግን ፓርላማው ጠርቶ ሪፖርት ሊሰማ ይችላል። ለእናንተ ስለሚታዘዙ ሙሉ ሪፖርት ማቅረብ እቸገራለሁ። ነገር ግን ምርጥ ዘር ስላለ ብቻ መሬቱ አብቃይ ካልሆነ ብንዘራም አይበቅልም። ሰዎቹ ደጋግ ሰዎች ስለሆኑ ሃሳባቸው ጥሩ ስለሆነ፤ ለኢትዮጵያ ቀናኢ ነገር ስለሚያስቡ ብቻ አይሳካላቸውም። የሚሳካላቸው ሁላችንም ካገዝናቸው ነው። ሁላችን በየአቅማችን ድጋፍ ካደረግን ብቻ ነው ብሔራዊ ምክከሩ ፍሬ የሚያፈራው። እኛ ጋር ያለው ችግር በትንሽ በትልቁ ነገር ሳይጀመር ጨዋታ ፈረሰ አባይ ደፈረሰ ምንል ከሆነ አይሆንም። ጨዋታ ፈረሰ አባይ ደፈረሰ ከማለታችን በፊት ጨዋታው እንዳይፈርስ ውሃውም እንዳይደፈርስ ማድረግ የሚገባንን ነገር ማድረጋችንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይሄ ለኢትዮጵያ በጣም ትልቅ ዕድል የሆነ ነገር ነው። ቢያንስ 70/80 በመቶ ችግሮቻችንን መፍታት ይችላል። ገብቶን ብንጠቀምበት ብናግዝ፣ ብንሳተፍ፣ ብንተባበር ብዙ መፍትሔ ስለሚያመጣ ሁላችንም በጋራ ሆነን በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ ይኖርብናል ብዬ አስባለሁ። ሰዎቹ አገራቸውን ለመደገፍ ፍላጎት አላቸው አነጋግረናቸዋል። በመንግሥት በኩል ከሆነ ጥያቄው ግን መንግሥት ሙሉ ፍላጎትና ድጋፍ አለው እንዲሳካ ይፈልጋል ይሄ ሃሳብ ።የኢትዮጵያ ጥያቄዎች በንግግር በውይይት ፈር እንዲይዙ ይፈልጋል። እዚህ ጋ ግንዛቤ መወሰድ ያለበት ነገር አንድ ሁኔታ ላይ ችግሩን ብቻ አይተው የሚሰሩ ሰዎችና ውጤቱን አስበው የሚሰሩ ሰዎች የተለያዩ ናቸው። ሳይንቲስቶች ወደ ስፔስ የሚወጣ መንኮራኩር ከሠሩ በኋላ መንኮራኩር የሚያክለውን ነገር ፈጥረው ከሠሩ በኃላ መጨረሻ ላይ በዜሮ ግራቪቲ ስፔስ ላይ ሆኖ እስኪቢርቶ አይጽፍም በዜሮ ግራቪቲ የሚጽፍ እስኪቢርቶ ካልፈጠርን በስተቀረ መንኮራኩሩ ላይ ወጥቶ ዳታ ለመያዝ እንቸገራለን ብለው ሁለት የተለያ አገራት ወይም ግሩፖች ይከፈላሉ። አንደኛው ግሩፕ አስር ዓመት 15 ሚሊዮን ብር አውጥቶ አስር ዓመት ተመራምሮ በዜሮ ግራቪቲ ስፔስ ላይ መጻፍ የሚችል ስኪሪብቶ ሠራ፤ አንደኛው ቡድን ግን እስኪቢርቶ እንደማይሰራ ሲያውቅ መፍትሔ ላይ አተኩሮ በእርሳስ ተካው ብሔራዊ ምክክር የሚገጥሙትን ችግሮች አይተን ሌላ ዓመታት የሚወስድ ምርምርና ጥናት ከምናደርግ መፍትሔ ተኮር ሆነን ካገዝናቸው የተሻለ ውጤት ልናመጣበት ጥያቄዎቻችን ምላሽ ሊያገኙበት ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ። እና ምክር ቤቱም ህዝባችንም በቀና ልብ ብንደግፋቸው ውጤት ስለሚገኝ ውጤቱም ከፍተኛ ስለሆነ በዚሁ አግባብ መፍትሔ ተኮር ሆነን በጋራ ብንሰራ መልካም ነው ብዬ አስባለሁ። በጥቅሉ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሪዚሊየንት መሆኑን ዓለም ተገንዝቧል እኛም ተገንዝበናል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ መናጡን በፈለገው ልክ እንዳይሮጥ እግሩ መያዙንም አይተናል። እግር የሚይዙ ጉዳዮች ፈተን በተባበረ መንፈስ በግሪን ሌጋሲ በሌማት ትሩፋት ላይ ብንሰራ ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት ማድረግ እንችላለን። ከልመና መገላገል እንችላለን። አምርተን ምንበላ አምርተን የምንሸጥ መሆን እንችላለን። ለዚህ በጋራ መቆም ያስፈልጋል። ሰላም የልማታችን መሰረት ነው። አቅማችን በፈቀደ መጠን ለሰላም በጋራ መስራት ይኖርብናል። ሰላም ካለ ቀጣዩ ነገር እየቀለለ ስለሚሄድ ሰላምና ልማት ሌብነት ካለ የፖለቲካል ማርኬት ፕሌሱ ስለሰፈር ብቻ የሚያስብ ከሆነ እንደ አገር ማደግ እንቸገራለን። በአስተሳሰብም በእጅ ልምምድም ያሉ ጥፋቶችን ደረጃ በደረጃ እያረቅን እያረምን ለመሄድ በጋራ መስራት ይኖርብናል። ሌብንት ቀንሶ ሰፈርተኝነት ቀንሶ ቡድንተኝነት ቀንሶ ተንኮል ኮንስፓይሬሲ ቀንሶ በትብብር መንፈስ መስራት ከቻልን ግን በስንዴ፣ በሩዝና በቡና ያመጣነውን መድገም በብዙ መንገድ መድገም እንችላለን ይሄን ለማድረግ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በምስራቅ አፍሪካ ያገኘውን ደረጃ አጠናክሮ እንዲቀጥል በአፍሪካ ደረጃም ባሰብነው ልክ ማደግ እንዲችል ከዓለም ጋር ባለው ሂደት ውስጥ ተዋህዶና ተግባብቶ ዕድገታችንን ማስቀጠል እንዲችል የበኩላችንን ሚና ማድረግ ይኖርብናል። መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን እነዚህን ጉዳዮች ለመስራትና ውጤት ለማምጣት ጥረት ያደርጋል። ስለነበረን ጊዜ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፤ ስለጥያቄያችሁም አመሰግናለሁ በሚቀጥለው እስከምንገናኝ ሰላም ሁኑ !

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ስነ ጽሑፍ

**ዋለልኝ አየለ**

> **ምሳሌያዊ አነጋገሮች ብዙ ሀሳብ ከማዝረክረክ በአጭሩ ግልጽ አድርገው የሚያስቀምጡ ናቸው። በውስጣቸው ቅኔን የያዙ ናቸው፤ ጣፋጭ ይዘት ያላቸው ናቸው፤ ሥዕላዊ ገላጭ ናቸው**

የቋንቋና ስነ ጽሑፍ ምሁራን በተሰበሰቡበት ሁሉ አንድ ተደጋግሞ የሚነሳ ቅሬታ አለ። ይሄውም የአገር ውስጥ ቋንቋ ትኩረት እንደተነፈገው ነው። ይሄ ጉዳይ ጥናትና ምርምር የሚጠይቅ አይደለም። እያንዳንዳችን በቀላሉ የምናስተውለው ችግር ነው። የ11ኛና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ልብ ማለት እንችላለን። 12ኛ ክፍል አማርኛም ሆነ ሌላ የአገር ውስጥ ቋንቋ ለብሄራዊ ፈተና አይሰጥም። ይህን ታሳቢ በማድረግ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ክፍል ውስጥ አይገቡም።

ይህ የሚሆነው በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ባልፈቱ ተማሪዎች ሊመስል ይችላል፤ ግን አይደለም። በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ናቸው ይህን የሚያደርጉት። ሌላ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያሉ አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ ተማሪዎች 11ኛና 12ኛ ክፍል ሲደርሱ በኦሮምኛን ክፍለ ጊዜ አይገቡም።

እነዚህ ተማሪዎች እንደ ምክንያት የሚያደርጉት አገር አቀፍ ፈተና ላይ የማይመጣ ነገር ለምን እናነባለን ነው። በመሰረቱ ግን ቋንቋ ለፈተና የሚነበብ አይደለም፤ ቋንቋ ለየትኛውም ትምህርት መግባቢያ የሚሆን የመጀመሪያው መሳሪያ ነው። አካባቢን ማወቅ የሚቻለው በራስ ቋንቋ ነው።

ወደ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ብንመለስ ችግሩ እንዳለ ነው። ከስርዓተ ትምህርቱ ጀምሮ ትኩረት የሚሰጠው ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው። የሒሳብና የእንግሊዝኛ ቋንቋ በሳምንቱ ሁሉም ቀናት የሚሰጥ ሲሆን የአገር ውስጥ ቋንቋ ግን ሁለት ወይም ሦስት ቀን ነው።

ይህ ደግሞ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ግድለሽ እንዲሆኑ አደረጋቸው። ለዚህም ነው አሁን አሁን ብዙ የታሪክና የባህል መዛባት እያጋጠመ ያለው። የራሳችን የሆኑ አባባሎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ እንቆቅልሾች እያሉን የውጭ አድናቂ የሆንን ነው። መገናኛ ብዙኃን ላይ እንኳን የምንሰማውና የምናነበው የውጭ አገራት አባባሎችን ነው።

ስለ ምሳሌያዊ አነጋገር እና ፈሊጣዊ አነጋገር ማብራሪያዎችን ለማወቅ ወደ በይነ መረቡ ዓለም ብንገባ አናገኝም፤ በአንጻሩ በእንግሊዝኛ Idiom ወይም Proverb ብለን ብንፈልግ ለማንበብ እስከሚያታክተን ድረስ እናገኛለን። ምንነታቸውንም በምሳሌ ያስረዳናል።

ወደ አገር ውስጥ ቋንቋ ስንመጣ ግን ይህ የለም። በዚህም ምክንያት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ላይ አሁን አሁን ያለትርጉማቸው መጠቀም እየታየ ነው። አንዳንዶቹንም ትርጉማቸውን ባለማወቅ «ስህተት ናቸውና ይውደቁ» የማለት ክርክር ላይ ሁሉ ደርሰናል። ነገር ግን የሚገቡበትን ዓውድ አለመረዳት እንጂ በስህተት የተነገረ ምሳሌያዊ አነጋገር የለም። ምሳሌያዊ አነጋገር ስሙ እንደሚያመለክተው አንድን ሀሳብ ሊመሳሰለው በሚችል ነገር መጠቀም ነው። ምሳሌያዊ አነጋገር ዓውድ አለው።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የስነ ጽሑፍና ፎክሎር መምህር ዶክተር ለማ ንጋቱ «ምሳሌያዊ አነጋገሮች የንግግር ማጣፈጫ ቅመሞች ናቸው» ሲሉ ሰምቻለሁ። የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ ስለተረትና ምሳሌዎች ሀሳብ ሲሰጥም ሰምቼ ነበር። እርሳቸው እንደሚሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ብዙ ሀሳብ ከማዝረክረክ በአጭሩ ግልጽ አድርገው የሚያስቀምጡ ናቸው። በውስጣቸው ቅኔን የያዙ ናቸው፤ ጣፋጭ ይዘት ያላቸው ናቸው፤ ሥዕላዊ ገላጭ ናቸው። ለምሳሌ «ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል» ይባላል። የችኮላ ሥራ ጥሩ እንዳልሆነና ቶሎ እንደሚበላሽ፤ ነገሮችን በጥንቃቄ መሥራት እንደሚያስፈልግ ብዙ ማብራሪያ ከማብዛት ይልቅ ይህ አባባል ውስጣችን የመግባት ኃይል አለው።

ምሳሌያዊ አነጋገር እንደ አስፈላጊነቱ በዓውድ የምንጠቀመው ነው። ይህንን ባለማወቅ ግን ልክ አይደሉም ተብለው የሚወገዙ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሁሉ አሉ፤ ግን ልክ ናቸው። እንደ ምሳሌም «ዝምታ ወርቅ ነው» የሚለውን ያነሳሉ። «ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል» የሚለው አባባል መናገርን ስለሚያበረታታ ይደገፋል፤ «ዝምታ ወርቅ ነው» የሚለው ደግሞ አለመናገርን ስለሚያበረታታ ይወገዛል። ግን አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜም አለ። ዝምታ ወርቅ የሚሆንበት ጊዜም አለ። አንዳንድ ጊዜ እኮ «ምነው ባልተናገርኩ፣ ምነው ባልተናገረ» የሚባልበት አጋጣሚ አለ። በማናውቀውና ባልተዘጋጀንበት ነገር ላይ ከመናገር ዝምታ የተሻለ ይሆናል። ይህ ብቻም ሳይሆን አግባብ ያልሆነን ነገር ከመናገርም ዝምታ የተሻለ ሊሆን ይችላል።

በምሳሌያዊ አነጋገር ውስጥ የትኛው አባባል ለየትኛው ጊዜና ቦታ ይሆናል የሚለውን መምረጥ እንጂ ሁሉም የሚገልጸው የራሱ የሆነ ሀሳብ አለ። አባቶች እነዚህን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያለምክንያት አይደለም የተናገሯቸው፤ በሆነ አጋጣሚ አስፈልጓቸው ነው።

በሌላ በኩል የተነገሩበት ዘመንም የወቅቱን ሁኔታ የሚገልጽ ነበር። ለምሳሌ በፊውዳሉ ሥርዓት «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» የተባለው በወቅቱ የነበረ ሹመኛ መብላት ስለነበረበት ነው። እዚህ አባባል ላይ ሌላም አከራካሪ ነገር ይኖራል።

«ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» ማለት አንድ ሹመኛ በኋላ ይቆጨዋልና በሥልጣን ላይ እያለ ይብላ ለማለት ብቻ አይደለም። ይልቁንም ከሙስና የጸዳ ልብ ከሌለው «ምነው በልቼ በነበረ ኖሮ» ብሎ ይጸጸታል ማለት ነው። ስለዚህ ይህ አባባል የሚገልጸው በሥልጣን ላይ እያሉ ሙስና መብላት የሚፈልጉትን ነው ማለት ነው። እንዲህ አይነት ሰዎች ከሥልጣን ወርደው እንኳን ይቆጫቸዋል ማለት ነው። ሥልጣን ላይ ሲቆዩም ዛሬ ነገ እያሉ ነው የቆዩት ማለት ነው። ድንገት ከሥልጣን ሲወርዱ ግን መጸጸት ይመጣል።

ዳሩ ግን በአጠቃቀማችን ይህን አባባል በግድ ሙስናን የሚያበረታታ ትርጉም ሰጥተነዋል። ምናልባትም አበው የተጠቀሙት ሲሾም ያልበላ ሰው በኋላ መጸጸቱን እንደ መጥፎ ነገር ቆጥረውት ይሆናል። መጸጸቱን እየፈረዱበት ይሆናል። ስለዚህ ይህ ምሳሌያዊ አነጋገር በሁለት ምክንያት መወገዝ የለበትም ማለት ነው። በትክክልም ሙስናን ለማበረታታት ከሆነ ይህ ያኔ በነበረው አገዛዝ የተባለ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ እውነትም ሲሾም ባለመብላቱ መጸጸቱን እየፈረዱበት ቢሆንስ?

ለቋንቋ ትምህርት ትኩረት አለመስጠቱ የምሳሌያዊ አነጋገሮች ትርጉም ከባድ እንዲመስልም አድርጎታል። ምሳሌያዊ አነጋገር የቅኔነትም ባህሪ አላቸው፤ ውስጠ ወይራ የሆነ ትርጉም ይይዛሉ። አንዳንድ ጊዜ ቃል በቃል ብቻ በመተርጎም መልዕክታቸው አልገባን ይላል። ወይም ግራ የሚያጋባ መልዕክት ይሆንብናል።

ለምሳሌ «ችግር ነው ጌትነት በቅቤ ያስበላል» ይባላል። ይህን አባባል የሰማ ሰው «በቅቤ መብላት ምኑ ነው ታዲያ ችግር? እንዲያውም ጥሩ ነው እንጂ» ይል ይሆናል። ነገሩ ግን ወዲህ ነው።

አንድ ሰው በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠው ክብር ይኖራል፤ ይህ ሁላችንም የምናውቀው ነው። እገሌ እኮ ጌታ ነው፣ ቤቱ ሙሉ ነው፣ ቤቱ ቢሄዱ የደላው ነው እየተባለ ጥሩ ስም ይሰጠዋል። ያ ሰውዬ ግን ሁሌም የተሟላለት ሊሆን አይችልም። የሚቸገርበት ጊዜም ይኖራል። ዳሩ ግን የቱንም ያህል ቢቸግረው ከቤቱ ቅቤ መጥፋት የለበትም። እንግዳ እንኳን ቢመጣ የመጣው ሰው በቅቤ ነው በልቶ መሄድ ያለበት። ስለዚህ ሰውዬው ቅቤ እየበላ ያለው ደልቶት ሳይሆን የስሙን ክብር ለማስጠበቅ ነው፤ ምናልባትም ሌላ ነገር ሊሰራ ያሰበበትን ገንዘብ ለዚህ ብቻ እያዋለው ይሆናል።

ለዚህ የሚቀራረብ ሌላ አባባል እንጥቀስ። «የሌለው በኮት ያርሳል» ይባላል። በአገራችን ነባራዊ ሁኔታ ኮት የክት ልብስ ነው። ለሰርግ ወይም በሌላ ከሰው ጋር በሚደባለቁበት ጊዜ የሚለበስ ነው። ለግብርና ሥራ የሚሆነው ሌላ ቀልጠፍ ያለና ለጭቃውም ለአቧራውም ምቹ የሆነ ልብስ ነው። እንዲህ አይነት ልብስ በየዓይነቱ የሚኖረው ግን ያለው ነው። ኮት ለብቻ የሥራ ልብስ ለብቻ ነው መሆን ያለበት። ይህን ማድረግ ያልቻለ ግን ከሰው ጋር ሲቀላቀል የሚለብሰው አንድ ኮት ብቻ ሊኖረው ይችላል። ይሄ ሰውዬ አማራጭ ሲያጣ ኮት ለብሶ እርሻ ሊሄድ ይችላል ማለት ነው።

ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ስንጠቀም በቀጥታ ለተባሉበት ሀሳብ ብቻ አይደለም፤ ለምሳሌ «የሌለው በኮት ያርሳል» የሚለውን በኮት ለሚያርስ ሰው ብቻ አይደለም የምንጠቀመው፤ ማመሳሰያ ነው። ለምሳሌ ምሳ ሳንቋጥር ወይም ቆሎ ነገር እንኳን ሳንይዝ መንገድ ሄድን እንበል። ያለንበት አካባቢ ትልልቅ ሆቴሎች ብቻ ያሉበት ቢሆንና ርሃብ ደግሞ ቢጠነክርብን ከኪሳችን ያለችዋን ጨርሰንም ቢሆን ዋጋው ውድ የሆነ ቤት እንበላለን ማለት ነው። ከትልቅ ሆቴል ስንወጣ ያየን ሰው «እንዴት ቢደላህ ነው» ብሎ ቢጠይቀን «የሌለው በኮት ያርሳል» ልንል እንችላለን። ለቅንጦት ብለን ሳይሆን አማራጭ አጥተን ነው ያደረግነው ማለት ነው።

ምሳሌያዊ አነጋገርን በቀጥታ ብቻ መተርጎም የተሳሳተ ነው። ለዚህም ነው አንዳንድ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ውግዘት እንዲደርስባቸው ያደረገው። ዶክተር ለማ «ሴት ከበዛ ጎመን ጠነዛ» የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር እንደ ምሳሌ አንስተው ነበር። «ሴት ከበዛ ጎመን ጠነዛ» የተባለው ለሴቶች ብቻ አይደለም። ወይም ጎመን በመከተፍና በቤት ውስጥ ሥራ ብቻ ለተወሰኑ ሴቶች አይደለም። በሽተኛ እየተጉላላ ሐኪሞች ተሰብስበው እያወሩ ከሆነ ይህን አባባል መጠቀም ይቻላል። ብዙ ወንዶች ሥራ ትተው ተሰብስበው ሲያወሩ ከታየ ይህን አባባል መጠቀም ይቻላል። «ሴት ከበዛ ጎመን ጠነዛ» የተባለው ሰዎች አንድ ላይ ከተሰባሰቡ ወሬ ብቻ እንጂ ሥራ እንደማይሰሩ ለመግለጽ ነው። ዋና ትርጉሙ ሴቶች ሥራ አይሰሩም አይደለም፤ ሰዎች ተሰብስበው ወሬ ብቻ ከሆነ ሥራው አይሰራም ለማለት ነው። አባባሉ የተቀረጸው ድሮ ሴቶች ብቻ የቤት ውስጥ ሥራ ይሰሩ በነበረበት ጊዜ ስለሆነ ነው።

ማንም ይሁን ማን ካልሰራ ሸንቆጥ ይደረጋል። ሴቶችም ቢሆን እኮ ካልሰሩ ሊነገራቸው ይገባል፤ በዚሁ መጠንም የአድናቆት ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሉ። «መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት፣ ሴት የላከው ሞት አይፈራም፣ በሴት የበከረ(የጀመረ) ከእግዜር ተማከረ፣ በሴትና በውሃ የማይርስ የለም» የሚሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚያሳዩት የሴትን መልካምነት፣ የሴትን አሸናፊነት፣ መጀመሪያ ሴት ልጅ የወለደ ሁሉ ነገር ጥሩ እንደሚሆንለት፣ የሴት ምክር ተሰሚነት እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው። ስለዚህ ሴቶችን ለመውቀስም ሆነ ለማመስገን እንደ አስፈላጊነቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሉን ማለት ነው። ምንም አይተቹ ማለት ደግሞ አይቻልም።

«ሴቶችን አሳንሰው የሚያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች» በሚል ጥናቶች ይሰራሉ፣ እንዲህ አይነቶች ብቻ ይሰበሰባሉ። መሆን ያለበት ግን እንዲህ አልነበረም፤ ለምን ሴቶችን የሚያደንቁት አልተሰበሰቡም? ስለዚህ የጥናቱ ዓላማ ለማውገዝ ብቻ ነው ማለት ነው? እንደ አጠቃላይ በምሳሌያዊ አነጋገሮች ላይ ለትውልድ መሆን ያለበት ጥናት ሲሰራ አይስተዋልም። የቋንቋ ሀብታችን እንደመሆኑ መጠበቅ አለበት። ቋንቋችን ሲጠናም ቀደም እንዲህ ይባል እንደነበር መታወቅ አለበት። መገናኛ ብዙኃን ደግሞ ይህን ማበረታታት አለባቸው።

የሚያሳዝነው ነገር ግን መገናኛ ብዙኃን እንኳን ይህን ሊያበረታቱ ጭራሽ የጥፋቱ አካል መሆናቸው ነው። አሁን መጽሔቶቹ ራሱ የሉም እንጂ ከዓመታት በፊት አንዳንድ መጽሔቶች ላይ «አራምባና ቆቦ» የሚል ዓምድ ሁሉ ነበር። በዚህ ዓምድ ላይ አባባሎች እየተበላሹ የሚቀርቡበት ነው። ለምሳሌ «ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ» የሚለውን አባባል «ላም አለኝ በሰማይ አውሮፕላን እንዳይገጭብኝ» ብለው ያስቀምጣሉ። ይህን ያነበበ ልጅ እንዴት የሚረዳው ይመስላችኋል? ጥያቄና መልስ ላይ ቢጠየቅ እኮ «... አውሮፕላን እንዳይገጭብኝ» ብሎ ነው የሚመልስ።

ብዙ የብሔርና የፖለቲካ መጻሕፍት እንደ አሸን ሲፈሉ በእንዲህ አይነት ጉዳይ ላይ ግን የተጻፉ ብዙም አያጋጥመንም። ቋንቋችን ጉዳያችን አይደለም ማለት ነው? የቋንቋችን መጥፋትና መበረዝ አያሳስበንም ማለት ነው?

ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በተመለከተ በአንዲት ደራሲ የተጻፈ አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው የማውቅ፤ የኔ አለማወቅ ነው እንዳልል ደግሞ ብዙ ሰዎችን ጠይቄ የጠቆመኝ አላገኘሁም።

ምሳሌያዊ አነጋገር «የድሮ ነው» ልንለው የሚገባ አይደለም። ዛሬም ልንጠቀመው ይገባል። ዛሬም እኮ በቋንቋ ነው እየተግባባን ያለነው። በቋንቋ እየተግባባን ደግሞ ምሳሌያዊ አነጋገር አንዱ የቋንቋ ውበት ነው። ስነ ጽሑፋዊ ለዛ ያለው ነው። ምሳሌያዊ አነጋገርም ይቀየር ይሻሻል የሚባል አይደለም። ለምሳሌ የምንግባባበት ቋንቋ የአማርኛ ቋንቋ ከሆነ ቋንቋውን ልንቀይረው ነው ወይስ እንዴት ሊሆን ነው? የአማርኛ ቋንቋ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ከቀየርን ምኑን በዚያ ቋንቋ ተግባባነው?

ምሳሌያዊ አነጋገር የተለያየ መጠሪያ አለው። ተረትና ምሳሌ እየተባለ ይጠራል፣ አባባል እየተባለ ይጠራል። በጽሑፍ ደረጃ ያለው ስሙ ግን «ምሳሌያዊ አነጋገር» የሚለው ነው። በእርግጥም ይህኛው ስም የተለመደ ነው። በዚያ ላይ ስያሜውም ምግባሩን የሚገልጽ ነው። ምክንያቱም ነገሮችን እያመሳሰልን የምንገልጽበት ስለሆነ ምሳሌያዊ አነጋገር የሚለው ትርጉም አለው።

ምሳሌያዊ አነጋገር በግጥም መልክ የሚባል አለ፣ በጥያቄና መልስ የሚባል አለ፣ በሐረግ መልክ አለ፣ በዓረፍተ ነገር መልክ አለ። «ሁለት ባላ ትክል፤ አንዱ ሲሰበር በአንዱ ተንጠልጠል» የግጥም ባህሪ ያለው ነው። «መስጠትን የማያውቅ መቀበልን ማን አስተማረው?» የሚባለው ደግሞ ለጥያቄያዊ ምሳሌ ይሆነናል። «ሲበሉ የላኩት» ሐረግ ሲሆን «ሲሮጥ የመጣ አህያን አጥብቀህ ጫነው» ዓረፍተ ነገር ነው።

እንዲህ የዳበረ እና የበለጸገ ቋንቋና ስነ ጽሑፍ እያለን መገናኛ ብዙኃኑ ግን ያን ያህልም ትኩረት አይሰጡትም። በማንነታችን እንኮራለን ስንል የራሳችን የሆኑ ነገሮችን በማወቅ ይሁን!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ትኩረት የሚሻው የስርዓተ ፆታ ጉዳይ

**አስናቀ ፀጋዬ**

የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አንፃር በየትኛውም ክፍለ ዓለም እየተሰራ ያለው ስራ በቂ ነው ማለት አይቻልም። ይህም ሆኖ ግን በርካታ ስራዎች በተለያዩ መንገዶች እየተሰሩ መሆኑ ደግሞ አይካድም። በኢትዮጵያም የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከማጉላት አንፃር በየዘርፉ በርካታ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑ ግልፅ ነው። ነገር ግን በተለይ ሴቶች ድምፃቸው እንዲሰማና እነርሱን የሚመለከቱ ዘገባዎች በተለያዩ መንገዶች እንዲቀርቡ እየተሰራ ያለው ስራ አሁንም በቂ እንዳልሆነ ይነገራል።

ጋዜጠኛና የሴት መገናኛ ብዙሃን ማህበር ነባር አባል ፀጋ ታሪኩ እንደምትናገረው በስርዓተ ፆታ እኩልነት ዙሪያ የመገናኛ ብዙሃን ምንም አይነት ሚና አልተጫወቱም ማለት አይቻልም። ነገር ግን ከብዛታቸው አንፃር የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲያረጋግጡ ከፍተኛ ሚና ይጠበቅባቸዋል። በተቻለ መጠን በሚሰሯቸውና በሚያስተላልፏቸው ፕሮግራሞች ውስጥ ለስርዓተ ፆታ በቂ ጊዜ በመመደብ በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በማህረሰቡ ውስጥ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶችን በመቅረፍ ብዙ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል።

አንዳንድ የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ያላቸውን አምድና የአየር ሰዓት ለስርዓተ ፆታ ጉዳይ በማመቻቸቱ በኩል ክፍተቶች ቢኖሩም ሌሎች በሚሰሯቸው ዘገባዎች ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ አካተው ሲሰሩ ይታያል ትላለች።

ከዚህ ውጭ በዜናዎች፣ በፕሮግራሞች፣ በአምዶችና በሚነሱ ወቅታዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ ሴቶች ሃሳብ እንዲኖራቸው ወይም የስርዓተ ፆታ ጉዳይ ተካታች እንዲሆን ምን እየሰሩ እንደሆነም ለማየት ተሞክሯል። በዚህም በአሁኑ ጊዜ ከስርአተ ፆታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተሻሉ አማራጮችና ስራዎች እንዳሉ ተመላክቷል።

ይሁንና አሁንም ድረስ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከማረጋገጥና በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚታዩ የተዛቡ አመለካከቶችን ከመቅረፍ አኳያ ብዙ ይቀራል። መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ባለቤቶች እንዲሁም ሃላፊዎች የስርዓተ ፆታ እኩልነት ጉዳይን ዋነኛ ትኩረታቸው አድርገው መስራትና አንዳንዴ ደግሞ በሚሰሯቸው ፕሮግራሞች፣ አምዶችና ዜናዎች ውስጥ የሴቶችን ጉዳይ አካታች አድርገው መስራት እንዳለባቸውን በዚህ ረገድስ ሚናቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ለመለየት ተሞክሯል።



ጋዜጠኛ ፀጋ ታሪኩ፤



አቶ ቃለወንጌል ምናለ፤

ፎቶ፦ በአስናቀ ፀጋዬ

ከዚህ በመነሳት ከመንግስት በኩል በፖሊሲ ደረጃ የስርዓተ ፆታ ስራ በመንግስት ተቋማት ውስጥ በመደበኛነት እንዲሰራበት መደረጉንና በመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ውስጥ ቢሮ ተቋቁሞለት እንደ አንድ የስራ ዘርፍ ሆኖ እየተሰራበት መሆኑን ነው ጋዜጠኛ ፀጋ የምትናገረው።

ነገር ግን አብዛኛዎቹ ተቋማት ራሱን የቻለ የስርዓተ ፆታ ጉዳይን የሚመለከት ዴስክ ወይም ቢሮ እንዲኖራቸው ስራ መስራት እንዳለበትም ነው የምትጠቁመው።

ከዚህ ባለፈ መንግስት በመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ውስጥ ያሉ ኤዲቶሪያል ፖሊሲዎች ከስርዓተ ፆታ መነፅር አንፃር ዝርዝር ይዘቶቻቸው ምን እንደሚመስሉ መልሶ መቃኘት፣ አዲስ የሚቋቋሙትም በዛ ደረጃ ይዘው እንዲመጡ ማድረግና ፍቃድ ከመስጠቱ በፊት በጉዳዩ ላይ ትኩረት መደረግ እንደለበትም ጋዜጠኛ ፀጋ ታመለክታለች።

ኃላፊ በመሾም ደረጃም የግልና የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ላይ የሚታዩ ችግሮች መኖራቸውን የምትናገረው ጋዜጠኛ ፀጋ፤ ተቋማቱ ሴት አመራሮች ቢበዙላቸው የስርአተ ፆታ ጉዳይ ይበልጥ ትኩረት ሊያገኝ እንደሚችልም ትጠቁማለች። በባለሙያዎችም በኩል ያለውን ክፍተት ስልጠናዎችን በማመቻቸት መቅረፍ ከመንግስት እንደሚጠበቅም ታሳስባለች።

አቶ ቃለወንጌል ምናለ በኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ምክር ቤት የፕሮግራምና ዴቨሎፕመንት አማካሪ ሲሆኑ ምክር ቤቱ በቅርቡ በአዋጅ የተቋቋመ ሲሆን የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚወክል፣ የሚመራ፣ የሚያስተባብርና ዘርፉን የሚቆጣጠር ሲሆን በዚሁ ዘርፍ የተለያዩ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

ሚዲያው የስርዓተ ፆታ ጉዳይን ከማጉላት አንፃር በእርግጥም ሚናውን እየተወጣ ነው ለማለት ዝርዝር ጥናት ይፈልጋል። ሆኖም ከብዙ አንግል ማየት ይቻላል። ለአብነትም ሴቶችን ምን ያህል አካቷል፣ ሴቶች ሴክተሩን ከመምራትና በባለቤትነት ከመያዝ አንፃር፣ በጋዜጠኝነትና በኃላፊነት ከመስራት አኳያስ ያላቸው ሚና ምን እንደሆነ መፈተሽ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከሚፈለገው ማህበረሰባዊ ለውጥ አኳያ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰራው ስራ ምን ያህል ነው? ምን ያህልስ በቂ ነው? የሚለውን መጠየቅ ይገባል። ከዚህና ከሌሎችም አንፃር ከታየ ሚዲያው የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከማረጋገጥ አንፃር ብዙ ክፍተት አለበት የሚል እምነት አለ።

ይህንኑ ክፍተት ለመሙላትም ብዙ ስራ መስራት ይጠበቃል የሚሉት አቶ ቃለወንጌል፤ በተለይ የሲቪል ማህረሰቡና ሚዲያው ተቀናጅተው በቅርበት መስራት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በስርአተ ጾታ ጉዳይ ዙሪያ የሚሰራው ስራ ማህበረሰባዊ ለውጥና ሽግግር ከማምጣት አኳያ ምን ያህል በቂ ነው የሚለውን መመልከት እንደሚገባ ይገልፃሉ።

የስርዓተ ፆታ እኩልነት ላይ ስራዎች አጠናክሮ መስራት እንደሚያስፈልግም ይጠቅሳሉ። ነገር ግን የሲቪል ማህበራት ይህን ክፍተት እንዴት ያዩታል ምክንያቱስ ምንድን ነው? የሚለውን ለመመለስ ዝርዝር ጥናቶች እንደሚስፈልጉ ነው የሚጠቁሙት። ምክር ቤቱም ይህንን ክፍተት በመረዳት ከሚመለከታቸው አካላትና ከተለያዩ የስርዓተ ፆታ ተኮር ድርጅቶች ጋር ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ያስረዳሉ።

# ዓለም አቀፍ



## አሳሳቢው የምስራቅ አፍሪካ ድርቅ የለጋሽ አገራት አስቸኳይ ምላሽ ይሻል

ለጋሽ አገራት ለምስራቅ አፍሪካ ድርቅ አስቸኳይ ድጋፍ ካላደረጉ በአስር ሚሊዮን የሚቆጠሩ አደጋ ላይ እንደሚወድቁ ዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ድርጅት ኮሚቴ ማሳሰቡን ሮይተርስ ዘግቧል።

ለጋሽ አገራት በድርቅ ምክንያት ለረሃብ የተጋለጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቀጠናው ዜጎች ሕይወት ለመታደግ አስቸኳይ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው። ድጋፉን ለማድረግ የቀጠናው ረሃብ እስኪታወጅ መጠበቅ እንደሌለበት ኮሚቴው አሳስቧል።

ኢትዮጵያ፣ ኬንያና ሶማሊያ ከ40 ዓመታት ወዲህ በዓይነቱ እጅግ አስከፊ በሆነ ድርቅ እየተጠቁ ሲሆን አገራቱ በአምስት ተከታታይ የዝናብ ወቅት ዝናብ ባለማግኘታቸው በተያዘው የፈረንጆቹ ዓመት ከመገባደዱ በፊት በተለይ በሶማሊያ ረሃቡ እንዲታወጅ ማሰቡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መግለጹ ሮይተርስ በዘገባው አመላክቷል።

የኮሚቴው ፕሬዝዳንት ዴቪድ ሚሊባንድ በቀጠናው ያደረጉትን ጉብኝት ተከትለው “የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አዋጁን በመጠባበቅ ላይ እንዳይቀዘቅዝ እለምናለሁ” ብለዋል።

ፕሬዚዳቱ፣ በዩክሬን ቀውስ ምክንያት የለጋሾችን ገንዘብ ወደ ሌላ አቅጣጫ መቀየሩ አሁን ላይ ለምስራቅ አፍሪካ ድጋፍ እያደረገች ያለችው አሜሪካ ብቻ ነው ካሉት በኋላ በምስራቅ አፍሪካ በሁሉም ቦታ የገንዘብ ፍላጎት ወይም ድጋፍ የሚፈልግ ድምፅ ጎልቶ እየተሰማ ነው ብለዋል።

እ.ኤ.አ. በ2011 በሶማሊያ በመጨረሻው ረሃብ ከሞቱት ሰዎች መካከል ግማሽ ያህሉ ረሃብ ከመታወጁ በፊት መሆኑን የተናገሩት ዴቪድ ሚሊባንድ ፤ በምስራቅ አፍሪካ በአየር ንብረት ለውጥ የተከሰተው ድርቅ እና በዓለም አቀፍ የምግብ ዋጋ መናር በቀጠናው ትልቅ ስጋት መደቀኑንም የዘርፉ ባለሙያዎችን ጠቅሰው ገልጿል።

በቀጠናው ዘጠኝ ሚሊዮን ከብቶች እንደሞቱ ሲገምት በደቡብ ሶማሌ በባይዶዋ ከተማ በረሃቡ ምክንያት ምግብና ውሃ ፍለጋ አካባቢያቸውን ጥለው የሚሄዱ የሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል።

በጥቅሉ በአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰቃዩ ያሉ እንደ ሶማሊያ፣ ኢትዮጵያ እና ኬንያ ያሉ አደግ አገሮች የገንዘብ ድጋፍ ቢያስፈልጋቸውም በግብፅ ላይ በተደረገው ስብሰባ የአየር ንብረት ለውጥን ተፅእኖን ለመቋቋም የሚያስችል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

## ሩሲያ ፖላንድ መንደር ውስጥ ለወደቁት ሚሳኤሎች ኃላፊነት አልወስድም አለች

ፖላንድ ማክሰኞ እለት ሩሲያ ሰራሽ ሚሳኤሎች ሁለት ንጹኃን ዜጎቿ መገደላቸውን በመግለጿ ተከትሎ ሩሲያ በጉዳዩ ኃላፊነት እንደማትወስድ አስታወቀች። ገድለዋል ብላለች።

ሚሳኤሎቹ ለዩክሬን ድንበር ቅርብ በሆነች የፖላንድ መንደር ውስጥ የሁለት ሰዎች ሕይወት ማጥፋታቸው ተከትሎ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ውጥረት በተለይም በምዕራባዊያኑ አገራት መሪዎች ዘንድ ተከስቷል።

በቡድን 20 አገራት ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ በኢንዶኔዢያዋ ደሴት ባሊ የሚገኙት የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን፣ በፖላንድ ላይ የተከፈተው ጥቃት ከሩሲያ የመሰንዘር ዕድሉ አነስተኛ መሆኑን ገልጸው ነበር።

ፕሬዝዳንቱ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች ጥቃቱ በእርግጥም ‘’ከሩሲያ በተተኮሰ ሚሳኤል ተፈጽሟል’’ የሚለውን ሐሳብ ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው ብለዋል።

ሩሲያ የቀረበባትን ክስ ያስተባበለች ሲሆን ‘’ሩሲያ በዩክሬን እና በፖላንድ ድንበር ላይ ምንም ዓይነት ጥቃት አልከፈተችም’’ ሲሉ የሩሲያ የመከላከያ ሚኒስትር ተናግረዋል።

በአገራቸው ላይ የቀረበው ክስ ‘’ሆን ተብሎ ሁኔታውን ለማባባስ የተደረገ ነው’’ ሲሉም ተናግረዋል።

በጉዳዩ ላይ አስቸኳይ ስብሰባ ሲያካሂዱ የቆዩት ጆ ባይደን ‘’ምርመራችንን ሙሉ በሙሉ እስከሚናጠናቅቅ ብዙ መናገር አልፈልግም። ነገር ግን መስመሩን ተመልክተን ከሩሲያ የተተኮሰ የመሆን ዕድሉ ጠባብ መሆኑን መናገር ይቻላል። ግን የምናየው ይሆናል’’ ሲሉ አክለዋል።

የኔቶ አባል የሆነችው ፖላንድ ሩሲያ ዩክሬንን ከወረረች ወዲህ በግጭቱ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ከርማለች። የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ማቴውስ ሞራዊስኪ ዜጎቻቸው እንዲረጋጉ የጠየቁ ሲሆን የአገሪቱ የአየር ክልል ላይ የሚደረገው ጥበቃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።



የአገሪቱ ፕሬዝዳንት አንድሬ ዱዳ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት ጥቃቱን የፈጸመው ማን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኖ ለመናገር የሚያስችል ድምዳሜ ላይ ገና መድረስ አልተቻለም።

‘’እስካሁን ድረስ ሚሳኤሉን ማን እንደተኮሰው የሚያሳይ የተሟላ መረጃ የለንም። ነገር ግን ሚሳኤሉ ሩሲያ ሠራሽ የመሆኑ ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ይሄ ምርመራ እየተደረገበት ያለ ጉዳይ ነው’’ ሲሉ ፕሬዝዳንቱ ተናግረዋል።

በጉዳዩ ላይ የቡድን 7 አገራት አስቸኳይ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፣ ፖላንድ የኔቶን ሕግ አንቀጽ 4 ትተገብራለች ተብሎ ይጠበቃል።

ይህ አንቀጽ አንድ የኔቶ አባል አገር ጥቃት በደረሰባት ወቅት አስቸኳይ የኔቶ አምባሳደሮች ስብሰባን የመጥራት መብትን ይሰጣታል።

በስብሰባውም አገሪቱ ሉዓላዊነት፣ ፖለቲካዊ ነጻነቷ ብሎም ደኅንነቷ መጣስ አለመጣሱን የተመለከተ ውይይት ይደረጋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ሐሙስ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በታዳጊዎች ስኬታማነት የሚተጋው የውሃ ስፖርቶች

**ብርሃን ፈይሳ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ እምብዛም በማትታወቅባቸው ስፖርቶች ተስፋ ያለው ውጤት እያስመዘገበች ትገኛለች። ይህ የተገኘው ደግሞ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ሀገራቸውን ወክለው ተካፋይ በሆኑ ታዳጊዎች ነው። በእርግጥም መሰረቱን በታዳጊዎች ላይ ያደረገ ስፖርት ውጤታማ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት ሀገራት በታዳጊና ወጣቶች ላይ በማተኮር እና ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ይሰራሉ።

ስፖርተኞችን ከታዳጊነታቸው አንስቶ በዘመናዊ ስልጠና አቅማቸውን ማጎልበት እንዲሁም ልምድ እንዲያገኙ በውድድሮች ላይ ማሳተፍ ሀገርን ለረጅም ጊዜ በስኬታማነት እንዲወክሉ በማድረግ ረገድ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በሀገር አቀፍ ደረጃ የታዳጊ ፕሮጀክቶች አተኩሮ የሚሰራ ፕሮግራም ተቀርጾ እየተሰራበት ይገኛል። ከትምህርት ቤቶችና ከፕሮጀክቶች የተገኙ ታዳጊ ስፖርተኞችም በእድሜያቸው ከሚካሄድ ውድድር ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገርን እስከማኩራት መድረሳቸውም በተግባር እየታየ ይገኛል። ለአብነት ያህልም ኢትዮጵያ በማትታወቅበት የወርልድ ቴኳንዶ ስፖርት ከዓለም ቻምፒዮና እስከ ኦሊምፒክ የደረሰ ተሳትፎ ያገኘችው



**የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰረት ደምሱ፤**

በታዳጊ ስፖርተኛ ነው። በቅርቡም በፈረስ ስፖርት የተገኘውን ስኬት ማንሳት ይቻላል።

ይህንን ተከትሎም የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ታዳጊ ዋናተኞችን የሚያበረታታና ስፖርቱንም በዘላቂነት ለማሳደግ የሚችል እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። የአፍሪካ የውሃ ማማ በመባል የምትታወቀው ኢትዮጵያ ካላት የተፈጥሮ ጸጋ አንጻር ምቹ ከሆኑ ስፖርቶች መካከል አንዱ የውሃ ዋና ነው። ሀገሪቷ በውሃ ሃብት የበለጸገች ትሁን እንጂ በስፖርቱ ያለችበት ሁኔታ እንዲሁም ተዘውታሪነት ግን አነስተኛ ሊባል የሚችል ነው። ከዚህ ባለፈ ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ሁለት ኦሊምፒኮች ላይ (ሪዮ እና ቶኪዮ ኦሊምፒኮች) በውዝግብ የታጀበ ተሳትፎ ማድረጓ ስፖርቱ ያለው ስም እንዲጠለሽ ምክንያት ሆኗል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ትኩረቱን በተለይ ታዳጊዎች ላይ አድርጎ እየሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰረት ደምሱ ይጠቁማሉ። ለዚህ ማሳያ የሚሆነውም ከትላንት አንስቶ በታንዛኒያ እየተካሄደ ባለው የምስራቅ አፍሪካ ዞን ሶስት የውሃ ዋና ቻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያ በታዳጊዎች እንድትወከል መደረጉን ነው። ቻምፒዮናው የሚካሄደው በተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች ቢሆንም ፌዴሬሽኑ የሚያሳትፈው ግን ከ14 እና 17 ዓመት በታች ዋናተኞችን ብቻ ነው። እነዚህ ስፖርተኞች የተመረጡት ከኢትዮጵያ ቻምፒዮና ላይ ሲሆን፤ በውድድሩ ተካፋይ የነበሩት ምንም ዓይነት የውድድር እድል ያላገኙና በታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክቶች የተወጣጡ ዋናተኞች ብቻ ነበሩ።

ይህም የሚደረገው እንደ ሀገር ለውጥ መምጣት ስላለበት እና ተተኪዎችን ለማፍራት እንደሆነም ፕሬዚዳንቷ ያስገነዝባሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ፌዴሬሽኑ ከዓለም አቀፉ የውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ጋር በመሆን የታዳጊ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽና የተለያዩ ድጋፎችንም በማድረግ እየሰራ ይገኛል። በተለያዩ ክልሎች ለተከፈቱት ፕሮጀክቶች የስልጠና መሳሪያዎች፣ የዋና ልብሶች እና ሌሎች ድጋፎችን ከመስጠት ባለፈ ከክልል የውሃ ስፖርት ፌዴሬሽኖች ጋር በቅርበት በመነጋገር እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር በማድረግም እየሰሩ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የውሃ ስፖርት ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ነገር ግን ባለው ነገር የተሻለ ለመሆን መስራት የሚለው በአሁኑ ወቅት ፌዴሬሽኑን እየመራ የሚገኘው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የአራት ዓመት የስራ ዕቅድ ነው። በመሆኑም የታዳጊ ፕሮጀክቶችን ከማቋቋምና ድጋፍ ከማድረግ ባለፈ፣ በሀገር ውስጥ ውድድሮችን በማዘጋጀትና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይም በመሳተፍ ልምድ እንዲገኝ እየተደረገ መሆኑንም ወይዘሮ መሰረት ይገልጻሉ። ይህም በቶሎ ውጤታማ ባያደርግም በጊዜ ሂደት ግን በስፖርቱ ተተኪዎችን ለማፍራትና እንደሀገርም ስኬታማ ለመሆን የሚያስችል ነው። ለዚህም ባለድርሻ የሆኑ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡና ከፌዴሬሽኑ ጎን እንዲቆሙም ነው ፕሬዚዳንቷ ጥሪ ያቀረቡት።